Samara University

2024/25
Annual Magazine
Third Edition ሦስተኛ ዕትም

የ 2017 ዓ.ም

የሠመራ ዩኒቨርሲቲ አመታዊ መጽሔት



www.su.edu.et

ማውጫ

የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

1 የአዘጋጁ መልእክት

2 ሀገራዊ መድረኮች

3 ጉብኝት

4 የዩኒቨርሲቲ መድረኮች

5 ምርምር የሥራ ክንውን

6 አቅም ግንባታ ሰልጠና

7 መማር ማስተማር

8 ጉድኝት

9 ልዩ ልዩ

10 ዲጂታል

11 ግቢ ውበት

12 ማህበረሰብ ሳምንት

Samara University
2024/25
Annual Magazine
Third Edition ሦስተኛ ዕትም
የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

የአዘጋጁ መልእክት

ይህ መጽሔት በዋናነት ተቋማዊ መረጃዎችን ተደራሽ ለማድረግና የዩኒቨርሲቲያችንን ሁለንተናዊ ገጽታ ለውድ አንባቢዎቻችን ለማስተዋወቅ ታስቦ የተዘጋጀ ነው። በመሆኑም በመጽሔቱ ውስጥ ዩኒቨርሲቲያችን እያከናወናቸው ያሉትን የምርምር፣ የማስተማርና የመማር እንዲሁም የማህበረሰብ አገልግሎት ተግባራትን በሰፋት የሚያስቃኙ መረጃዎች ተካተዋል።

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ በአሁኑ ወቅት የላቀ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥና በሀገራዊ የልማት ግቦች ውስጥ የራሱን አሻራ ለማሳረፍ ሰፊ የለውጥ ጉዞ ላይ ይገኛል። ይህ ተቋማዊ የለውጥ ጉዞ ከዳር ሊደርስ የሚችለው ደግሞ የእናንተ—የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች ንቁ ተሳትፎ፣ ጥረትና ቁርጠኝነት ሲታከልበት ብቻ ነው። እያንዳንዱ ሰራተኛ የለውጡ ባለቤት በመሆን፣ የጋራ ራዕያችንን ለማሳካት የሚጠበቅበትን የላቀ አገልግሎት እንዲሰጥ ጥሪያችንን እናቀርባለን። ይህ መጽሔት ስለ ተቋማችን ያለዎትን ግንዛቤ እንደሚያሰፋና ለተሻለ ሥራ መነቃቃትን እንደሚፈጥር ተሰፋ እናደርጋለን።

መልካም ንባብ!

የአዘጋጆች

- ዋና አዘጋጅ — መሀመድ አህመድ አበጋር
- ም/ አዘጋጅ — ይሰፋዘር ከበደ አሸንጎ
- አርታኦት — አብዱፈታህ መላኩ መኮነን
- ፎቶ ግራፈር — ያሬድ አለሙ አበበ

የፕሬዝዳንት መልዕክት



ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ብዝሃነት የሚከበርበት፣ ተሰጥኦ የሚጎለብትበት እና እውቀት የሚገበይበት፣ የማህበረሰብ የእርስ በርስ ግንኙነት የሚዳብርበት፣ ትልቅ እሴት ያለው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ ላለፉት ሁለት አሰርት አመታት እያገለገለ መጥቷል። ዩኒቨርሲቲው ከአካዳሚክ ተቋምነት ባሻገር የሰላምና አብሮ የመኖር ምልክት፣ ለዓመታት በአንድነት፣ በመከባበር የሚኖርበት የትንሿ ኢትዮጵያ ተምሳሌት የሆነ ተቋም ነው። ይህም ተቋማዊ እና ሀገራዊ ተልዕኮን አንግቦ እየሰራ ያለ እና በሰኬታማ የለውጥ ጎዳና ላይ እንዲገኝ አስችሎታል።

በኢትዮጵያ የትምህርት ፍኖተ ካርታ ውስጥ ቁልፍ ተዋናይ እንደመሆናችን መጠን የሀገሪቱን የሰው ኃይል ፍላጎት ለማሟላት እና የኢኮኖሚ ብዝሃነትን ለማሳደግ ቁርጠኞች ሆነን እየሰራን እንገኛለን። ለአብነት ያህል "የመማር ፍላጎት ያለው ሰው ሁሉ የሚፈልገውን ትምህርት ማግኘት አለበት" በሚል ፅኑ እምነት “የአርብቶ አደር ሴቶች ስኮላርሽፕ ፕሮጀክት” በማመቻቸት ባለፉት 4 ዓመታት ብቻ ከ 300 በላይ ሴቶችን በሁለተኛ ድግሪ በማስተማር በሁሉም ዘርፍ የሴቶችን ተሳትፎ ማሳደግ ተችሏል።
የትኩረታችን ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት በመስጠት፣ ተግባር ተኮር ምርምር በመስራት፣ወደ ተግባር ተኮር ዩኒቨርሲቲነት መሸጋገር፣ እንዲሁም ራስገዝ ተቋም ሆኖ መገኘት እና በማህበረሰብ-ተኮር መፍትሄዎች ላይ መስራት ነው። ይህንም ለማሳካት ዩኒቨርሲቲው በግብርና፣ በማዕድን እና በቱሪዝም ዘርፎች ላይ የልዕቀት ማእከልን በማድረግ በዙሪያው ባሉ ሀብቶችን እና እድሎች ሰፊ ሰራ እየሰራ ነው። ይህን የሚደግፉ የቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ እና በማህበረሰብ ፍላጎት ላይ መሰረት ያደረጉ ሰራዎችን በመስራት የበለፀገች ኢትዮጵያን ለመፍጠር በሚደረገው የለውጥ እንቅስቃሴ ውስጥ የበኩላችንን አስተዋፅኦ እናደርጋለን።

Samara University
2024/25
Annual Magazine
Third Edition ሦስተኛ ዕትም
የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

አለምአቀፍ መድረክ ዘጠኝ ዩኒቨርሲቲዎች የተሳተፉበት የMAKERSPACE አለም አቀፍ አውደ ጥ

በሰመራ ዩኒቨርሲቲ 4 አለም እና 5 ሀገር አቀፍ ዩኒቨርሲቲዎች የተሳተፉበት የኢትዮጵያ እና የጅቡቲ ሴቶችን ወደሰራ ፈጠራ የሚያሰገባ Makerspace አለም አቀፍ አውደ ጥናት ተካሂዷል::



የMakerspace ፕሮጀክት ከአውሮፖ ህብረት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ የሚተገበር ሴቶችን ለኢንዱስትሪ ግብአት የሚሆኑ ምርቶችን ማምረት እንዲችሉ የሚያደርግ በተመረጡ የተግባር ዩኒቨርሲቲዎች የሚተገበር አለም አቀፍ ፕሮጀክት ነው:: አውደ ጥናቱ “Empowering Hands, Empowering Minds” በሚል መሪ ሀሳብ ገለጻዎችና ውይይቶች ቀርበውበታል።



ሀገራዊ መድረኮች

21ኛው የትምህርት ጉባኤ "የማህበረሰብ ተሳትፎ ለትምህርት ጥራት



በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት 21ኛው የትምህርት ጉባኤ "የማህበረሰብ ተሳትፎ ለትምህርት ጥራት " በሚል መሪ ቃል የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሀኑ ነጋ፣ የክልል አመራሮች፣ የክልል ትምህርት ቢሮ፣ ሰመራ ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም የትምህርት ባለድርሻ አካላት ተካሂዳል።

በትምህርት የሀገራችንን ተተኪ ትውልድ የምናፈራበት በመሆኑ ያለማህበረሰቡ ተሳትፎ ይህን ማሳካት ሰለማይቻል በትምህርት ዙሪያ የተሰማራን አካላት ማህበረሰቡን ለትምህርት ትኩረት እንዲሰጥ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ይገባል ሲሉ የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሀኑ ነጋ ተናግረዋል።



ሀገራዊ መድረኮች

የምግብ ዋስትናና ስነ-ምግብ የውይይት መድረክ በአፋር ክልል



የአፋር ክልል ርዕሰ መስተዳደር ክቡር ሀጂ አወል አርባ በመድረኩ እንደተናገሩት፣ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ የመንግሥትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ስራ ብቻ ሳይሆን የግሉ ዘርፍም ኃላፊነት መሆኑን በመገንዘብ በጋራ መከናወን ያለበት ተግባር ነው ብለዋል።

የሰለዚህ የምግብና ስነ-ምግብ ምክር ቤት መቋቋም የእመጋገብና የምግብ ዋስትና ዘርፉን ለማጠናከር ምግብ እና የተመጣጠነ ምግብ ችግሮችን ለመፍታት ጠቃሚ እንደሆነ ተመላክቷል።



ሀገራዊ መድረኮች

የአርብቶ አደር ትምህርት የፖሊሲ ገፅታ በኢትዮጵያ" ኮንፈረንስ



የአርብቶ አደሮችን የአኗኗር ሰርዓት የተከተለ አካታች የትምህርት ተደራሽነትን ማጎልበት የጥናት ና ምርምር ሰራዎች ሚናቸው የጎላ መሆኑ ተገለፀ ።

ለአርብቶ አደር ትምህርት ተደራሽነትና ፍትሃዊነት የዘርፉ ጥናት አቅራቢዎችና ባለሙያዎች የጎላ ሚና እንዳላቸው ጠቅሰዋል። በዘርፉ የሚስተዋሉትን ልዩ ልዩ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ እንዲሁም በጥልቀት መርምሮ መፍትሄ ለማበጀት የጉባኤው ጠቀሜታ ነው።

ከአገራችን የቆዳ ሰፋት 60 በመቶውን እንዲሁም ከህዝብ ቁጥሩ 15 በመቶውን የሚይዘው የአርብቶ አደር አካባቢ ሲሆን ቀጣይነት ያላቸው የምርምር ሰራዎችን በመሥራት የአርብቶ አደሩን የትምህርት ተደራሽነት ለማሻሻል የምሁራኑ ሚና ከፍተኛ መሆኑንም ተገልጿል። ጉባኤው ለፖሊሲ አውጪዎች ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ ጥናቶች ቀርበው ውይይት ተካሂዶበታል።



ሀገራዊ መድረኮች

የህንድ መምህራን አስተዋፅኦ በኢትዮጵያ የትምህርት ዘርፍ

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር መሀመድ ኡስማን "የህንድ መምህራን አስተዋፅኦ በኢትዮጵያ የትምህርት ዘርፍ" በተዘጋጀው ኮንፈረስ ባደረጉት ንግግር የህንድ መምህራንን አመሰግነዋል።

የህንድ መምህራን ለአካዳሚክ ልህቀት፣ መካሪነት፣ ጥናትና ምርምር እና የባህል ልውውጥ ያደረጉትን አስተዋጾ በመጥቀስ ዘላቂውን የኢትዮጵያ-ህንድ አጋርነት አበረታቷል።

ዶ/ር መሀመድ ኡስማን የኢትዮጵያን የትምህርት ሰርዓት የበለጠ ለማሳደግ የተጠናከረ ትብብር፣ የጋራ ምርምር እና ሙያዊ እድገትን ጠይቀው የህንድ መምህራን እና ኤምባሲው በኢትዮጵያ የትምህርት እድገት ላደረጉት ድጋፍ ምስጋና አቅርበዋል።



ሀገራዊ መድረኮች የ2017 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ብሄራዊ ፈተና



በዩኒቨርሲቲው በሁለት ዙር 4ሺ 8መቶ 53 ተማሪዎች ለፈተና እንደሚቀመጡ እና በመጀመሪያው ዙር 2ሺ 7መቶ 55 የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪዎች የሚፈተኑ ሲሆን፣ 5መቶ 52 በበይነመረብ፣ቀሪዎቹ በወረቀት እንደሚፈተኑ ተገልጿል:: ከ2ሺ 7መቶ 55 ተፈታኞች ውስጥ 9መቶ 43ቱ ሴቶች መሆናቸው ተመላክቷል::







ጉብኝት ርዕሰ መስተዳድር አቶ አወል አርባ የአፋር ታለንት አካዳሚ ጉብኝት



ርዕሰ መስተዳድር ሀጅ አወልአርባ እንደገለፁት የአፋር ታለንት አካዳሚ የተሻለ አቅም ያላቸው በሰነ-ምግባር የታነፀና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የነገ ሀገር ተረካቢ ትውልድ ለመቅረፅ አላማ ያደረገ ሲሆን ለወደ ፊት አላማቸውን ለማሳካት ዛሬ ላይ በርትተው መማር እንደሚገባቸው አሰገንዝበዋል።



የሠመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት መሐመድ ኡስማን(ዶ/ር) በበኩላቸው፤ አካዳሚው በትምህርት ዘርፉ ያለውን ሰብራት ለመጠገን የሚረዳ መሆኑን ተናግረዋል።



ጉብኝት የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሀኑ ነጋ ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ጉብኝት ::





የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስተር ፕሮፌሰር ብርሀኑ ነጋ በሰመራ ዩኒቨርሲቲ ተገኝተው የአፋር ታላንት አካዳሚን ፣ ሬደ ባህል ማእከልን ጨምሮ በግቢው እየተከናወኑ ያሉ የልማት ሰራዎችን ተዘዋውረው ተመልክተዋል።

ሚኒስትሩ በዩኒቨርሲቲው ጉብኝት ያደረጉት በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በተዘጋጀው "የማህበረሰብ ተሳትፎ ለትምህርት ጥራት " በሚል መሪ ቃል እየተካሄደ ባለው በ21ኛው የትምህርት ጉባኤ በተገኙበት ወቅት ነው።

የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሀኑ ነጋ በሰመራ ዩኒቨርሲቲ ተገኝተው የአፋር ታላንት አካዳሚን ፣ ሬደ ባህል ማእከልን ጨምሮ በግቢው እየተከናወኑ ያሉ የልማት ሰራዎችን ተዘዋውረው ተመልክተዋል።

ጉብኝት የአሶሳ እና የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንቶች ጉብኝት



ሀገራዊ ትስስርን ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ በተወሰደው እርምጃ የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ከማል አብዱረሂም እና የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ዋቆ ገዳ ከልዑካኖቻቸው ጋር ሰመራ ዩኒቨርሲቲን ጎብኝተዋል።

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር መሀመድ ኡስማን ከማኔጅመንት ካውንሰል ጋር በመሆን ዩኒቨርሲው አሁን ያለበት ደረጃ ላይ ጥልቅ ገለጻ በማድረግ ወደ አፕላይድ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲ በመሸጋገር ላይ ያተኮሩ ሰራዎችን እና ውጥኖችን አሳይተዋል።

ይህ ጉብኝት የዩኒቨርሲቲዎች ትብብር በኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት ገጽታ ላይ ያለውን ጠቀሜታ አጉልቶ ያሳያል።

ጉብኝቱ በተሳታፊ ተቋማት የሚሰጡ የትምህርት ልምዶችን የበለጠ ለማሳደግ በሚችሉ አጋርነቶች፣ በምርምር ትብብር እና ምርጥ ተሞክሮዎችን በማካፈል ዙሪያ የትብብር ሰራ ውጤት መሆኑ አመላክቷል።



ጉብኝት የአፋር ዲያስፖራ አባላት የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ጉብኝት



በአሜሪካ የሚኖሩ የአፋር ዲያስፖራ አባላት በሰመራ ዩኒቨርሲቲን ጎብኝተዋል። በጉብኝታቸው ወቅትም በክልሉ ያለውን ትምህርታዊ እና ባህላዊ እንቅስቃሴዎች ለመደገፍ ያላቸውን ቁርጠኝነት አመልክተዋል።

የልዑካን ቡድኑ በዩኒቨርሲቲው የሚገኘውን የአፋር ታሊንት አካዳሚ እና የዶ/ር ሬዶ የባህልና አገር በቀል የዕውቀት ጥናት ማዕከልን ጎብኝተው ለአካዳሚው እድገት ድጋፍ ለማድረግ ያላቸውን ቁርጠኝነት ገልጸዋል።

በተጨማሪም ዩኒቨርሲቲው የአፋርን ባህልና ቅርስ ለመጠበቅና ለማስተዋወቅ ወሳኝ ግብአት ሆኖ የሚያገለግለውን ማዕከሉን ለማቋቋም ያደረገውን ጥረት አድንቀዋል።





ጉብኝት የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ጉብኝት



የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ባዘጋጀው ትምህርታዊ ጉብኝት የሰመራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና የመግለኪቦ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በዶ/ር ሬዶ የባህልና አገር በቀል ጥናቶች ማዕከል ጎብኝት አድርገዋል።

ጉብኝቱ ተማሪዎች ለባህል ፣ ለታሪክ እና ለትምህርት ያላቸውን ግንዛቤ በማጎልበት ፣ ቀደምት አባቶች/እናቶች የሰሩትን የማድነቅ ባህል እንድኖራቸው እና እነሱ በተራቸው በትምህርታቸው ጠንክረው ሰርተው የማህበረሰቡን ኑሮ የሚያሻሽሉ ፈጠራዎችን ለመሰራት ተነሳሽነትን እንዲኖራቸው ለማድረግ ያለመ ነው።



Samara University
2024/25
Annual Magazine
Third Edition ሦስተኛ ዕትም
የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

ዩኒቨርሲቲ መድረኮች

2ተኛው አለምአቀፍ ኮንፈረንስ

ለሁለት ቀናት ሲካሄድ የነበረው 2ተኛው አለምአቀፍ የምርምር ኮንፈረንስ በስኬት ተጠናቋል:: ኮንፈረንሱ "ተግባራዊ እውቀትን ለአርብቶ አደር እና ከፊል-አርብቶ አደር ማህበረሰቦች ለውጥ ጥቅም ላይ ማዋል" በሚል ርዕሰ ነበር::





24 የምርምር ውጤቶች የቀረቡበት እና ከአውሮፓ -ጣሊያን፣ ከኤሲያ-ቻይና፣ከአፍሪካ-ኬንያ እንዲሁም ከካናዳ እና ከሀገራችን የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ምሁራን እና ከፌደራል እና ክልል መንግስት ተጋባዥ እንግዶችን ያሳተፈው 2ተኛው አለምአቀፍ የምርምር ኮንፍረንስ ተካሂዷል::

በኮንፈረንሱ የቀረቡ የቱሪዝም: የግብርና:የሰነ-ምድር:ሰነ-ህይወት እና የሰብአዊ መብት ጥናቶችን በተመለከተ ሰፊ ውይይት የተደረገ ሲሆን ከተሳታፊዎች የተነሱ ጥያቄዎችን ተመራማሪዎቹ ምላሽ በመስጠት ሁሉንም ያሳተፈ ኮንፈረንስ ተካሄዷል።



Samara University
2024/25
Annual Magazine
Third Edition ሦስተኛ ዕትም
የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

ዩኒቨርሲቲ መድረኮች

የ2017 ሩብ ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ግምገማ



የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ካውንሰል የ2017 ትምህርት ዘመን የሩብ ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ግምገማና ውይይት አካሂዷል:: በዩኒቨርሲቲው ያሉ የሁሉም ሰራ ክፍሎች የሩብ አመት የእቅድ አፈፃፀም በስትራቴጅክ ጉዳዮች ሰራ አስፈጻሚ ለካውንሰል ቀርቧል።

በተሳታፊዎች አስተያየት እና ጥያቄ ተነስቶ ማብራሪያና ውይይት ከተደረገበት በኃላ በቀጣይ ሰራዎች ላይ የጋራ መግባባት ላይ አቋም ተይዟል::



ዩኒቨርሲቲ መድረኮች የ2017 1ኛ ሩብ አመት የሰራ አፈፃፀም ሪፖርት ግምገማ



የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝደንት መሀመድ ኡስማን (ፒኤችዲ) ከከፍተኛ አመራሮች ጋር የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ቦርድ የ2017 በጀት አመት 1ኛ ሩብ አመት የሰራ አፈፃፀም ሪፖርት ሰፊ ዘገባ አቅርበዋል:: በመቀጠልም የቦርድ ሰብሳቢ አቶ ሰለሺ ግርማ ከተከበሩ የቦርድ አባላት ጋር በሪፖርቱ ላይ ጥልቅ ግምገማ አድርገዋል።

በውይይቱ ዩንቨርስቲው ከ2016 ዓ.ም ጋር ሲነጻጸር እቅዶቹን አፈጻጸም ላይ ያሳየውን ጉልህ እድገት አመላክቷል።

ቦርዱ ወደ ተግባራዊ ሳይንስ ፈጣን ሽግግር አስፈላጊነትን አፅንዖት ሰጥቷል፣ ይህም በልህቀት ዘርፎች ማለትም በደረቅ መሬት ግብርና፣ ቱሪዝም እና ማዕድን ላይ በማተኮር ነው።

በተጨማሪም የሀገር አቀፍ መልቀቂያ ፈተናን በተሳካ ሁኔታ ማለፍ የሚችሉ ጥራት ያላቸው ተመራቂዎችን በማፍራት ረገድ የሚደረገውን ጥረት ማጠናከር እንደሚገባ አሳስበዋል።

ቦርዱ የ1ኛ ሩብ አመት ሪፖርትን ገምግሞ ሲያፀድቅ የዩኒቨርሲቲው አካሄድ እና ተማሪዎችን ለቀጣይ ፈተናዎች የሚያዘጋጅ ጠንካራ የአካዳሚክ አካባቢን ለማጎልበት ያለውን ቁርጠኝነት ገልጿል።

በአላት

የአፋርኛ ቋንቋ የፊደል አጻጻፍ 50ኛ ዓመት የምስረታ በዓል



የአፋርኛ ቋንቋ የፊደል አጻጻፍ ሰልት 50ኛ ዓመት የምስረታ በዓል በጅቡቲ ከተማ የተከበረ ሲሆን ይህም አፋርኛ ቋንቋን የምርምር ቋንቋ ለማድረግ ትልቅ ምዕራፍ ያሳየ ነው።

በመርሀግብሩ ላይ የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶክተር መሀመድ ኡስማን እና የጅቡቲ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ አብዱልቃድር መሀመድ የእውቅና ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።

50ኛ ዓመት የምስረታ በአል አከባበር ያለፉትን ድሎች ከማክበር ባለፈ የአፋርኛ ቋንቋ በሰነጽሁፍ፣በመገናኛ ብዙሃን እና በቴክኖሎጂ ያለውን ሚና ለማሳደግ ለሚደረገው ጥረት መሰረት ጥሏል።



በአላት

የኤች.አይ.ቪ ኤድስ: አካል ጉዳተኞች እና የነጭ ሪባን ቀን



የኤች.አይ.ቪ ኤድስ ቀን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ37ኛ፣ በኢትዮጵያ ለ36ኛ ጊዜ "ሰብአዊ መብትን ያከበረ የኤች አይ ቪ አገልግሎት ለሁሉም!" በሚል መሪ ቃል ተከብሯል::

መድረኩን የዩኒቨርሲቲው የሴቶች እና ማህበራዊ አካቶ ሥራ አስፈጻሚ ከአቶ/ብ/ክ/መ የኤች.አይ.ቪ ኤድስ መከላከል እና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ጋር በጋራ ያዘጋጁት ሲሆን በመድረኩ ኤች.አይ.ቪ ኤድስ በሀገራችን የተዘነጋ የሚመስል ነገር ግን በጣም እየተሰፋፋ እንደሆነ በመጥቀስ የወረርሽኙን ሰርጭት ለመግታትና ለመቆጣጠር ሁሉም የበኩሉን ሊወጣ እንደሚገባ ተመላክቷል።

የአካል ጉዳተኛ ወገኖችን እኩል ተጠቃሚነት እና የአካል ጉዳትን ያገናዘበ አገልግሎት እንዲኖር ለማስቻል የሁሉምን ጥረት እንደሚሻ ተገልጿል።

ነጭ ሪባን ቀን ሴት ሕፃናትና እናቶች በጾታቸው ምክንያት አካላዊ፣ ሥነ ልቦናዊ፣ ወሲባዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቃቶች የሚደርሰባቸው በተዛባ አመለካከት በመሆኑ ጥቃቶችን ለማስቆም ሁሉም ይመለከተኛል ብሎ መታገል እንደሚገባው በውይይት መድረኩ ተነስቷል።



በአላት

17ኛው የሰንደቅ አላማ ቀን



ሰመራ ዩኒቨርሲቲ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለ17ኛ ጊዜ እየተከበረ ያለውን የሰንደቅ አላማ ቀን ከሰሜን ምስራቅ እዝ የመከላከያ ሰራዊት አባላት ጋር በተለያዩ መርሃ-ግብሮች በዱብቲ አክብሯል::

በዚህም የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ዶ/ር መሀመድ ኡስማንንን ጨምሮ አመራሮች:በርካታ ተማሪዎች:የግቢ ፌደራል ፖሊስ አባላት በመገኘት ሰራዊቱን አግዘዋል::

ክብረ-በዓሉ ሁለት አላማዎችን ያነገበ ሲሆን የሰንደቅ አላማ ቀንን አሰመልክቶ የሀገር ፍቅር:አብሮነት እና ማንነት የሚዘከርበት እንዲሁም ሰራዊቱን በግብርና ሰራው ላይ ማሳው ድረስ በመሄድ ማገዝ እና ማበረታታት ነው::



በአላት

19ኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦችቀን



19ኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች "ህገራዊ መግባባት ለህብረ ብሔራዊ አንድነት" በሚል መሪ ሀሳብ በዓል

በዓሉ በልዩነት ውስጥ ያለው አንድነት የጥንካሬያችን መገለጫ መሆኑን የሚያሳይ ነው::

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ በሰላም አምባሳደርነቱ የሚታወቅ መሆኑን ገልጸው በዓሉ በዩኒቨርሲቲው ያለውን አብሮነት፣ መከባበርና አንድነት ለማሰቀጠል ያግዛል ብለዋል።

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ የአስተዳደር ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት ሁሴን ኡመር(ዶ/ር) እንዳሉት በዓሉን በጋራ ማክበር የባህል፣ ወግና ብዝሃ ውበቶች ጎልተው እንዲወጡ ዕድል የፈጠረ ነው ብለዋል።

በአሉ መከበሩ በመካከላቸው አብሮነትና መቻቻል እንዲጎለብት እንደሚያደርግ ከተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች በሰመራ ዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ተማሪዎች በዓሉ አብሮነትና መቻቻልን የሚያጠናክር ነው ብለዋል።



ዩኒቨርሲቲ መድረኮች የPLRA ባለ ብዙ ባለድርሻ አካላት ማስተባበሪያ ሰብሰባ



አጋርነት ለቆላማ አካባቢዎች የመቋቋም እንቅስቃሴ (PLRA) የባለብዙ ባለድርሻ አካላት ማስተባበሪያ መድረክ ሰብሰባ ተካሄደ::

የPLRA ተነሳሽነት በበርካታ ደረጃዎች ውስጥ ባሉ ተቋቋሚ ባለድርሻ አካላት መካከል ያለውን ቅንጅት እና ግንኙነት ለማጎልበት፣ የጣልቃ ገብነትን ውህደት ለማሻሻል እና የጥረቶችን ድግግሞሽ ለመቀነስ ያለመ ነው።



ዩኒቨርሲቲ መድረኮች

የሰልጠና ኮርሶች ሂደት እና UDACITY ሥልጠና



የሰመራ ዩኒቨርሲቲ የUdacity 5 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ኮዴርስ ኢኒሼቲሸን ከመጀመሩ ጎን ለጎን የተማሪዎች ስኬት ሰዊት እና የማሰተር ክላሰ፡ ፋውንዴሽን በልህቀት ፎር ቲቺንግ ኦንላይን ኮርሶች ላይ ጥልቅ ግምገማ አድርጓል።

ዩኒቨርሲቲው በe-Learning for Strengthing Higher Education (e-SHE) ተነሳሽነት፣የማሰተር ክፍል ማሰልጠኛ (MCT) ኮርሶችን ለአሰተማሪዎች እና የተማሪ ስኬት ሰዊት (ኤሰኤሰኤሰ) ኮርሶችን ለተማሪዎች በመሰጠት ነው።

ኤሰኤሰኤሰ የተነደፈው ተማሪዎችን ለመደገፍ ሲሆን ኤምሲቲ ግን የመምህራንን ክህሎት ማሳደግ ላይ ያተኩራል፣ ሁለቱም ቡድኖች ከትምህርታዊ አቅርቦቶች ተጠቃሚ መሆናቸውን ያረጋግጣል።



ዩኒቨርሲቲ መድረኮች 4ኛው የሰብአዊ መብት ፊልም ፌስቲቫል በሰመራ ዩኒቨርሲቲ



የሰመራ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን፣ በኢሰመጉ አፋር ክልል ጽ/ቤት እና የህግና አስተዳደር ትምህርት ቤት አዘጋጅነት 4ኛውን የሰብአዊ መብት ፊልም ፌስቲቫል አዘጋጅቷል።

በፌስቲቫሉ በኢትዮጵያ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መብቶችን እና የሴቶችን ህይወት የሚዳስስ “ተመለስ” የተሰኘ አሳማኝ የቲያትር ፊልም ቀርቧል። ፊልሙ ሴቶች ያጋጠሟቸውን የመብት ጥሰቶች ግንዛቤ ለማሰጨበጥ እና በፍትህ አስፈላጊነት ላይ ውይይት ለማድረግ ያለመ ነው።

ሁሉም በአንድነት ለሰብአዊ መብትና ለማህበራዊ ፍትህ ለመቆም ያላቸውን ቁርጠኝነት አሳይቷል።



ዩኒቨርሲቲ መድረኮች በቁልፍ አፈጻጸም አመልካቾች (KPIs) አተገባበር ላይ ውይይት



የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ አመራሮች የመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን አፈጻጸም ለማሳደግ በትምህርት ሚኒስቴር ያወጣውን መመሪያ መሰረት በማድረግ የቁልፍ አፈጻጸም አመልካቾችን አተገባበር ላይ ውይይት ተደርጓል።

ውይይቱ KPIs በዩኒቨርሲቲው ውስጥ እና በባለድርሻ አካላት መካከል የተጠያቂነት፣ የጥራት እና የህብረተሰብ ተፅእኖን ለማሻሻል ያለውን ጠቀሜታ አመልክቷል።

KPIs በተቋሙ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም የሥራ አስፈፃሚዎችን ያጠቃልላል, ከሁለቱም ተቋማዊ እና አገራዊ ግቦች ጋር እንዲጣጣም ተደርጎ ፈጠራን ማበረታታት ፡-በምርምር ጥራት እና በማህበረሰብ ተሳትፎ ላይ የሚያተኩሩ KPIs ጉልህ የሆኑ የህብረተሰብ ተግዳሮቶችን የሚፈቱ ተነሳሽነቶችን ቅድሚያ ሰጥቶ ይሰራል ።

ሌላው ተማሪዎችን ያማከለ ትኩረት በማድረግ የተማሪን እርካታ እና የሰራ እድልን የሚለኩ KPIs ዩኒቨርሲቲዎች ለዋና ባለድርሻዎቻቸው - ተማሪዎች ፍላጎቶች ቅድሚያ እንዲሰጡ ያስችላል።



Samara University
2024/25
Annual Magazine
Third Edition ሦስተኛ ዕትም
የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

ዩኒቨርሲቲ መድረኮች

ቁልፍ የአፈጻጸም አመላካቾችን ተግባራት



የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር መሀመድ ኡስማን ከሁሉም ምክትል ፕሬዝዳንቶች ጋር በቁልፍ የአፈጻጸም አመላካቾች(Key Performance Indicators) ላይ የኮንትራት ሰምምነት ተፈራርመዋል::

ፕሬዚዳንቱ በፊርማ ሰነሰርዓቱ ላይ ለካውንሰል አባላት እንደገለፁት ቁልፍ የአፈጻጸም አመላካቾች ሳይንሳዊና ዓለም አቀፋዊ መለኪያዎች በመሆናቸው በትክክል በመፈጸም: አጠቃላይ እድገትን የሚያፋጥኑ የለውጥ ሰራዎች ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲፈፀሙ የሚያስችል ነው ብለዋል።

በመጪዎቹ ቀናት ሁሉም ምክትል ፕሬዚዳንቶች ተመሳሳይ የኮንትራክት ሰምምነቶችን ከመካከለኛው አመራር ክፍል ማለትም ከኮሌጅ እና ከትምህርት ቤት ዲኖች፣ ከዳይሬክተሮች፣ ከሰራ አስፈፃሚዎች፣ ከት/ርት ክፍል ኃላፊዎችና አስተባባሪዎች ጋር ለመፈራረም እንደታቀደ ተገልጿል።



ዩኒቨርሲቲ መድረኮች ዓመታዊ የቴክኖሎጂ ሽግግር ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ግምገማ አውደ ጥናት



የሰመራ ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ሽግግር ፕሮጀክት ፕሮፖዛልን ለመገምገም አመታዊ አውደ ጥናት በማካሄድ በህብረተሰቡ ላይ የሚኖራቸውን ተፅዕኖ እና አዋጭነታቸውን የሚያጎሉ ሰድሰት ጥናቶችን ገምግሟል።

የቀረቡት ሀሳቦች በማህበረሰቡ አባላት ህይወት ላይ ትርጉም ያለው ለውጥ ለማምጣት የተነደፉ ተግባራዊ መፍትሄዎችን ለማቅረብ ያለመ ነው።

የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ም/ፕሬዝዳንት አቶ አደም አሊ እንደገለፁት የእነዚህ ጅምሮች የመጨረሻ ግብ በመድገም በህብረተሰቡ ውሰጥ እንዲሰራጭ በማድረግ ኑሮን ማሻሻል ነው።



ዩኒቨርሲቲ መድረኮች

ተማሪዎች የስፖርት ፌስቲቫል



የስመራ ዩኒቨርሲቲ የስፖርት ልዑካን ቡድን በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ አስተናጋጅነት ከጥር 17-27 /2017 ዓ.ም በሚካሄደው የ2017 ዓ.ም የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የስፖርት ፌስቲቫል ላይ በ3 የስፖርት አይነቶች፣ የወንዶች አትሌቲክስ በሁሉም አይነት፣ ቴኳንዶ በሴት እና ወንድ እንዲሁም በእግር ኳስ ተወዳድርዋል።

ለስባት አመታት ተቋርጦ የነበረው የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የስፖርት ፌስቲቫል የትምህርት ሚኒስትሩ ብርሀኑ ነጋ(ፕ/ር) በተገኙበት በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ተካሂዷል።

በአምስት የስፖርት አይነት ከ 49 የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የተወጣጡ ተማሪዎች የሚሳተፉበት ይህ ውድድር በደማቅ ባህላዊ ትርዒት ታጅቦ ተካሂዷል።







የዩኒቨርሲቲ መድረኮች ለህግ እናአስተዳደር ት/ት ቤት ተማሪዎች በተጋባዥ እንግዳ ልምድ

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎቹን እና የሰራተኞቹን አካዳሚያዊ ልምድ ለማበልጸግ የታለሙ ሁለት ልዩ የእንግዳ በመጋበዝ ልምዶቻቸውን እንዲሰጡ አድርጓል።



የህግ እና አስተዳደር ትምህርት ቤት ተማሪዎችን እና ሰራተኞችን በማደራጀት ልምድን ለማሳደግ እና ስለሰደት ህግ እና በማህበረሰቦች ላይ ስላለው ተጽእኖ ግንዛቤዎችን ለሚሹ የህግ ባለሙያዎች ለማካፈል ነው። ይህም ለመምህራን እና ተማሪዎች የተሻለ ግንዛቤ ይዘው እንደሄዱ ያሰቻለ መርህግብር ነበር።



ዩኒቨርሲቲ መድረኮች በተጋባዥ እንግዳ አካዳሚክ ልምድ ተሰጥቷል



ለቱሪዝም እና እንግዳ ተቀባይ አስተዳደር ትምህርት ቤት ተማሪዎች እና ሰራተኞች በተጋባዥ እንግዳ አካዳሚክ ልምድ ተሰጥቷል።

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎቹን እና የሰራተኞቹን አካዳሚያዊ ልምድ ለማበልጸግ የታለመ ልዩ ተጋባዥ እንግዳ በማምጣት ትምህርት ሰጠ።

ይህ መርህግብር የቱሪዝም እና የእንግዳ ተቀባይነት ማኔጅመንት ትምህርት ቤት ተማሪዎችን እና ሰራተኞችን ያተኮረ ሲሆን አለም አቀፋዊ የቱሪዝም ደረጃዎችን ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በማቀናጀት ዘላቂ ልማትን ለማስፋፋት ያተኮረ ነበር።

በሆንግ ኮንግ ፖሊ ቴክኒክ ዩኒቨርሲቲ የሆቴልና ቱሪዝም አስተዳደር ትምህርት ቤት መምህር እና ተመራማሪ በሆኑት በዶ/ር ጄሰን ኬሊ “የቱሪዝም መዳረሻ አስተዳደር ለዘላቂ ልማት፡ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን ማመጣጠን እና የአካባቢ ማህበረሰብን መሰረት ያደረገ ቱሪዝም” በሚል ርዕሰ ተዘጋጅቷል።



ዩኒቨርሲቲ መድረኮች

የኢንተርፕረነርሺያል አስተሳሰብን እና ኢ-ኮሜርስ



በሰመራ ዩኒቨርሲቲ ከተለያዩ የትምህርት ዘርፎች ለተውጣጡ ተማሪዎች የሰራ ፈጠራ አስተሳሰብ እና ዲጂታል ኢኮኖሚን ለማሳደግ ያለመ አውደ ጥናት ተካሂዷል።

ዩኒቨርሲቲው በተማሪዎች መካከል የኢንተርፕረነርሺያል አስተሳሰብን እና ኢ-ኮሜርስን ለማሳደግ ያለመ ወርክሾፕ አካሂዷል።

ከቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ አይስአዲስ እና ማስተርካርድ ፋውንዴሽን ጋር በመተባበር የተካሄደ ሲሆን ይህ ዝግጅት የወጣቶችን ሰራ ፈጣሪዎች ለማብቃት የተነደፈው የ"ቬንቸር ሜዳ ፕሮጀክት" አካል መሆኑ ተመላክቷል።

በዩኒቨርሲቲው የኢንዱስትሪ ትስስርና የቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክቶሬት አስተባባሪነት በአውደ ጥናቱ ሀሳባቸውን ያጋሩት ወጣት ኢንጂነር ዳውድ አሊ የኮንስትራክሽን ንግድ ሥራ ፈጣሪ ባለሙያ ሰለቢዝነስ ጉዟቸው ተግባራዊ ተሞክሮዎችን ለተሳታፊ ወጣቶች አካፍሏል።



ዩኒቨርሲቲ መድረኮች ብሔራዊ ጥቅሞቻችንና ቀጠናዊ ትስስር የምክክር መድረክ



መርሀግበሩ በሰመራ ዩኒቨርሲቲ እና ሰላም ሚኒስቴር ትብብር የተዘጋጀ ሀገራዊ የምክክር መድረክ ተካሄዷል::

የውይይት መነሻ ጥናታዊፅሑፍ በመምህር ሀይሌ ረዳቀርቦ በሰነዱ ላይ ጥያቄዎች፣ አስተያየቶች እና ውይይት ተደርገዋል::

እንደ አገር እና ዜጋ የጋራ የሆኑ ህልሞች፣ መገለጫዎች፣ ሰጋቶች፣ ጥቅሞችና እሴቶች ያሉን ህዝቦች በመሆናችን የጋራ አረዳድን በማዳበር ብሔራዊ ጥቅሞቻችንን በእያንዳንዱ ዜጋ ውስጥ ማስረፅ እንደሚገባ ተመላክትዋል።

የተከበሩ አቶ ገዛህኝ ጥላሁን ፣ በሰላም ሚኒስቴር የብሄራዊ መግባባት ዴስክ ሀላፊ በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች እየተካሄዱ ያሉ መሰል ውይይቶች ለእርስበርስ እና ቀጠናዊ መግባባት ብሎም ለጋራ ጥቅሞቻችን መከበር ወሳኝ ሚና ይኖራቸዋል ብለዋል::



ዩኒቨርሲቲ መድረኮች

የመምህራን ማህበር አዲስ የሰራ-አስፈጻሚዎች ምርጫ



በዩኒቨርሲቲው የመምህራን ማህበር ጉባኤ እና አዲስ የሰራ-አስፈጻሚዎች ምርጫ ተካሄዷል::

በሰመራ ዩኒቨርሲቲ የመምህራን ማህበር ጉባኤ እና አዲስ የሰራ አስፈጻሚዎች ምርጫ ተካሄዷል::

በጉባኤ ላይ ዶ/ር ዩሀንስ በንቲ የኢትዮጲያ መምህራን ማህበር ፕሬዚዳንት : ዶ/ር ፈቃዱ ዘለቀ የዩኒቨርሲቲ መምህራን ማህበር ፕሬዚዳንት: ዶ/ር መሀመድ ኡሰማን የሠመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዝዳንቶች: የኮሌጅና የት/ት ቤት ዲኖች:የት/ት ክፍል ሀላፊዎች እና የማህበሩ አባላት ተገኝተዋል::

በደሞክራሲያዊ የምርጫ ሂደት የአብላጫ ድምፅ በማግኘት ተመርጠው ቃለመሃላ ፈፅመዋል::

ይህ አዲስ አደረጃጀት በአጠቃላይ የተቋሙ መምህራንን መብት ማሰከበር እና በተቋሙ ውስጥ በመማር ማስተማር ፣ በአስተዳደር ፣ በአቅም ማጎልበት ፣ በትምህርት ጥራት እና ሥነ ምግባር ጉዳዮችን በተደራጀ መልኩ ለመቅረጽ እና ለማንቀሳቀስ የሚያስችል አስተዳደራዊ ለውጥ እንደሚያምጣ አመራሮች እና አባላቱ አስተያየት ሰጥተዋል።

ተጋባዥ የመምህራን ማህበር ፕሬዝዳንቶቹ ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ለመምህራን ቤት መሰሪያ ከሰመራ ሎጊያ ከተማ አስተዳደር እና ከክልል አስተዳደር ተረክቦ ያጠረውን 200ሺ ካ.ሜ ቦታ ጎብኝተዋል።



ዩኒቨርሲቲ መድረኮች ሀገር አቀፍ የሰነ-ምግባር አምባሳደርነት ውድድር

በሠመራ ዩኒቨርሲቲ ለሀገር አቀፍ የተማሪዎች የሰነ-ምግባር አምባሳደርነት ውድድር የሚሳተፉ ተማሪዎችን ለመምረጥ የሚያስችል የማጣሪያ የጥያቄ እና መልስ ውድድር ተካሂዷል::



በማጣሪያው ሰድስት ተማሪዎች የተወዳደሩበት ሲሆን አንድ ተማሪ በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚካሄደው ውድድር ላይ ሰመራ ዩኒቨርሲቲን ወክሎ ከመላው የዩኒቨርሲቲዎች የሚመጡ ተማሪዎች ጋር እንደሚወዳደር ሰራ-አፈፃሚው አመላቷል::

የተማሪዎች የሰነ-ምግባር አምባሳደርነት ውድድሩን በበላይነት የፌደራል የሰነ-ምግባር እና የፀረ-ሙሰና ኮሚሽን የሚመራው ሲሆን በሠመራ ዩኒቨርሲቲ በኩል የሰነ-ምግባር መከታተያ ሰራ-አስፈፃሚ አስተባብሮታል::



ዩኒቨርሲቲ መድረኮች በተማሪዎች መረጃ አስተዳደር ሰርዓት (SIMS) ሰልጠና



የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ሬጅስትራር ጽ/ቤት የመማር ማስተማር አገልግሎቱን ተአማኒነትና ቀልጣፋነት ለማረጋገጥ ያለመ በተማሪዎች መረጃ አስተዳደር ሰርዓት Student Information Management System(SIMS) ሰልጠና ሰጥቷል::

ሰልጠናው በትምህርቱ ዘርፍ በየደረጃው ያሉ ሁሉም አመራሮች የተማሪዎችን ውጤት/መረጃ በSIMS መተግበሪያ አማካኝነት በሀላፊነት : በእውቀት እና በተመደበለት ጊዜ መመዝገብ:መቀበል:መላክ: ማጽደቅ እና ማስተዳደር እንዲችሉ የሚያግዝ መሆኑ ተገልጿል::

ዩኒቨርሲቲው ከ2008 ጀምሮ ላለፉት 10 አመታት በ SIMS መተግበሪያ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ ሲሆን : የአሁኑ ሰልጠና አድስ ለተመደቡና ነባር የኮሌጅና የትምህርት ቤት ዲኖች: ም/ዲኖች: የትምህርት ክፍል ሀላፊዎች: አስተባባሪዎች እና መምህራኖች የተሰጠ ነው::

ዩኒቨርሲቲ መድረኮች

114ኛው አለም አቀፉ የሴቶች ቀን በተለያዩ ሁነቶች

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ አለም አቀፍ የሴቶች ቀንን ”ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ሁሉን አቀፍ ለውጥ በሴቶች ተሳትፎ ይረጋገጣል” በሚል መሪ ሀሳብ በተለያዩ ሁነቶች አክብሯል።

በሀገራችን ለ49ኛ ጊዜ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ114ኛ ጊዜ እየተከበረ የሚገኘው ይህ የአለም አቀፍ የሴቶች ቀን ሁሉም ለፍትህ የሚታገሉበት እና ለቀጣይ የለውጥ ሰራ የሚንቀሳቀሱበት የድርጊት ጥሪ ነው።

በአከባበሩ ላይ የዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ አመራሮች፣ የሴት መምህራንና ሰራተኞች አመራሮች እና አባላት፣ ሴት የተማሪዎች ህብረት አባላት እና ሌሎች እንግዶች ተገኝተዋል።





የሴቶች ቀን በአመት አንድ ጊዜ ብቻ ታስቦ የሚውል በአል ሳይሆን፤ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ሁሉን አቀፍ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ተሳታፊነት እና ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ መሆን እንዳለበት የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚደንት ዶ/ር መሀመድ ኡስማን ተናግረዋል::



ዩኒቨርሲቲ መድረኮች አመታዊን "ተቋሙን ከመካከለኛው መምራት" የሚል ፕሮግራም



ዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ አመራሮች ተቋሙን ከመካከለኛው ሆኖ መምራትአርያነት ያለው ተግባር መሆኑ ተገለጸ።

የፕሬዝዳንት የድጋፍ እና ክትትል ቡድን ፕሮግራሙ ወደ ሌሎች ኮሌጆች እንደሚዘልቅ አረጋግጧል።, ይህም የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ለቀጣይ መሻሻል እና የትምህርት ጥራት ያለውን ቁርጠኝነት የሚያጠናክር ሥራ መሆኑን አመላክቷል.

መርሃ ግብሩ ሁለት ዋና ዋና አላማዎች አሉት፡ እንደኛው፡ የኮሌጆችን እና ትምህርት ቤቶችን ወቅታዊ ሁኔታ በቢሮ ምልከታ ማድረግ ፣ በክፍል ፍተሻ እና ከመምህራንና ተማሪዎች ጋር በመተባበር የእለቱን ተግዳሮቶች ለመፍታት እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ለማሰተካከል ትኩረት ያደረገ ነው።

ሁለተኛው፡- ቁልፍ የሰራ አፈጻጸም አመልካቾች (KPIs)፣ የሰርአተ ትምህርት ጥራት እና የመውጫ ፈተና ዝግጅት ላይ በማተኮር የአካዳሚክ አፈጻጸም ሰልታዊ ግምገማ ለማካሄድ ያለመ ነው።



ዩኒቨርሲቲ መድረኮች

በፊልም ፣ ድራማ እና ቲያትር ፕሮዳክሽን ላይ ለተሰማሩ የአካባቢው ወጣቶች የአቅም ግንባታ ሰልጠና

የ'እምቢዳ' እና 'ማላሳይ' ፊልም፣ ድራማ እና ቲያትር ፕሮዳክሽን ማህበራት ወጣቶች የአቅም ግንባታ ሰልጠና በተሳካ ሁኔታ ሰጥቷል።

ሰልጣኞቹ በመርሃግብሩ ማጠቃለያ ወቅት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን የሚዳስሱ በማህበረሰብ ግንዛቤ ላይ ያተኮሩ ሶስት የመድረክ ተውኔቶችን በማዘጋጀት ክህሎታቸውን አሳይተዋል።

ሰልጠናው የተለያዩ የፊልም እና የቲያትር ፕሮዳክሽን ዋና ዋና ጉዳዮችን ያካተተ ሲሆን ከነዚህም መካከል የድርሰት አፃፃፍ ፣ የገፀ ባህሪ አመራረጥ፣ የመድረክ ዝግጅት፣ የካሜራ አጠቃቀም፣ የፎቶ እና የቪዲዮ ቀረጻ፣ በኮምፒውተር መተግበሪያ የድምፅ እና የምስል ቅንብር፣ ጥልቅ ንባብ፣ የማህበራዊ ሚዲያ ይዘት ፈጠራ እንዲሁም በፕሮዳክሽን እና ሰርጭት ሰነምግባር ላይ ያተኮረ ነበር::







ዩኒቨርሲቲ መድረኮች ተከሰቶ ለነበረው የፍየል ወረርሽኝ የተሰጠ ምላሽ



ሰመራ ዩኒቨርሲቲ: የዱብቲ ወረዳ ማህበረሰብ በፍየሎች ላይ ሰሞኑን ለተከሰተው ወረርሽኝ አስቸኳይ የተንቀሳቃሽ ህክምና አገልግሎት መሰጠቱ ተገልጿል::

የእንሰሳት ህክምና ባለሙያዎቹ ዩኒቨርሲቲው ጉዳዩን በቅርበት እየተከታተለ እንደሆነ ገልፀው የህመም ምልክት ሲያዩ የታመሙትን ከጤናማዎቹ ለይቶ ማቆየት: በተናጥል መመገብ እና በቂ የውሃ መሰጠት ፤ አዲስ የሚገቡ ፍየሎችን ከመንጋው ጋር ሳይቀላቀሉ ለሁለት ሳምንታት ለይቶ መከታተል ፤ እንሰሳቱ የተለመዱ በሽታዎችን መከላከያ ክትባቶችን መውሰዳቸውን ማረጋገጥ፤የበሽታ ስርጭትን ለመቀነስ መጠለያዎችን እና የምግብ እና የውሀ ቦታዎችን አዘውትሮ ማጽዳት፣ ንፅህናውን መከታተል የተለዩ ክስተቶችን ሲያዩ በአፋጣኝ ለእንሰሳት ህክምና ማእከል/ ባለሙያ ሪፖርት ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ አሰገንዝበዋል::

ዩኒቨርሲቲው ጥያቄውን ተቀብሎ የህኪሞች ቡድን በመላክ በጥናት ላይ የተመሰረተ ህክምና በሽዎች ለሚቆጠሩ ፍየሎች እና በጎች በዋድ ባዱራ፤ ቀበሌ 03 እና ሂናሌ ቀበሌዎች ፈጣን ምላሽ ሰጥቷል።



ዩኒቨርሲቲ መድረኮች

የትምህርት ሚኒስቴር ሱፐርቪዥን ቡድን የምልከታ መርሃግብር



በሰመራ ዩኒቨርሲቲየትምህርት ሚኒስቴር ሱፐርቪዥን ቡድንለሁለት ቀናት ያደረገውን የውይይትእና የምልከታ መርሃግብር ተካሂዷል::

በሰመራ ዩኒቨርሲቲየትምህርት ሚኒስቴር ሱፐርቪዥን ቡድን ከተማሪዎች ፣ ከመምህራን፣ከአስተዳደር ሰራተኞች እና ከመካከለኛአመራሮች ጋር በተናጠል ባደረጉትውይይት የወሰዷቸውን ነጥቦች እንዲሁም ከተለያዩ የመስረተ ልማቶች እናየሰራ ክፍሎች የመስክ ምልከታየያዟቸውን ነጥቦች አንድ ላይአጠቃለው ከከፍተኛ አመራሩ ጋርተወያይተዋል።

ልኡኩ በቆይታው በጥንካሬየወሰዳቸውን አፈፃፀሞች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ: ማስተካከያ የሚፈልጉ ብሎ የለያቸውንናበዩኒቨርሲቲው ደረጃ መፈታት የሚችሉትንበትኩረት እንዲሰራባቸው: የትምህርት ሚኒስቴርንድጋፍ የሚሹ ጉዳዮችን ለሚኒስቴርመሰሪያቤቱ እንደሚያቀርቡ አመልክተዋል::

በተለይም የመንግሰትን ልዩትኩረትና ድጋፍ የሚፈልጉ የአካባቢውየሙቀት ሁኔታ ያገናዘበ የበጀትድልድል እና የመብራት የሀይልአቅርቦት: የሀገር አቀፍ ፈተናዎችመርሃግብር እና ሌሎችንም ጥያቄዎችለበላይ አካል እንደሚያቀርቡ ገልጸዋል::
ዩኒቨርሲቲው ከተፈጥሮ ጋርእየታገለም ቢሆን አመራሩ በየደረጃውእና ሰራተኛው በመናበብ የሰሯቸውበርካታ ለሌሎችም ተሞክሮ የሚሆኑአሰራሮችን እና ተቋማዊ ባህሎችንእንደተገነዘቡ ገልጸዋል:



ዩኒቨርሲቲ መድረኮች ኢትዮ ቴሌኮም ለተማሪዎች ድጋፍ እያደረገ አድርጓል።



ኢትዮ ቴሌኮም በሠመራ ዩኒቨርሲቲ ለሚማሩ ልዩ ድጋፍ ለሚሹ መደበኛ ተማሪዎች የገንዘብ ድጋፍ እያደረገ እንደሚገኝ ትናንት ባዘጋጀው መድረክ ላይ ገልጿል::

ድርጅቱ በአሁኑ ሰአት 80 (ወንድ እና ሴት) ተማሪዎችን በመደገፍ በትምህርታቸው የያዙትን አላማና ፍላጎታቸውን እንዲያሳኩ የሚያግዝ የገንዘብ ድጋፍ እያደረገ እንደሆነ ገልጾ: በቀጣይ በቁሳቁስም ድጋፉን አጠናክሮ የመቀጠል እቅድ እንዳለው አስታውቋል ።

በመድረኩ ተማሪዎች የኢትዮ ቴሌኮምን አገልግሎቶች በብቃት ለመጠቀም በሚያስችሉ ክህሎቶች ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ሰጥቷል:: ይህም ለተማሪዎች አስፈላጊ ግብአቶችን ከማሟላት ባለፈ የኢትዮ ቴሌኮም አምባሳደር እንዲሆኑ የሚያነሳሳ የሚሰጣቸውን ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶች የማስተዋወቅ ሰራ ስርቷል።

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ: ኢትዮ ቴሌኮም ለተማሪዎች እያደረገው ላለው ድጋፍ ምስጋናውን እየገለፀ: ይህን ትብብር ወደ ላቀ ደረጃ በማድረስ ተማሪዎችን እና ማህበረሰቡን የሚጠቅም ምቹ የመማር ማስተማር ሁኔታን መፍጠር እንደሚቻል ያምናል። ኢትዮ ቴሌኮም ከሰመራ ዩኒቨርሲቲ ጋር ለአመታት በአጋርነት እየሰራ ያለ ድርጅት መሆኑም ተመላክቷል::



ዩኒቨርሲቲ መድረኮች

ዩኒቨርሲቲው የሰነ_ፅሁፍ_ምሽቱ_ተካሄደ

የሠመራ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ያዘጋጁት ታላቅ የሰነ-ፅሁፍ ምሽት ተካሄደ::



ከሰነ-ፅሁፍ ሰራዎች በተጨማሪ: በሀገር አቀፉ የመላው የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሰፖርት ፌስቲቫል ላይ ለተሳተፉ የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ሰፖርት ልኡክ በመንግሰት ዩኒቨርሲቲዎች ሰፖርት ማህበር እና በአዘጋጁ የአድስ አበባ ሳይንሰና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የተዘጋጀ የምሰክር ወረቀት ተበርክቷል::

በተለያዩ ጊዜያት በተማሪዎች አቀባበል ላይ ተሳትፎ ላደረጉ አካላትም እውቅና ተሰጥቷል::በመጨረሻም የእለቱን የሰነ-ፅሁፍ ምሽት ላዘጋጁት:ላስተባበሩት እና በትወና ላደመቁት ተማሪዎች ምሰጋናና እውቅና ተሰጥቷል::

በዚህ የጥበብ አፍቃሪያን መምህራን:ሠራተኞች እና ተማሪዎች የታደሙበት መድረክ ላይ ቲያትር ግጥም: ሞኖሎግ: ሙዚቃ:ዳንሰ እና የጭውውት ትዕይንቶች ቀርበውበታል:: ተማሪዎቹ በሰነ-ፅሁፍ እያዝናኑ ቁም ነገር የሚያሰጨብጡ ሀሳቦችን በማንሳት መድረኩን ከማድመቅም ባለፈ የመማር ማስተማሩን እና የተማሪዎችን የግቢ ቆይታ አይረሴ የሚያደርጉ የጥበብ ሰራዎችን በማቅረብ ቀልብ መግዛት መቻላቸውን የታዳሚው ቁጥር ምሰክር ነው::



ዩኒቨርሲቲ መድረኮች

ተማሪዎቹ "የምሰለ-ችሎት ዉድድር"



በሰመራ ዩኒቨርሲቲ ህግ እና አስተዳደር ትምህርት ቤት: የህግ ተማሪዎች "የምሰለ-ፍርድ ቤት ዉድድር" በርካታ ታዳሚዎች በተገኙበት አካሒደዋል።

የምሰለ-ችሎት ውድድር በዩኒቨርሲቲዎች ደረጃ እንዲሁም በሀገር አቀፍ እና አለም አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጅ ሲሆን:ተማሪዎች በፅንሰ ሀሳብ የተማሩትን በተግባር የሚለማመዱበት መድረክ በመሆኑ ፋይዳው የጎላ መሆኑን ውድድሩን የዳኙት መምህራን ተናግረዋል::

ተወዳዳሪ ተማሪዎቹ ዩኒቨርሲቲያቸውን ወክለው በቅርቡ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚደረገው የህግ ተማሪዎች ምሰለ-ችሎት ውድድር ሰለሚሳተፉ: የዛሬው ምሰለ ችሎት ለቅድመ ዝግጅት ይረዳቸው ዘንድ የተዘጋጀ መሆኑን ትምህርት ቤቱ ገልጿል።



ዩኒቨርሲቲ መድረኮች

በሠላም ግንባታና በግጭት አፈታት አውደ ጥናት ተካሄደ



የሰላማዊ መግባባት እና እርቅ ለአርብቶ አደር ኑሮ መጎልበት የሚቆም የጋራ አውደ ጥናት አካሂዷል።

የአፋር አርብቶ አደር ልማት ማህበር (አህዴድ) ከሰመራ ዩንቨርሲቲ ጋር በመተባበር በ"ፐርፕል ፕሮጄክት" -የሰላማዊ መግባባት እና እርቅ ለአርብቶ አደር ኑሮ መጎልበት የሚቆም የጋራ አውደ ጥናት አካሂዷል።

የግንዛቤ ማሰጨበጫ ሰራው አካል ሆኖ በአውደ ጥናቱ በሰላም ግንባታ እና በግጭት አፈታት ዙሪያ ሁለት ጥናቶች ግንዛቤ ያላቸው ገለጻዎች ቀርበዋል። በተጨማሪም የዩኒቨርሲቲው 'ድንቅ ክለብ' የእውነተኛ ህይወት ግጭቶችን እና እርቅን የሚያንፀባርቅ ድራማ አቅርቧል።

በዝግጅቱ የአፋር አርብቶ አደር ልማት ድርጅት(APDA) ለ35 የዩኒቨርሲቲው ‘የሰላም ፎረም’ ተማሪዎች የሁለት ቀናት ስልጠና በመሰጠት፣ በተማሪዎች የሚመራ የሰላም እና ለህብረተሰባቸው ትርጉም ያለው አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ የሚያስችል ብቃት በማሳታጠቅ ስልጠና ሰጥቷል።



ዩኒቨርሲቲ መድረኮች

ሀገራዊ የመምህራን የውይይት መድረክ

ሰመራ ዩንቨርሲቲ "ትውልድ በመምህር ይቀረፃል፤ ሀገር በትምህርት ይበለፅጋል" በሚል መሪሃሳብ የተዘጋጀው የመምህራን የውይይትመድረክ ተደርጓል::

ሰነዱ ከቀረበ በኋላ የነበረውን የፓናል ውይይት የሰመራ ዩንቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር መሀመድ ኡሰማን፣ የአፋር ክልል ብልፅግና ፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት የፖሊቲካ ዘርፍ ኃላፊ አቶ መሀመድ አህመድ፣ የሠመራ-ሎጊያ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ እና የሰመራ ዩኒቨርሲቲ የቦርድ አባል አቶ አብዱ ሙሳ በጋራ በመሆን መርተውታል።





መምህራን ለሀገር ግንባታ ያላቸው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ትውልድን በመቅረጽ ረገድ የማይተካ ኃላፊነታቸውን በመወጣት ባለፉት የለውጥ ዓመታት የተመዘገቡ ስኬቶች፣ የገጠሙን ተግዳሮቶች በመገንዘብ እንደ ሀገር ለተጀመረው ሁለንተናዊ የብልጽግና ጉዞ የበኩላቸውን ማድረግ እንደሚያስፈልግ በፖናል ውይይቱ ወቅት ተነስቷል።

መምህራን በቀረበው ጽሁፍ ላይ ላነሷቸው ጥያቄዎች እና አስተያየቶች ከመድረኩ ገለፃ እና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸው ፍፃሜውን አድርጓል።





ዩኒቨርሲቲ መድረኮች

አፋርኛ ቋንቋ ሲማሩ የቆዩ ተማሪዎች ምርቃት

በሰመራ ዩኒቨርሲቲ መሰረታዊ የአፋርኛ ቋንቋ ትምህርት ሲማሩ የነበሩ ተማሪዎች ተመርቀዋል። የተማሪዎች ህብረት መሰረታዊ የአፋርኛ ቋንቋ ትምህርት 1 መቶ ለሚሆኑ ተማሪዎች ለሁለት ወራት ሲሰጥ ቆይቶ አሰመርቋል።

ይህ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ትምህርት አፋርኛን ጨምሮ የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎችን ያካተተ እንደነበረ የተገለፀ ሲሆን፣ በማጠቃለያ ምዘና ደረጃ ውሰጥ ለገቡ ተማሪዎች ፣ እንዲሁም ለአስተማሪዎችና አስተባባሪዎች እውቅና መሰጠቱ ተገልጿል::







ዩኒቨርሲቲ መድረኮች በድረ-ገጽ ትምህርት (E-Learning) ላይ ያተኮረ ውይይት

የሰመራ ክላስተር ዩኒቨርሲቲዎች የመሰመር ላይ ትምህርት (E- Learning) ላይ የምክክር አድርገዋል።

የሰመራ፣ ወሎ፣ ወልድያ እና መቅደላአምባ ዩኒቨርሲቲዎች በጋራ ስትራቴጂዎች የመሰመር ላይ መማሪያ ጥረቶችን ለማጠናከር የምክክር መድረክ በሰመራ ዩኒቨርሲቲ አካሄደዋል።

በመርሃግብሩ የሰመራ ዩኒቨርሲቲ የዲጂታል ይዘት ልማት አሠራሮችን አሳይቷል፣ ይህም የመሰመር ላይ መማሪያ ጥረቶችን በጋራ እንዴት መውሰድ፣ መመዘን እና ማሰቀጠል እንደሚቻል ላይ ውይይት ተደርጓል።





ዩኒቨርሲቲዎቹ በቅንጅት እና በተሟላ የመሰመር ላይ ኮርስ ልማት ላይ በትብብር ለመሰራት እና ግብዓቶችን ለመጋራት ተስማምተዋል።

ሰመራ፣ ወሎ፣ ወልድያ እና መቅደላአምባ ዩኒቨርሲቲዎች በጋራ የሚጠቀሙበት ዲጂታል ስቱዲዮ በማስተርካርድ ፋውንዴሽን፣ ትምህርት ሚኒስቴር እና በአሪዞና ስቴት ዩኒቨርሲቲ ተገንብቶላቸዋል።





ዩኒቨርሲቲ መድረኮች

የኢትዮጵያ መከላከያ ዩኒቨርሲቲ የውይይት ፕሮግራም



የኢትዮጵያ መከላከያ ዩኒቨርሲቲ መከላከያውን ቁልፍ ተልዕኮዎች አሁን ላይዘመኑ በደረሰበት ቴክኖሎጂላይ መድረሱ መከላከያ ዩኒቨርሲቲ ሚናው የጎላ እንደሆነ ተገልጸዋል።

ሻለቃ ዶ/ር በተለይ ተካ በመከላከያ ዩኒቨርሲቲ የህዝብና አለምአቀፍ ግንኙነት ዳይሬክተር ሰለ መከላከያ ዩኒቨርሲቲ ከምሰረታ ጀምሮ አሁን እስካለበት ቁመናአጠቃላይ ማብራሪያ የሰጡሲሆን ሰላሉት የተለያዩ ዕድሎችም ገለፃ አድርገዋል። ዩኒቨርሲቲው ባሉት ፕሮግራሞች ተማሪዎች በምርጫቸው ገብተው መማር እንደሚችሉበት እድልክፍት እንዲደረገ አብራርተዋል።

የኢትዮጵያ መከላከያ ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ አመራሮች የተቋማቸውን የትምህርት፣ የምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮግራሞች በተመለከተ የውይይት መርሃግብር አካሂደዋል::







አውቅና

ዩኒቨርሲቲው በትምህርት ዘርፍ ላደረገው አስተዋፅኦ እውቅና ተሰጥቷል



የአፋር ክልል ትምህርት ቢሮ ለሠመራ ዩኒቨርሲቲ በትምህርቱ ዘርፍ ላበረከተው አስተዋጽኦ ልዩ የእውቅና ዋንጫ ተሸልሟል።

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ከክ
በመተባበር የአፋር ታለንት
የተማሪዎች አገልግሎት እ
ዩኒቨርሲቲው በመቶዎች
ተማሪዎች ለአራት ወራት
ግብር አመቻችቶ ድጋፍና
ሽልማቱ የተሰጠው በሰመ
የትምህርት ኮንፈረንስ ላይ



ድጋፍ ለአፋር ታለንት አካደሚ 10 ኮምፒዩተሮችን ድጋፍ አደርጓል::



የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ፋይናንስ ቢሮ ለአፋር ታለንት አካደሚ ተማሪዎች መገልገያ ኮምፒውተሮችን ተማሪ መሀመድ አካድር የላፕቶፕ ኮምፒውተር አበርክቷል።

አፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ፋይናንስ ቢሮ ድጋፉ የመጀመሪያ እንደሆነ እና በቀጣይም አካዳሚውን እንደሚደግፍና በተለይም በትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤት ለሚያስመዘግቡ ተማሪዎች ልዩ ሽልማት ቢሮው እንደሚያበረክት ተመላክቷል::

አቶ አህመድ በመጨረሻም የሰመራ ዩኒቨርሲቲ አመራሮችን:የክልል ትምህርት ቢሮ ሀላፊዎችን እና የአካደሚውን ኮሚቴ እና ሰራተኞች: ብቁ እና ተወዳዳሪ የሆኑ ተማሪዎችን በመቀበል የትምህርት ዘርፉን ከታች ለመደገፍ እና በእውቀትና በሰነምግባር የታነፀ ተተኪ ትውልድ ለማፍራት እየሰሩት ያለውን ሰራ አድንቀው አመሰግነዋል::

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ አመራሮች:የክልሉ ት/ት ቢሮ ሀላፊዎች እና የአካደሚው የቴክኒክ ኮሚቴ አስተዳደር እንዲሁም ተማሪዎች የፋይናንስ ቢሮ ላደረገው ድጋፍ እና ማበረታቻ አመሰግነዋል::



ድጋፍ

የመሬት መንቀጥቀጥ በአዋሽ ፈንታሌ እና አካባቢው ከፍተኛ ሰጋትን



በአዋሽ ፈንታሌ እና አካባቢው የተከሰተው የመሬት መንቀጥቀጥ በሬክተር ስኬል 4 ነጥብ 9 የተመዘገበበት እስከ አዲሰ አበባ ድረሰ ንዝረቱ መሰማቱን ኢዜአ በዘገባው አሰነብቧል::

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ የጂኦሎጂ ጥናት ቡድን በአዋሽ ፏንታሌ ወረዳ ባደረገው የመሰክ ምልከታ የመሬት መንቀጥቀጡ የተከሰተበትን በተለይም ሳቡሬ ቀበሌ ተገኝቶ መረጃ የመሰብሰብ እና ለማህበረሰቡ ጥንቃቄ የግንዛቤ ማሰጨበጥ ሰራ ተሰርቷል።

የአሜሪካው ጂዮሎጂካል ሰርቬይ: የጀርመን እና ሌሎች አለም አቀፍ ጂዮሎጂካል ሰርቬይ የምርምር ተቋማት በአዋሽ ዙሪያ በተከታታይ የተከሰተውን የመሬት መንቀጥቀጥ የትናንቱን ጨምሮ በድረ-ገጻቸው ላይ አሰፍረውታል።



ድጋፍ

የራያ ዩኒቨርሲቲ ከቀያቸው ለተፈናቀሉ የአዋሽ ፈንታሌ እና ዱለቻ ወረዳ ድጋፍ



የግብአት አቅርቦቱ ለወገን የእለት ጉርሰ ከማድረስ ባለፈ የማህበረሰብ ትብብርን እና አብሮነትን በተግባር ለመግለፅ እና ለሌሎችም አርአያ እንዲሆን በማሰብ የተደረገ ነው ሲሉ ፕሮፌሰር ታደሰ ገልፀዋል::

ርዕደ መሬት ምክንያት በገቢ ረሱ ዞን አዋሽ ፈንታሌ እና አካባቢው ካሉ 6 ቀበሌዎች 10ሺ የሚሆኑ ነዋሪዎች ከቀያቸው ተፈናቅለው በ 3 መጠለያ ጣቢያዎች እንደሚገኙ እና ተጨማሪ ድጋፍ እንደሚያሰፈልግ እንዲሁም ወደተሻለ ቦታ ለማዘዋወር እየተሰራ እንደሆነ የአደጋና ሰጋት መከላከል ቢሮ ም/ሀላፊ በርክክቡ ወቅት ገልጸልናል::



ድጋፍ

ዩኒቨርሲቲው ለሀገራዊ የአረንጓዴ አሻራ ችግኞችን ድጋፍ ተደርጓል

የሠመራ ዩኒቨርሲቲ ምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት በግብርና ሰርቶ ማሳያ ጣቢያ የተዘጋጀ የዘይቱና ችግኝ ለገረኒ ወረዳ አስተዳደር ድጋፍ አድርጓል::

የሠመራ ዩኒቨርሲቲ ምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት በማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በኩል ከግብርና ኮሌጅ ጋር በመተባበር የቀረበ ሶሆን ችግኞችን ከማቅረብባለፈም ተቋማዊ አሻራውንለትውልድ ለማስቀመጥ እስራ መሆኑን አመላክቷል።



ባለፈው አመት የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግሰት ከፍተኛ አመራሮች እና የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ አመራሮች በአዋሽ ዱለሳ ወረዳ አመታዊ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ-ግብር ማከናወናቸው የሚታወሰ ነው።
ዛፍ መትከል ብዝሃ ህይወትን በመጠበቅ፣ ጤናማ ሰርዓተ ምህዳር እንደሚፈጥር እና የዛሬ ችግኝ የነገ ውበት ምግብ እና መጠለያ መሆኑን ሰመራ ዩኒቨርሲቲ አሰገንዝቧል።



ድጋፍ

በኢትዮጵያ ዳያስፖራ ለአፋር ታለንት አካዳሚ መጻሕፍት አስረክበዋል




በኢትዮጵያ ዳያስፖራ ለአፋር ታለንት አካዳሚ የተበረከተ ጉልህ የመጻሕፍት አስረክበዋል።

ይህ ድጋፍ በአምባሳደር ሀሰን አብዱልቃድር በካናዳ ቆይታው የተሰበሰብ ሲሆን ለትምህርት ግብአት የላቀ አበርክቶ ይኖረዋል።

በተጨማሪም ዶ/ር መሐመድ የኢትዮጵያ አየር መንገድ መፅሃፎቹን ከካናዳ ወደ ኢትዮጵያ ለማጓጓዝ በማመቻቸት ላደረገው ወሳኝ ሚና እውቅና ሰጥተዋል። ይህ ትብብር የትምህርት እድገትን ለማሳደግ የሚያስፈልገውን የጋራ ጥረት ያጎላዋል።

የመጽሐፍቶቱ ድጋፍ ወደ ግማሽ ሚሊዮን የሚጠጋ የኢትዮጵያ ብር የሚገመተው እና በአፋር ወጣቶች የወደፊት ዕጣ ፈንታ ላይ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

ዶ/ር መህመድ ባለፈው አመት ከአፋር ትምህርት ቢሮ ጋር በመተባበር በአካዳሚው የተማሪዎችን የትምህርት ግብአት በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያሳድግ ቃል የገባለትን ዶ/ር ሙሉ ላደረጉት የላቀ ምስጋና አቅርበዋል።



ድጋፍ

በመሬት መንቀጥቀጥ ለተፈናቀሉ ወገኖች ሙያዊ እና ሰብአዊ ድጋፍ

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ አመራሮች 1 ሚሊየን ብር የሚገመት ዱቄት እና ዘይት በመሬት መንቀጥቀጥ ምክንያት ከቀያቸው ተፈናቅለው በሁለት መጠለያዎች ለሚገኙ ምግብነክ ድጋፍ ለተቋቋመው ግብረ ሀይል አስረክበዋል::



በተጨማሪም የዩኒቨርሲቲው የሰነ-ምድር ባለሙያዎች ለበርካታ የሀገር ውሰጥ እና የውጪ የሚዲያ ተቋማት:ተመራማሪዎች እና ሰብአዊ ድርጅቶች በተደጋጋሚ የተከሰተውን የመሬት መንቀጥቀጥ: የህዝቡን ሁኔታ እና የደረሱ ጉዳቶችን የተመለከቱ ወቅታዊና በሳይንሳዊ ዘዴ የተሰበሰቡ መረጃዎችን እያደረሰ እንደሚገኝ አመራሮቹ ገልጸዋል።

የዩቨርሲቲው ባሳለፍነው ታህሳስ ወር Earthquake Awareness Across Sectors in Afar Region በሚል ርዕሰ የክልል ባለድርሻ አካላትን ያካተተ የጥናት ውጤት የቀረበበት እና በቀጣይ በትብብር የሚሰሩ ሰራዎች ላይ ያተኮረ አውደ ጥናትም ማካሄዱ ይታወሳል::



ድጋፍ

በሲባይቢ ወረዳ የእንስሳት ወረርሽኝ የህክምና አገልግሎት

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ በያንጉዲ ዞን ሲባይቢ ወረዳ አራት ቀበሌዎች ድንገተኛ የእንስሳት ወረርሽኝ መከሰቱን ተከትሎ ከህብረተሰቡ በቀረበለት ጥያቄ መሰረት ተንቀሳቃሽ የእንስሳት ህክምና አገልግሎት ቡድን በመላክ የሶስት ቀን ዘመቻ ማድረጉን ገልጿል::





ሰመራ ዩኒቨርሲቲ በያንጉዲ ዞን ሲባይቢ ወረዳ አራት ቀበሌዎች ድንገተኛ የእንስሳት ወረርሽኝ መከሰቱን ተከትሎ ከህብረተሰቡ በቀረበለት ጥያቄ መሰረት ተንቀሳቃሽ የእንስሳት ህክምና አገልግሎት ቡድን በመላክ የሶስት ቀን ዘመቻ ማድረጉን ገልጿል::

የህክምና ቡድኑ ከወረዳው ግብርናና አርብቶ አደር ጽ/ቤት ጋር በመተባበር ወረርሽኙ በተከሰቱባቸው በኡዴልታ፣ ቴሌ፣ ኡንዳፎያ እና ቤሎቡሊ ቀበሌዎች 3ሺህ የሚሆኑ እንስሳትን በተሳካ ሁኔታ ማከም ተችሏል ሲል የህክምና ቡድኑ አስታውቋል።



ድጋፍ

የኢትዮጵያ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የምክክር መድረክ በመሬት መንቀጥቀጥ ለተጎዱ ድጋፍ



የኢትዮጵያ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የምክክር መድረክ (መዩምመ) በአፋር ክልል በርዕደ መሬት ምክንያት ከቀያቸው ለተፈናቀሉ ወገኖች 4 ሚሊዮን 542 ሺ ብር ድጋፍ በሰመራ ዩኒቨርሲቲ በመገኘት አሰረክቧል::

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ የመሬት መንቀጥቀጥ ከጀመረበት መሰከረም ወር ጀምሮ የበኩሉን የተለያዩ የቁሳቁስ እና የባለሙያ ድጋፍ ሲያደርስ የቆየ ሲሆን: በተጨማሪም ተቋማትን በማስተባበር ባሳለፍነው ወር የራያ ዩኒቨርሲቲ የቁሳቁስ ድጋፍ እንድሁም ዛሬ 23 ዩኒቨርሲቲዎች በኮንሰርቲየሙ በኩል 4.5ሚሊየን ብር በላይ ድጋፍ ማድረስ ተችሏል::



የኢትዮጵያ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የምክክር መድረክ (መዩምመ) 49 አባል ዩኒቨርሲቲዎች ያሉት ሲሆን: ከእነዚህ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ 23ቱ ከ4.5 ሚሊየን ብር በላይ የገንዘብ ድጋፍ ለወገኖች አድርገዋል::

የዩኒቨርሲቲዎች የምክክር መድረኩ ምንም እንኳን የተቋቋመበት ዋና አላማ የተሻለ የትምህርት ጥራትንና ተደራሽነትን በዩኒቨርሲቲዎች ማረጋገጥ ቢሆንም ከተቋቋመበት 2003 ዓ.ም ጀምሮ ለበርካታ ወገኖች ድጋፍ በማድረግ ማህበራዊ ተሳትፎ አድርጓል።



ድጋፍ

የቅሪተ አካል እና መጽሐፍት ድጋፍ

ለማስተማሪያ የሚሆን የቅሪተ አካል እና መጽሐፍት ለአንትሮፖሎጂ ዲፓርትመንት ድጋፍ ተደረገ።



ዶ/ር ሬኮተር በቅርቡ በዩኒቨርሲቲው ባደረጉት ጉብኝት ከአንትሮፖሎጂ እና ጂኦሎጂ ሰራተኞች ጋር በመሆን የአካዳሚክ ግንኙነቶችን በማጠናከር እና የምርምር ትብብርን እንደሚሰሩ ገልጸዋል።

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ አንትሮፖሎጂ ትምህርት ክፍል ከዶክተር ኤሚ ሬኮተር ተባባሪ ፕሮፌሰር እና የሌዲ ገራሩ የምርምር ፕሮጀክት አባል (ከ25 ዓመታት በላይ በጂኦሎጂ ፣ በፓሊዮንቶሎጂ እና በአርኪኦሎጂ ላይ በአፋር ክልል ውስጥ የሰሩ ፣ ለማስተማሪያነት ጠቃሚ የሚሆን የቅሪተ አካል እና የአካዳሚክ መጽሐፎችን በድጋፍ አግኝቷል።



አቅም ግንባታ ስልጠና

ዩኒቨርሲቲው የሥራ ፈጠራ ስልጠና ሰጥቷል



በሰመራ ዩኒቨርሲቲ እና በአፋር ክልል የሰራ ፈጠራ ቢሮ በጋራ የሚያሰተባብሩት እና የሥራ ፈጠራ ልማት የ የሥራ ፈጠራ ልማት ተቋም (EDI) የሚሰጠው የሰራ ፈጠራ ስልጠና ለዩኒቨርሲቲው መምህራን ሰጥቷል::

ስልጠናውን በሁለት ዙር ከ90 በላይ ለሚሆኑ መምህራን የተሰጠ ሲሆን ስልጠናውን የሥራ ፈጠራ ልማት ተቋም (EDI) የካበተ ልምድ ባላቸው የራሱ ባለሙያዎች መሆኑ ተገልጿል።

ይህን ስልጠና ለመምህራን ማህበረሰቡን በሚጠቅም መልኩ ወጣቶችን በማስልጠን ወደ ሰራ ፈጠራ እንዲገቡ እና በሙያ የታገዘ ሰራ እንዲሰሩ ለማስቻል ያለመ ነው::

ስልጠናውን በሁለት ዙር ከ90 በላይ ለሚሆኑ መምህራን የተሰጠ ሲሆን ስልጠናውን የሥራ ፈጠራ ልማት ተቋም (EDI) የካበተ ልምድ ባላቸው የራሱ ባለሙያዎች መሆኑ ተገልጿል።

ይህን ስልጠና ለመምህራን ማህበረሰቡን በሚጠቅም መልኩ ወጣቶችን በማስልጠን ወደ ሰራ ፈጠራ እንዲገቡ እና በሙያ የታገዘ ሰራ እንዲሰሩ ለማስቻል ያለመ ነው::



አቅም ግንባታ ሰልጠና

ለአመራር ምክር ቤት አባላት የአመራር ሰልጠና ሰጥቷል

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ "የከፍተኛ ትምህርት ለውጥን የመምራት እና የማሰቀጠል የአመራር ሚና" በሚል ርዕሰ ወሳኝ ሰልጠና ሰጥቷል።



ሰልጠናው ከኢትዮጵያ ሰራ አመራር ኢንስቲትዩት የተውጣጡ ክቡር አቶ አብዱልሃሊክ ረሺድ እና አቶ ጅብሪል ዘሪሁን የተመሰከረላቸው ከፍተኛ አመራር ልማት አማካሪዎች፣ አሰልጣኞች እና ተመራማሪዎች እየተሰጠ ነው።

ክፍለ-ጊዜዎቹ ከኦክቶበር 18 እስከ ኦክቶበር 20፣ 2024 (ከዓርብ እስከ እሑድ) ባሉት ሶስት ተከታታይ ቀናት ውስጥ አዲስ በተመረቀው የአሰተዳደር ህንጻ አዳራሽ ውስጥ እንዲካሄዱ ታቅዷል።

ይህ ፕሮግራም በተቋሙ ውስጥ የአመራር ብቃትን በማሳደግ እና በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ዘላቂ ለውጥ ለማምጣት ጉልህ እርምጃን ይወክላል።

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ "የከፍተኛ ትምህርት ለውጥን የመምራት እና የማሰቀጠል የአመራር ሚና" በሚል ርዕሰ ወሳኝ ሰልጠና ዩኒቨርሲቲው ለአመራር ምክር ቤት አባላት ችሎታዎችን አቅም ለማሳደግ ያለመ ነው።



አቅም ግንባታ ሰልጠና

የአሰልጣኞች የሰራ ፈጠራ እና የንግድ ክህሎት ሰልጠና

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ 40 መምህራንን በማሳተፍ ለሰምንት ቀናት የቆየውን የኢንተርፕረነርሺፕ እና የቢዝነስ ክህሎት የአሰልጣኞች ሰልጠና በተሳካ ሁኔታ አጠናቋል።

በዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስር እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀው ይህ ፕሮግራም እነዚህን አሰተማሪዎች በቀጣይም በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣት ግለሰቦችን በመላው አፋር ክልል እንዲያሰለጥኑ ለማድረግ ታሰቦ የተዘጋጀ ነው።

በማሰተር ካርድ ፋውንዴሽን የገንዘብ ድጋፍ የተደረገው ይህ ተነሳሽነት ከኢንተርፕረነርሺፕ ልማት ኢንሰቲትዩት (ኢዲአይ) በመጡ ባለሙያዎች እና በሳማራ ዩኒቨርሲቲ አሰተባባሪነት በብቃት ተከናውኗል።

ሰልጠናው የኢንተርፕረነርሺፕ አቅምን በከፍተኛ ደረጃ የሚያጠናክር እና በክልሉ ውሰጥ ያለውን የንግድ ልማት ያበረታታል ተብሎ ይጠበቃል።



አቅም ግንባታ ሰልጠና የሥራ ዕድል ፈጠራ ሰልጠና



ኢንስቲትዩቱ ከሰመራ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር በኢንተርፕርነርሽፕ እና በንግድ ሥራ ክህሎት ላይ የአሰልጣኞች ሰልጠና መስጠት ጀምሯል።

በዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስር እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀው ይህ ሰልጠና በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣት ግለሰቦችን በመላው አፋር ክልል ማሰልጠን ሚያስችል ነው።

ሰልጠናው የክልሉን የተፈጥሮ ፀጋዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማልማትና ለሥራ ዕድል ፈጠራ ለማዋል ያለመ መሆኑንም አመልክተዋል።

በሰልጠናው ላይየተገኙት የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የምርምርናቴክኖሎጂ ሽግግር ተቀዳሚ ምክትልፕሬዚዳንት አቶ አደም ዓሊበበኩላቸው እንደገለጹት የአሰልጣኞች ሰልጠናመዘጋጀቱ ለበርካታ የአፋር ክልልወጣቶች የሥራ እድል ፈጠራንለማሰፋት የሚያስችል ነው።

ከዚህ ቀደም ለ90 የሠመራ ዩኒቨርሲቲ መምህራን በኢንተርፕነርሽፕ፣ በንግድና በሥራ ክህሎት ተግባር ተኮር ያልሆነ ሰልጠና ከወሰዱት መካከል የተሻለ አፈጻጸም ያስመዘገቡ 40ዎቹ የአሁኑን ተግባር ተኮር ሰልጠና ወሰደዋል።



አቅም ግንባታ ሰልጠና

'በሰሜት ብልህነት መምራት' ላይ ሰልጠና ሰጥተዋል



ሰመራ_ዩንቨርስቲ የአመራር ክህሎትን ለማሳደግ የተነደፈ 'በሰሜታዊ ኢንተለጀንስ መምራት' ላይ ያማከለ ውጤታማ ሰልጠና አካሂዷል።

በአስተዳደር እና ልማት ምክትል ፕሬዝዳንት በዶ/ር ሁሴን ኡመር የተሰጠው ሰልጠና ለተሳታፊዎች የበለጠ ሰሜታዊ ብልህ የሰራ ቦታን ለማልማት አስፈላጊ መሳሪያዎችን ለማቅረብ ያለመ ነው።

ይህ ተነሳሽነት የሳማራ ዩኒቨርሲቲ በአስተዳደር ማዕቀፉ ውስጥ ጠንካራ የአመራር ብቃቶችን ለማጎልበት ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ሲሆን በመጨረሻም የበለጠ አወንታዊ እና ውጤታማ የሰራ አካባቢ ለመፍጠር አስተዋፅያው የጎላ ነው ።

ሰሜታዊ ግንዛቤን እና ውጤታማ ግንኙነትን በማጉላት ፕሮግራሙ የቡድን ተለዋዋጭነትን ለማሻሻል እና አጠቃላይ ድርጅታዊ አፈፃፀምን ለማሻሻል የሚጠቅም ሰልጠና ነው።



አቅም ግንባታ ሰልጠና

የምርምር ህግና ስነ-ምግባር አቅም ግንባታ ሰልጠና ተሰጠ



በሠመራ ዩኒቨርሲቲ ለሁለት ቀናት የሚቆይ በምርምር ስነ-ምግባር ላይ ያተኮረ የአቅም ግንባታ ሰልጠና ተሰቷል።

ሰልጠናው በዩኒቨርሲቲው እስካሁን በሚሰሩ ምርምሮች ላይ በሰፋት የሚታዩ የምርምር ስነ-ምግባር ክፍተቶችን ለመሙላት ያስችላል ተብሏል::
ሰልጠናውን የምርምር ህትመት፣ ስነ-ምግባር እና ሰርፀት ዳይሬክቶሬት ያዘጋጀው ሲሆን ከሁሉም ኮሌጆች እና ትምህርት ክፍሎች የተውጣጡ መምህራን እየተሳተፉበት ይገኛል::

ዩኒቨርሲቲው ተግባራዊ የሚሆኑ እና የማህብረሰቡን ችግር በዘላቂነት የሚፈቱ ምርምሮች በትኩረት መሰኩ ማለትም በግብርና፣ በማዕድን እና ቱሪዝም ላይ እንድሰሩ ሰለሚያስፈልግ ሰልጠናው ለተመራማሪዎች የምርምር ስነ-ምግባር እና ህግን ጠበቀው ምርምር ለመሰራት እንደሚያግዝ ተመላክቷል።



አቅም ግንባታ ሰልጠና ለሀገራዊ የግብርና መረጃ ናሙና ቆጠራ ሰልጣኞች በዩኒቨርሲቲው

በሰመራ ዩኒቨርሲቲ: የኢትዩጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት እና ትምህርት ሚኒስቴር በጋራ ላዘጋጁት የ1ኛ ዙር የግብርና ናሙና ቆጠራ መረጃ ሰብሳቢ ሰልጣኞች ገለፃ ተሰጥቷል።



ከዚህም ባለፈ ለፖሊሰና ስትራቴጂ እውጭዎች፣ ለጥናትና ምርምር ፈጻሚዎች ባጠቃላይ ለአገራዊ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ቆጠራው ጉልህ ጠቀሜታ እንዳለው አውስተዋል።

ይህም በመሆኑ ሰልጠናውን ወስደው ለመረጃ ሰብሰባው የሚሰማሩት ተሳታፊዎች ከመጀመሪው እስከ መጨረሻ ቀን ድረስ ሃላፊነት ተሰምቷቸው እንዲሰሩ መልዕክት አስተላልፈዋል።

በተለይም ለእንሰሳቱ የሚያስፈልጋቸውን የግብዓት ዓይነቶች ለመለየት የሚሰበሰቡት የመረጃ ናሙናዎች ጠቀሜታ ያላቸው መሆኑን አስረድተዋል።

ሰልጠናው የግብርና ቆጠራ በተለይም ለአካባቢው አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር ጠቀሜታው የጎላ ነው።



አቅም ግንባታ ሰልጠና

“የተቋምና የአካዳሚክ ፕሮግራም ዕውቅና አሰጣጥ” ሰልጠና

ለአካዳሚክ ባለሙያዎች ተቋማዊ እና አካዳሚክ ኘሮግራም እውቅና ላይ ያተኮረ የአካዳሚክ ፕሮግራሞች ጥራት ለማሳደግ ያለመ ሰልጠና ተሰጥቷል።

ሰልጠናው በከፍተኛ ትምህርት የጥራት እና የጥራት ማረጋገጫ፡ ፅንሰ-ሀሳቦች እና ተግባራት፣ ውጤት ላይ የተመሰረተ ትምህርት፣ የእውቅና ሂደት እና የእውቅና ደረጃዎች፣ የእውቅና መረጃ ምንጮች፣ ሰልጣኞች የአካዳሚክ እውቅና ውሰብሰብ ጉዳዮችን እንዲዳሰሱ የሚያስችል አሰፈላጊ እውቀትን የመሳሰሉ ርዕሶች ወሰደዋል።





ከዩኒቨርሲቲው ትምህርትና ሰልጠና ባለሰልጣን በተውጣጡ ባለሙያዎች እና የከፍተኛ ትምህርት ፕሮግራም ዕውቅና ባለሙያ ሰልጠናው ተሰጥቷል።

የኮሌጅ እና የትምህርት ቤት ዲኖች ፣የመምሪያ ሓላፊዎች እና መምህራንን ጨምሮ የአካዳሚክ ባለሙያዎች የተሳተፉበት ሰልጠናው ተካሂዷል።

ይህ ሰልጠና ዩኒቨርሲቲው ወደ አፕሊኬሽን ሳይንስ ዩኒቨርሲቲ በሚሸጋገርበት ወቅት ደረጃቸውን የጠበቁ ሰርአተ ትምህርቶችን ለማዘጋጀት እና ለማሻሻል እንደሚረዳ ታምኖበታል።



አቅም ግንባታ ሰልጠና

ከብራይተር ጀነሬሽን ጋር በመተባበር ለተማሪዎች ሰጠ

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ፣ ብራይተር ጀነሬሽን ከተባለ ግብረ-ሰናይ ድረጅት ጋር በመተባበር ለ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች የክረምት ልዩሰልጠና ሰጥቷል።

ትምህርቱ አውሮፖ እናአሜሪካ በሚኖሩ በጎ ፈቃደኛዲያሰፖራ ምሁራን በበይነ-መረብየሚሰጥ ሲሆን፣ ሰልጠናው በተማሪዎቹአቅም ልክ የተዘጋጀ እናለወደፊት ህይወታቸው መሰረት የሚሆን፣የእንግሊዝኛ ቋንቋ ክህሎቶችን እና የአመራርነት ክህሎቶችን ያካተተ ነው።

ሰልጠናው በምርምር እናቴክኖሎጂ ሽግግር ም/ፕሬዚዳንት: የኢንደስትሪ ትሰሰርና ቴክኖሎጅ ሽግግርዳይሬክቶሬት ከመምህራን ጋር በመሆን የሚያሰተባብሩት ነው።





አቅም ግንባታ ሰልጠና

በዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ላይ የአቅም ግንባታ ሰልጠና

በሰመራ ዩኒቨርሲቲ የፈተና ማእከል ዳይሬክቶሬት ከጤናና ህክምና ሳይንስ ኮሌጅ ጋር በመተባበር የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ሰልጠና መርሃ ግብር አካሂዷል።

ከአምሬፍ ሄልዝ አፍሪካ እና ከጃፒዬጎ ጋር በመተባበር በተለያዩ ክፍሎች ውስጥ የመምህራንን እና የሰራተኞችን አቅም ለማሳደግ ያለመ ነው።



ሰልጠናው በሞዴል ትምህርት አስተዳደር ሰርዓት ላይ ያተኮረ ነው። የአካዳሚክ ፕሮግራሞች ዳይሬክተር የሆኑት አቶ አብደላ ይህ ሰልጠና እንደ ኢ-መማር እና እውቅና ያለው የሰርዓተ ትምህርት አስተዳደርን የመሳሰሉ ወሳኝ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ለማድረግ ያለውን ጠቀሜታ አፅንዖት ሰጥተዋል። ይህ ሰልጠና የተሳታፊዎችን ዲጂታል ብቃት በከፍተኛ ደረጃ ያሳድጋል ተብሎ ይጠበቃል።



አቅም ግንባታ ሰልጠና

የኢትዮጵያ ህግ ትምህርት ቤቶች ማህበር ተማሪዎች ሰልጠና ሰጠ።

ከአምሬፍ ሄልዝ አፍሪካ እና ከጀፒዬጎ ጋር በመተባበር በተለያዩ ክፍሎች ውስጥ የመምህራንን እና የሰራተኞችን አቅም ለማሳደግ ያለመ ነው።

የኢትዮጵያ ህግ ትምህርት ቤቶች ማህበር በግጭት አፈታት እና ሁከት መከላከል ላይ ያተኮረ ሰልጠና ለሰመራ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ት/ርት ቤት ተማሪዎች ሰጥቷል።





ይህ ለ20 የህግ ተማሪዎች የተሰጠው የ4 ቀን ሰልጠና ተማሪዎቹ በሁከትና ግጭት አፈታት ዘዴዎች ላይ ያተኮሩ ትንንሽ ፕሮጄክቶችን እንድነድፉ የሚያግዝ ሲሆን በቀጣይ ሰልጠናውን ለሁሉም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በተለይ ተፅዕኖ ፈጣሪ ሰዎችን በማሳተፍ ለመሰጠት እንዳቀደ ማህበሩ ገልጿል።

የኢትዮጵያ ህግ ትምህርት ቤቶች ማህበር ፕሮጀክቱን The International Foundation for Electoral Systems እና USAID የደገፉት መሆኑን ገልጾ ይህንን ተነሳሽነት ወደ ሌሎች ዩኒቨርሲቲዎችም ለማስፋፋት ማቀዱን አመላክቷል።



አቅም ግንባታ ሰልጠና

ታዳጊዎቹ የተሰጠውን የክረምት ሰልጠና አጠናቀው ተመረቁ



ሠመራ ዩኒቨርሲቲ Bright generation እና Stem Power ከተባሉ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ ተማሪዎችን አሰመርቋል።

ተቋሙ በራሱ እና ከተባባሪ ተቋማት ጋር በመሆን ታዳጊዎችን በትምህርት ፣ በቴክኖሎጂ ለማብቃት በበጋ እና በክረምት ከጀመራቸው በርካታ ሥራዎች መካከል አንዱ ይሄ በመሆኑ ተጠናክሮ ይቀጥላል ።



በምረቃ ሰነ-ሰርዓቱ የተማሪ ቤተሰቦች የዩኒቨርሲቲው ከፍተኛና መካከለኛ አመራሮች፣መምህራን እና የሰልጠና አሰተባባሪዎች ተገኝተዋል።

ተማሪዎችየሳይንስ፣ የሒሳብ፣ የቴክኖሎጂየእግሊዝኛ ቋንቋ፣ የአመራር ጥበብእና የህይወት ክህሎትሰልጠናዎችን በሚገባ ወሰደውለምረቃ መብቃታቸው ጀምሮበመጨረስ አቅማቸውን ያሳዩበትእና ለሌሎች ምሳሌየሚሆን ሰራ ነውበማለት የምርምር እናቴክኖሎጂ ሽግግር ተ/ም/ፕሬዚደንትአቶ አደም አሊገልጸዋል።



አቅም ግንባታ ሰልጠና

ሰልታዊ ግምገማ እና NETWORK ሜታ-ትንተና ሰልጠና



የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ለኮሌጁ አባላት “የላቀ ሰልታዊ ግምገማ፡ የእውታረ መረብ ሜታ-ትንታኔ” በሚል ርዕሰ ጠቃሚ የሥልጠና መርሃ ግብር አካሂዷል።

ሰልጠናው የተመራማሪዎችን ሰልታዊ ግምገማዎች እና ሜታ-ትንተና፣ የምርምር ግኝቶችን ለማዋሃድ እና በማሰረጃ ላይ የተመሰረቱ ልምዶችን ለማሳደግ ያለመ ነው።

ይህ ሰልጠና የመምህራንን ከፍተኛ ጥራት ያለው ሰልታዊ ግምገማዎች ጠቃሚ ግንዛቤዎችን በከፍተኛ ሁኔታ ያሲዛቸዋል። ይህ እውቀት ዋና ዋና የምርምር ሀሳቦችን ለማዳበር እና በታዋቂ የምርምር መጽሔቶች ውስጥ ጽሁፎችን የማተም መጠን ይጨምራል።



አቅም ግንባታ ሰልጠና

በቲማቲክ ምርምር ላይ ሰልጠና

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ የምርምር እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ምክትል ፕሬዝዳንት ጽህፈት ቤት በቲማቲክ ምርምር ላይ አጠቃላይ የሰልጠና መርሃ ግብር ሁለት ቀናት ሰጥቷል።



ሰልጠናው በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የሚደረጉ የምርምር ስራዎችን ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ አስፈላጊ የሆኑ የተለያዩ ወሳኝ ርዕሶችን ይዟል።

በሜጋ፣ በትልልቅ እና መካከለኛ ደረጃ የምርምር ፕሮጀክቶች ላይ ለተሰማሩ ከፍተኛ የአካዳሚክ ባለሙያዎች በቲማቲክ ምርምር ላይ አጠቃላይ የሰልጠና መርሃ ግብር ሁለት ቀናት ሰጥቷል።

ሰልጠናው ከሀገራዊ የምርምር ቅድሚያ የሚሰጧቸው ጉዳዮች ጋር መጣጣም እና የኢንተር ዲሲፕሊን ቡድኖችን መመስረትን ጨምሮ ዋና ዋና የምርምር ዘርፎችን አካቷል።
በተጨማሪም፣ ክልላዊ እና አለምአቀፍ ትብብር የቲማቲክ ምርምር ተፅእኖን እና ወሰንን ለማሻሻል አስፈላጊ ናቸው።



አቅም ግንባታ ሰልጠና

በመሠረታዊ ጂአይኤስ እና በጂፒኤስ ሰልጠና ተሰጠ

ለውጤታማ የውሳኔ አሰጣጥ እና ግብአት አሰተዳደር በጂአይኤስ እና በጂፒኤስ ላብራቶሪዎች ከተደረጉት የሰልጠና ክፍለ ጊዜዎች የተገኙ ሲሆን ይህም ተሳታፊዎች በየመሰካቸው ለተሻሻለ የመረጃ ትንተና እነዚህን መሳሪያዎች እንዲጠቀሙ አሰችሏቸዋል።





በሰመራ ዩኒቨርሲቲ ለአፋር ብሔራዊ ክልላዊ ኢንዱስትሪ(ቢሮዎች) በመሰረታዊ ጂኦግራፊያዊ መረጃ ሲሰተምሰ (ጂአይኤስ) እና ግሎባል ፖዚሽን ሲሰተምሰ (ጂፒኤስ) ላይ ጠቃሚ ሰልጠና ተሰጥቷል።

ሰልጠናው ከተለያዩ የአፋር ክልል ኢንዱስትሪዎች/ቢሮዎች የተውጣጡ ባለሙያዎችን ክህሎት ለማሳደግ ያለመ ነው።
የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ለባለሙያዎች ለሙያ እድገታቸው ከፍተኛ አሰተዋጽኦ ላበረከተው እና በአፋር ክልል የኢኖቬሽን እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማጎልበት ያለውን ቁርጠኝነት በማሳየቱ ተመሰግኗል።



አቅም ግንባታ ሰልጠና

የሰነ-ምድር ት/ቤት ቤተ-ሙከራ ባለሙያዎች ሰልጠና እየሰጠ ነው

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ የሰነ-ምድር ት/ቤት ቤተ-ሙከራን በአዳዲስ የAtomic Absorption Spectrophotometer (AAS) ማሽኖችን እንደገና በማደራጀት ፣ ከጂኦሎጅ ፣ ኬሚስትሪ ፣ ግብርና እና ምህንድስና ትምህርት ክፍሎች ለተውጣጡ መምህራን እና የቤተ-ሙከራ ባለሙያዎች መሰረታዊ ሥልጠና



የተጀመሩት ሰራዎች ፣ የዩኒቨርሲቲውን የተግባር ዩኒቨርሲቲነት ጉዞ የሚያቀላጥፉ እና በልህቀት መስኮቹ ላይ እቅሙን ለማሳደግ: ጠቀሜታቸው የጎላ ነው::

የAAS ማሽን በጂኦሎጂ ፣ ምህንድስና ፣ ሰነ-ምግብ እና የአካባቢ ጥናት በኩል የሚሰሩ የውሃና የማዕድን ጥራትና ይዘትን ለመተንተን፣ የኬሚካልንና፣ የመሬትን ናሙና ትንታኔን በመሰራት ምርምርን እና ትምህርትን ለማሻሻል የሚረዳ እይነተኛ መሳሪያ መሆኑን ባለሙያዎች ገልጸዋል ።



አቅም ግንባታ ሰልጠና

ለሰራተኞች ተመራማሪዎች አጠቃላይ ሰልጠና ሰጠ

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ በቆቦ Toolbox እና በ STATA ሶፍትዌር ላይ ለአካዳሚክ ሰታፍ ተመራማሪዎች የአራት ቀናት ሰልጠና ሰጥቷል።



ዓላማው ተሳታፊዎችን በተግባራዊ ክህሎት እና እውቀት ለማስታጠቅ Kobo Toolboxን በመሰመር ላይ እና በሞባይል መረጃ ለመሰብሰብ እና STATA ለሰታቲስቲክስ ትንተና በመጠቀም መረጃን በብቃት እንዲሰበሰቡ፣ እንዲያሰተዳድሩ እና እንዲተነትኑ ለማድረግ ነው።

ሰልጠናው የKobo Toolbox የመረጃ አሰባሰብን ለማቀላጠፍ፣ ወጪን ለመቀነሰ እና የምርምር የሰራ ሂደቶችን ለማሻሻል እንደ ሃይለኛ መሳሪያ ያሳያል።



በተግባራዊ ክፍለ-ጊዜዎች፣ ተሳታፊዎች የመረጃ ታማኝነት፣ አሰተማማኝነት እና የምርምር ቅልጥፍናን ለማረጋገጥ ተግባራዊ እውቀት ያገኛሉ።

በተጨማሪም ሰልጠናው ውሰብሰብ የመረጃ ሰብሰቦችን ለመተንተን በ STATA የላቀ የሰታቲስቲክስ ቴክኒኮች ላይ ያተኩራል።



አቅም ግንባታ ሰልጠና

የ RADMS የሰልጠና ማጠቃለያ ፕሮግራም



በዘመናዊ የመንገድ ትራፊክ አደጋ መረጃ አያያዝ ላይ ትኩረቱን ያደረገ አዲስ የ RADMS ድጂታል መተግበሪያ ሰልጠናፕሮግራም ተካሄዷል::

የRoad Accident Data Management System (RADMS) መተግበሪያ የፌደራል የመንገድደህንነት እና መድን ፈንድአገልግሎት ፣ ትራንሰፖርት እናሎጅስቲክስ ሚኒስቴር እና ፌደራልፖሊስ ኮሚሽን በጋራ ያበለፀጉት በመላ ሀገሪቱ ወደ ሰራ የገባ መተግበሪያ መሆኑ ተገልጿልነው::

መተግበሪያው ከአፋር ክልል ከወረዳ፣ዞን በየደረጃው የሚላኩለትን የትራፊክ መረጃዎችን በማቀናጀት ወደ ማዕከል ለመላክ የሚያስችል: አደጋን የመከላከል ፣ አደጋዎች ሲፈጠሩ ፈጣን ምላሽ የመስጠት እና መረጃዎችን በዘመናዊ መልኩ የመስነድ እንዲሁም ለጥናትና ምርምርአገልግሎት ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚያስችል መሆኑ ተመላክቷል::

በማጠቃለያ ፕሮግራሙ ላይ የፌዴራል፣ አፋር ክልል እና የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ መካከለኛ አመራሮችም ተገኝተዋል::



አቅም ግንባታ ሰልጠና

ለሴት ተማሪዎች የሕይወት ክህሎት ሰልጠና እና የልምድ ልውውጥ



የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተመራጭ ሴቶች ኮከስ ፣ ከሰው ሀብት ልማት ሥራ ሰምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ከሠመራ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመሆን ለዩኒቨርሲቲው ሴት ተማሪዎች የሕይወት ክህሎት ሰልጠና እና የልምድ ልውውጥ መድረክ ተካሄዷል::

ሰልጠናው በሕይወት ክህሎት ዙርያ ማለትም በGoal Setting, Time Management and Designing Your Future ላይ ያተኮረ ሲሆን ሴት የምክር ቤት አመራሮች የራሳቸውን የህይወት ተሞክሮአቸውን በዩኒቨርሲቲው ከመጀመሪያ ዓመት እስከ ተመራቂዎች ድረስ ከ 500 ለሚልቁ ሴት ተማሪዎች አካፍለዋል::



አቅም ግንባታ ሰልጠና

ከመካከለኛ አመራሮች ጋር በቁልፍ ጉዳዮች ላይ ውይይት ::



የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር መሀመድ ኡስማን በቁልፍ የአፈፃፀም ጉዳዮች ፣በመውጫ ፈተና ፣ የሰራተኞች የብቃት ምዘና እና ከመሀል ሆኖ መምራት ላይ ያተኮረ ውይይት ከመካከለኛ አመራሮች ጋር አድርገዋል::

ፕሬዚዳንቱ በመሩት በዚህ መድረክ ለውይይት መነሻ የሚሆኑ በስትራቴጅክ ጉዳዮች ሰራ አስፈጻሚ እና በፕሬዝዳንቱ ድጋፍ ሰጪ ቡድን የተዘጋጁ የሰራ ሪፖርቶች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል::

መድረኩ በተነሱት ቁልፍ ጉዳዮች ላይ የዘርፎችና የክፍሎች ቁመና የተለየበት እና ድጋፍ ለሚሹት የክትትል እና ጥሩ አፈፃፀም ላሳዩት ማበረታቻ የሚሆን የወደፊት አቅጣጫ አስቀምጦ ተጠናቋል::

በመጨረሻም ፕሬዚዳንቱ ለዩኒቨርሲቲው ህክምና ትምህርት ቤት/School of Medicine ለተማሪዎች ተግባራዊ የህክምና ትምህርት መስጫ እየተሰናዳ ያለውን ልዩ Cadaver Dissection Room ግንባታ የደረሰበትን ደረጃ ጎብኝተዋል::



Samara University
2024/25
Annual Magazine
Third Edition ሦስተኛ ዕትም
የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

አቅም ግንባታ ሰልጠና

የሲቢኤምፒ የግምገማ ሰብሰባ አውደ ጥናት



የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ከአፋር ክልል ጤና ጥበቃ ቢሮ እና ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር በአቅም ግንባታ እና ክትትል መርሃ ግብር (CBMP) ፕሮጀክት ላይ የክለሳ ሰብሰባ አውደ ጥናት በተሳካ ሁኔታ አካሄደ።

ሲቢኤምፒ ፕሮጀክት በተመረጡ አራት ወረዳዎች - ማሌ፣ ታላላክ፣ ጭፍራ እና ሰመራ - ሎጊያ - በ12 ጤና ጣቢያዎች እና 41 ጤና ኬላዎች ውስጥ አገልግሎት መሰጠት ነው ።

በሰመራ ዩኒቨርሲቲ የሚመራው ከአራቱ ተቋማት ጋር በመደበኛ የመግባቢያ ሰነድ በመተግበር ላይ ሲሆን ይህም ጠንካራ እና ወቅታዊ ክልላዊ የጤና መረጃ አያያዝ ሰርዓት ለመገንባት እና ለማሰቀጠል ያለመ ነው።

ኘሮግራሙ የክልሉን የጤና መረጃ ሰርዓት ለማጠናከር በዲጂታላይዜሽን፣በአቅም ግንባታ እና በፕሮጀክት ወረዳ ለሚገኙ የጤና ባለሙያዎች የተግባር ሰልጠና በመሰጠት ሴቶችን ጨምሮ ሁሉን አቀፍ ተሳትፎ ላይ በማተኮር ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል።

በአፋር ክልል የጤና አገልግሎት አሰጣጥን ለማሳደግ ትብብሩን በዘላቂነት ማሰቀጠል ያለውን ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታም አጽንኦት ሰጥቷል።



አቅም ግንባታ ሰልጠና

የምርምር ፕሮጀክቶችን የሚገመግም አውደ ጥናት አካሂዷል።



የሰመራ ዩኒቨርሲቲ በውስጥ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸውን የምርምር ፕሮጀክቶቹን ገንግሟል፣ ይህም ለክልሉ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ተግዳሮቶች አዳዲስ መፍትሄዎችን አጉልቶ ያሳያል።

ጂኦ-ቱሪዝም፣ ባዮቴክኖሎጂ፣ ዲጂታል ፈጠራ፣ ግብርና፣ የህብረተሰብ ጤና፣ የአፈር ሳይንስ፣ የአየር ንብረት መቋቋም፣ የከተማ ልማት እና የሰነ-ምህዳር ጥበቃን ጨምሮ ቁልፍ በሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ምርምር አሳይቷል።

አውደ ጥናቱ ለክልላዊ ለውጥ ሁሉን አቀፍ፣ ዲሲፕሊናዊ አካሄድ አፅንዖት የሰጠ ሲሆን የዩኒቨርሲቲው ሚና በማሰረጃ ላይ የተመሰረተ ፖሊሲ ማውጣት እና በክልላዊ እና በአገር አቀፍ ደረጃ ዘላቂ ልማትን በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና አሳይቷል።



አቅም ግንባታ ሰልጠና

በማሽን መማሪያ ላይ ሰልጠና ሰጠ።

ዩኒቨርሲቲው በምርምር፣ ሕትመት፣ ሰነ-ምግባር እና ሰርፀት ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ "የማሽን መማሪያ ፋውንዴሽን በፓይዘን" የተሰኘ የሶስት ቀናት የሰልጠና መርሃ ግብር አከናውኗል።

የሰልጠናው ዓላማ ፋኩልቲዎችን በ AI እና በዳታ ሳይንስ ውስጥ በተግባራዊ፣ በፍላጎት የሚፈለጉ ክህሎቶችን ለማስታጠቅ ነው።

በ AI እና በዳታ ሳይንስ ውስጥ ተፈላጊ ችሎታዎች፣ እንደ ጤና አጠባበቅ ፣ግብርና እና ፋይናንስ ካሉ መሰኮች ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን በ Python ላይ የተመሠረተ የማሽን መማሪያ መተግበሪያዎች።





ሰልጠናው AIን ከዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ እና የምርምር ባህል ጋር በማዋሃድ አንድ እርምጃ ወደፊት የሚያመለክት ነው።




አቅም ግንባታ ሰልጠና

ለክልል ኢንዱስትሪዎች የ FAO-CROPWAT ሶፍትዌር ሰልጠና

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ለተመረጡ የአፋር ክልል ኢንዱስትሪዎች “Advancing Irrigation Scheduling for Efficient Agricultural Water Management using FAO-CROPWAT for Selected Afar Region Industries” በሚል ርዕሰ የተግባር ሰልጠና ለዘርፉ ባለሙያዎች ሰጥቷል።





በሰልጠናው የአፋ/ብ/ክ/መ/ የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ልማት ቢሮ ፣የእንሰሳትና አሳ ሃብት ልማት ቢሮ፣ የመሰኖና ቆላማ አካባቢ ቢሮ፣ የአደጋ ሰጋት አመራር ኮሚሽን፣ የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር ምርምር ኢንስቲትዩት የተውጣጡ ባለሞያዎች ተሳትፈውበታል።



አቅም ግንባታ ሰልጠና

2017 ተመራቂ ተማሪዎች ሰልጠና

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ከኢትዮ ቴሌኮም ሰመራ ቅርንጫፍ ጋር በመተባበር ለተመራቂ ተማሪዎች Internet Protocol (IP)፣ IT Operation እና Networking ላይ ትኩረቱን ያደረገ ሰልጠና ሰጥተዋል።



ሰልጠናውን የሰጡት የኢትዮ ቴሌኮም ባለሙያዎች ሲሆኑ ከ60 በላይ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና ኮምፒውተር ሳይንስ ተመራቂ ተማሪዎች ተሳትፈውበታል::



አሰልጣኞቹ በድርጅታቸው ያካበቱትን ልምድ በማካፈል: ተመራቂ ተማሪዎቹ በኢትዮቴሌኮም እና ሌሎች የቴክኖሎጂ ድርጅቶች ሰራ ለመቀጠር የሚያስችላቸውን የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ እንደሆነም ተገልጿል።



ጉድኝት

የአፋር ተሰጥኦ አካዳሚ ለማሳደግ የመግባቢያ ሰነድ ተፈራረመ



የሰመራ_ዩኒቨርስቲ ከካናዳ የአፋር ማህበረሰብ ማህበር (ACAC) ጋር የመግባቢያ ሰምምነት ተፈራርሟል።

የአፋር ተሰጥኦ አካዳሚ የተጀመሩ ሥራዎችን ለማጠናከር እና ለማሰፋፋት ለአፋር ወጣቶች መሰል የትምህርት እድሎች በጋራ በቁርጠኝነትን በማሳየት ከተከበረው የአፋር ህዝብ አጋር የአፋር ዲያስፖራ 'Can-Go Afar Foundation' ውይይቱን አድርገዋል ።

በዶ/ር መህመድ ኡስማን፣ የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት፣ ሚስተር ጀማል አህመድ ቼም፣ የኤሲሲ ፕሬዝዳንት እና ዋረን ኤል ፍጠር የካን-ጎ አፋር ፋውንዴሽን መሰራች እና ፕሬዝዳንት መሪነት ይህ ትብብር በኦታዋ የሚገኙ የአፋር ዳያስፖራ አባላት በተገኙበት ተፈራርመዋል።

በመጨረሻም ዶ/ር መህመድ ኡስማን ከ2008 ጀምሮ ላበረከቱት አስደናቂ አስተዋፆኦ የዜግነት እና የኢሚግሬሽን ህግ ባለሙያ ዋረን ኤል ፍጠርስ ያላቸውን ክብር እና ምስጋና ገልጸዋል።



ጉድኝት

የማህበረሰብ ድጋፍን ለማሳደግ ከዩኤንኤችአር ጋር ውይይት አድርጓል።

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ በአካባቢው እና ሰደተኛ ማህበረሰቦችን ለመደገፍ በሚደረገው የትብብር ሰራዎች ላይ ተወያይተዋል።

በውይይቱ ላይ ዶ/ር መሀመድ ሰለ ዩኒቨርሲቲው እና እንደ UNHCR ካሉ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የሀገር ውሰጥ እና አለምአቀፋዊ ግንኙነቶችን ለማጎልበት ሰላለው ተነሳሽነት ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተዋል።

ሚስተር ቴንኮራንግ UNHCR ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ጋር ለመተባበር ያለውን ቁርጠኝነት በድጋሚ አረጋግጠዋል።

በቴምር ፓልም እና ዲቦራ ባልደረባ ምርት፣በህግ ርዳታ፣በኑሮ፣በጤና እና በሰነ-ምግብ ዙሪያ የዩኒቨርሲቲውን እውቀት በመጠቀም የአካባቢውን ህብረተሰብ፣በክልሉ የሚገኙ ሰደተኞችንና ከሰደት ተመላሾችን ተጠቃሚ ማድረግ አሰፈላጊ መሆኑን አሰምረውበታል።

ውይይቱ የተመረጡትን የመተዳደሪያ ፕሮጀክቶችን ለመከታተል የሚያሰችል የመግባቢያ ሰነድ ለመፈረም ሰምምነት ላይ ደርሷል።



ይህ አጋርነት የዩኤንኤችአር ኔትወርኮችን በሳማራ ዩኒቨርሲቲ ከሚገኙ የሰው ሃይሎች ጋር በማዋሃድ ለተቸገሩ ሰዎች የሚሰጠውን ድጋፍ የበለጠ ለማሳደግ ያለመ ነው።

በተጨማሪም ፕሬዝዳንቱ SU IOM የእቅም ማጎልበቻ ሰልጠናዎችን እና ምክክርን የሚሰጥበት 'የሰደት ጥናት ማዕከል' ሊያቋቁም መዘጋጀቱንም አሰረድተዋል።

ማዕከሉ ከሰደት ጋር ተያይዘው የሚመጡ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ ዩኒቨርሲቲው የሚጫወተውን ሚና ለማጠናከር ትልቅ ርምጃ ነው።



ጉድኝት ከDAI GLOBAL LLC ጋር በጋራ ለመሰራት የመግባቢያ ሰነድ ገብቷል።

ሰመራ_ዩንቨርስቲ የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርሟል። ይህ ተነሳሽነት በአፋር ክልል ውስጥ የሰዎችን ፣ የተቋማትን እና ሰርዓቶችን የመቋቋም አቅም ለማሳደግ ያለመ ነው።



በመግባቢያ ሰነዱ መሠረት DAI Global በዩኤስኤአይዲ የወደፊት ፖሊሲ LINK/የምግብ ዋስትና ሻምፒዮንሺፕ (C4FS) ተግባር የቴክኒክ ድጋፍ፣ የማመቻቸት ድጋፍ እና ለአቅም ማጎልበት፣ የጋራ ተፅዕኖ ሞዴልን ተግባራዊ ለማድረግ እና የባለብዙ ባለድርሻ አካላት መድረኮችን እና የፖሊሲ ውይይቶችን በማመቻቸት የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል።

በተራው፣ የሳማራ ዩኒቨርሲቲ በክልሉ ውስጥ ያለውን የPLRA እድገት ለመደገፍ ሰራተኞቹን፣ መገልገያዎችን እና ሀብቶቹን ቆርጧል።

የመግባቢያ ሰነዱን የተፈራረሙት የሳማራ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ኤ/ቪ/ፕሬዝደንት አቶ አደም አሊ ካቦ እና የዩኤስኤአይዲ ፊድ ዘ ፊውቸር ፖሊሲ LINK/ቻምፒዮንስ ፎር ምግብ ዋስትና (C4FS) ተግባር በDAI የሚተዳደር የሀገር ውስጥ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ዶ/ር አንተነህ ግርማ ናቸው።

ሽርክናው በተጨማሪም የእውቀት ምርቶችን በጋራ ለማተም፣ የባለብዙ ባለድርሻ አካላት የወጪ መጋራት እና የፖሊሲ ውይይቶችን እና የረጅም ጊዜ የድጋፍ ድጋፍን እድሎችን ይዘረዝራል።

ጉድኝት

በቁልፍ የአፈጻጸም አመላካች (KPI) ሰምምነት ተፈራርመዋል::



ሰምምነቱን በትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ ሚኒስተር ዴኤታ ክቡር አቶ ኮራ ጡሹኔ እና የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ቦርድ ሰብሳቢ እና የቱሪዝም ሚኒስተር ዴኤታ የሆኑት ክቡር አቶ ሰለሽ ግርማ እና የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር መሀመድ ኡስማን ተፈራርመዋል::

ይህ በቁልፍ የአፈጻጸም አመላካቾች / Key Performance Indicators / ላይ የሚደረገው የሰምምነት ፊርማ በ47ቱም የመንግሰት ዩኒቨርሰቲዎች እና በትምህርት ሚኒሰቴር መካከል እየተፈፀመ ያለ እንደሆነ እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ሰራ በውጤታማነት ለመፈጸም የሚያሰችል የአሰራር ሰርዓት ለመዘርጋት መሆኑን ትምህርት ሚኒሰቴር በቅድመ ፊርማ ውይይቱ ላይ ገልጿል::

የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ድሪባ ኢተቻ(ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የአርብቶ አደሩን የኢኗር ሰልት መሰረት ያደረገ ትምህርት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚያሻ ገልፀዋል። ዩኒቨርሲቲው የባሮ ወንዝን ተከትለው ለሚኖሩ እና ሌሎች አርብቶ አደሮችን ህይወት መቀየር የሚያሰችል ትምህርት ላይ ትኩረት ያደረገ ምርምር መሰራቱንም ጠቁመዋል።



በሠመራ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት አማካሪ አህመድ ኢብራሂም(ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የአርብቶ አደሩን ትምህርት ማሻሻል የሚያሰችል አንድ ማዕከል ለማቋቋም መታቀዱን አስታውቀዋል።
የአርብቶ አደሩን ኢኗር መሰረት ያደረገ የመማር ማስተማር ሰርአትን ለመተግበር ዩኒቨርሲቲዎች ማገዝ እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

ሰምምነቱ ተቋማት ብቃትና ችሎታ ያላቸው ምሩቃንን በማፍራት ሂደት ውስጥ ተጠያቂነትን ከማሰፈን ባለፈ ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የሚያሰችል እና ሳይንሳዊና ዓለም አቀፋዊ መለኪያዎች ላይ ያተኮረ እድገት እንዲኖራቸው የሚያሰችል መሆኑ ተጠቁሟል።

ጉድኝት

በጋራ ለመሰራት የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል።



የሰመራ ዩኒቨርሲቲ እና ሂጅራ ባንክ በሰልጠና እና በማህበረሰብ ተሳትፎ ላይ በጋራ ለመሰራት የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል

በሰመራዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶክተር መሀመድ ኡሰማን እና በሂጅራ ባንክ የኢንፎርሜሽን ሲስተም እና ዲጂታላይዜሽን ምክትል ፕሬዝዳንት የተፈራረሙት የመግባቢያ ሰነድ በ HALAL የፋይናንሺያል ሰርዓት ላይ ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሰልጠና በመሰጠት ለተማሪዎች ፣ለሰራተኞች እና ለሰፊው ማህበረሰብ ስነ ምግባራዊ የፋይናንስ አሰራርን በማስተዋወቅ ላይ ያተኩራል።

የትብብሩ አንድ አካል ሂጅራ ባንክ ለተማሪዎች እና ሰራተኞች በሃላል ፋይናንሺያል ትምህርት ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ አውደ ጥናት አካሂዷል።





ጉድኝት

የመቀሌና የሰመራ ዩኒቨርሲቲዎች በጋራ እንደሚሰሩ ገለፁ::

የመቀሌና የሰመራ ዩኒቨርሲቲዎች ለትግራይና አፋር ህዝቦች ዘላቂ ጥቅምና የጋራ እድገት ማምጣት በሚያስችሉ የምርምርና የማኅበረሰብ አገልግሎት ላይ ትኩረት ሰጥተው እንደሚሰሩ ገለጹ።

ዩኒቨርሲቲዎቹ "የህዝብ ለህዝብ ትስስር ለዘላቂ ሠላም" በሚል መሪ ሃሳብ በአፋር ክልል ዓብዓላ ከተማ ዛሬ የጋራ ምክክር መድረክ አካሂደዋል።

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት መሐመድ ኡስማን (ዶ/ር) እንዳሉት፤ መድረኩ ሠላምና ልማት ተነጣጥለው የማይሄዱ በመሆናቸው ሁለቱም ህዝቦች ቀጣይነት ባለው መንገድ በጋራ እንዲያጎለብቱ ለማስቻል ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

የመርሃ ግብሩ አስተባባሪ ፕሮፌሰር ምትኩ ሀይለ እንዳሉት፤ ዛሬ የተከልናቸው ችግኞች የሁለቱንም ህዝቦች ህብረት በማጠናከር ለአካባቢው ዘላቂ ሰላም መጎልበት አብነት ሊሆን የሚችሉ ናቸው።

የሠመራ ዩኒቨርሲቲ ከመቐለ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመቀናጀት ከአፋር ክልል ሥነ-ምህዳር ጋር የሚስማሙና በዘላቂነት ለህዝቡ ጠቀሜታ ያላቸው የምርምር ተግባራትን ለማከናወን በዕቅድ እንደሚሰሩ ገልጸዋል።

የመቐለ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማኅበረሰብ ተሳትፎ ምክትል ፕሬዚዳንት እያሱ ያዘው (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ዩኒቨርሲቲው በአካባቢው ከሚያካሄዳቸው የምርምር ሰራዎች በተጨማሪ ለሁለቱም ህዝቦች ሙያዊ ሥልጠናዎችን በመሰጠት "የህዝቦች የእርስ በእርስ ግንኙነትን ለማጠናከር ጥረት ይደረጋል" ብለዋል።

የመቐለ ዩኒቨርሲቲ ማኅበረሰብ ክፍሎች 1 ሺህ 500 የፍራፍሬ ተክሎችን በዓብዓላ ወረዳ ተክለዋል።

የሁለቱም አካባቢዎች የአገር ሽማግሌዎች ተወካዮች አቶ ደረጀ ገብረሚካል እና አቶ ዳውድ ንብዓሉ እንደገለፁት፤ በሁለቱም ዩኒቨርሲቲዎች ዛሬ የተጀመረው መርሃ ግብር የህዝቦቹን ግንኙነት ለማጎልበት ቁይዳው የላቀ ነው።

የሁለቱም ዩኒቨርሲቲዎች ፕሬዚዳንቶችን ጨምሮ የአካባቢው አስተዳደሮች፣ የአገር ሽማግሌዎችና የዞን ሁለት ነዋሪዎች ተገኝተዋል።



Samara University
2024/25
Annual Magazine
Third Edition ሦስተኛ ዕትም
የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

ጉድኝት

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ የካን ጎ አፋር ፋውንዴሽን አብሮ ለመሰራት ሰምምነት



በሰመራ ዩኒቨርሲቲ የካን ጎ አፋር ፋውንዴሽን ከፕሬዝዳንታችን ዶ/ር መሐመድ ኡስማን ጋር የተወያዩትን ሃሳቦች እና የተደረሱትን ሰምምነቶች ወደ ተግባር ለመቀየር ዝግጁ እና ቁርጠኛ እንደሆኑ ገልጸዋል።

የካን-ጎ አፋር ፋውንዴሽን እና የኦታዋ አፋር ማህበረሰብ የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር መሀመድ ኡስማን (በስሜን ኢትዮጵያ አፋር ክልል ሰመራ ውሰጥ የምትገኝ) አቀባበል አድርገውላቸዋል። ዶ/ር መሀመድ ሰለ ዩኒቨርሲቲያቸው አጠቃላይ ሁኔታ ገለጻ ካደረጉ በኋላ የአፋር ባህላዊ ምግቦች ግብዣ ተደርጎላቸዋል።

ካን-ጎ አፋር በሰመራ ዩኒቨርሲቲ በአፋር ታለንት አካዳሚ ለተመዘገቡ የአፋር ተማሪዎች የሰኮላርሺፕ ፕሮግራም መደገፍ እንዲሁም ከዩኒቨርሲቲው የቱሪዝም የልህቀት ማዕከል ጋር በመተባበር ሥራዎችን ለመሰራት የሚያሰችል ሰምምነት ደርሰዋል።



ጉድኝት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሙከራ ፕሮጀክት ላይ ውይይት ተካሂዷል።

ፕሮጀክቱን የጀርመን የህንድ እና የኢትዮጵያ መንግስታት በጋራ የሚተገብሩት መሆኑ ተመላክቷል:: ፕሮጀክቱ በአጭር ጊዜ የሚደርስ ማሽላን በማምረት የምስራቅ አፍሪካን የምግብ ዋስትና በአጭር ጊዜ ለማረጋገጥ ያስችላል ተብሏል::



የሶስቱ መንግስታት ተወካዮች ከሰመራ ዩኒቨርሲቲ አመራሮች ጋር ባደረጉት ውይይት በጋራ በሚሰሩባቸው ጉዳዮች ላይ የመከሩ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው ፕሮጀክቱን በጥናትና ምርምር በመደገፍ የበኩሉን ሚና እንደሚወጣ ፕሬዚደንቱ ዶ/ር መሀመድ ኡስማን ገልጸዋል።



ለዚህ ፕሮጀክት በተመረጠው የአፋር ክልል ያለውን ለም መሬት እና የውሀ ሀብት ለፕሮጀክቱ ውጤታማነት ተሰፋ ተጥሎበታል።

የሶስቱ ሀገራት የመንግስት ተወካዮች በዩኒቨርሲቲው የነበራቸው ውይይት እና የመስክ ምልከታ ውጤታማ እንደነበረ እና በቀጣይ ለፕሮጀክቱ ትግበራ የሚሆን በቂ መረጃና ግንዛቤ መያዝ እንደተቻለ ተብራርቷል።



ጉድኝት

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ እና ሂጅራ ባንክ የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ እና ሂጅራ ባንክ በሰልጠና እና በማህበረሰብ ተሳትፎ ላይ በጋራ ለመሰራት የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል።





በሰመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶክተር መሀመድ ኡሰማን እና በሂጅራ ባንክ የኢንፎርሜሽን ሲስተም እና ዲጂታላይዜሽን ምክትል ፕሬዝዳንት የተፈራረሙት የመግባቢያ ሰነድ በ HALAL የፋይናንሺያል ሰርዓት ላይ ተከታታይ የግንዛቤ ማሰጨበጫ ሰልጠና በመሰጠት ለተማሪዎች ፣ለሰራተኞች እና ለሰፊው ማህበረሰብ ሰነ ምግባራዊ የፋይናንስ አሰራርን በማስተዋወቅ ላይ ያተኩራል።

የትብብሩ አንድ አካል የሆነው ሂጅራ ባንክ ለተማሪዎች እና ሰራተኞች በሃላል የፋይናንሺያል ትምህርት ላይ የግንዛቤ ፈጠራ አውደ ጥናት አካሂዷል።



ጉድኝት

ትብብርን ለማጠናከር የሚያስችል የመግባቢያ ሰምምነት ተፈራርመዋል



የሰመራ እና የመቀሌ ዩኒቨርሲቲዎች የህብረተሰቡን ችግሮች ለመቅረፍ የአቅም ግንባታ፣ምርምር፣ኢኖቬሽን እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማሳደግ በጋራ ተባብረዋል።

ከእንስሳት ጤና አጠባበቅ ጀምሮ የ5 ዓመት የጋራ የምርምር እና የማህበረሰብ ተሳትፎ መርሃ ግብር ለማዘጋጀት መሪ ኮሚቴ ተቋቁሟል። ትብብሩን ከፍተኛ ትምህርት ፣የምርምር እና የማህበረሰብ ተሳትፎ ላይ ለመስራት የመግባቢያ ሰነድ ተሰማምተዋል። በቅርቡ በአብአላ ከተማ በTrees4Peace ዘመቻ ላይም አብረው ሰርተዋል።



ጉድኝት ለልህቀት ዘርፍ አለም አቀፍ አማካሪ ቦርድ አቋቁሟል።

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ የቦርድ እውቀት ሰልታዊ መመሪያን ለመሰጠት፣ ምርጥ ልምዶችን ለማካፈል እና አለም አቀፍ ትብብርን ለማመቻቸት እና ተማሪዎችን ለተለዋዋጭ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ የሚያዘጋጅ ሰርአተ ትምህርት እንዲሰጥ ይጠበቃል። ይህ ጅምር ክልላዊም ሆነ ሀገራዊ የቱሪዝም ሴክተሮችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ሲሆን ዘላቂ የኢኮኖሚ ልማትን ከማሰፈንም የላቀ ድርሻ ይኖረዋል።



ይህ ጅምር ክልላዊም ሆነ ሀገራዊ የቱሪዝም ሴክተሮችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ሲሆን ዘላቂ የኢኮኖሚ ልማትን ከማሰፈንም የላቀ ድርሻ ይኖረዋል።



ጉድኝት

ከአለም አቀፍ ትብብር በማጠናከር ጂኦሎጂ ትምህርት ክፍል

ማስተማሪያ ድጋፉ ትልቅ ሚና የተጫወተችው የሰመራ ዩኒቨርሲቲ የጂኦሎጂ ትምህርት ቤት ባልደረባ እና የሌዲ ገራሩ ፕሮጀክት ንቁ ተሳታፊ የሆነችው ራህዋ ገብረ ህይወት ናት።

ወደ አፕላይድ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲ ሰንሸጋገር እነዚህ ቁሳቁሶች ተግባር ተኮር መማር ማስተማር ላይ አበርክቶው የተሻለ ነው።





በዩኒቨርስቲዎቹ መካከል ያለውን ግንኙነት ያጠናክራል፣ የተማሪ እና የሰራተኞች ልውውጥ፣ የጋራ ግብአት እና የጋራ የምርምር ጥረቶችና የትብብሩን ሰፊ አንድምታ አጽንኦት አሳይቷል። ይህ ድጋፍ የአፋር ክልል በአለም አቀፍ ደረጃ እውቅና እያደገ መምጣቱን የሚያሳይ እና ለጂኦሎጂ ትምህርት ቤት ምርምር ወሳኝ ቦታ ሲሆን ሰመራ ዩኒቨርሲቲን የተግባር ትምህርት እና አለምአቀፋዊ የአካዳሚክ ትብብር ማዕከል አድርጎታል።

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ለአካዳሚክ ትብብር ከፍተኛ እድገት ትኩረቱን በማድረግ ለጂኦሎጂ ትምህርት ቤት ዶ/ር ራሞን አሮውሰሚዝ ከአሪዞና ሰቴት ዩኒቨርሲቲ እና ዶ/ር ኤሪን ዲማጊዮ ከፔንሰልቬንያ ሰቴት ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ የሆነ የጂኦሎጂካል ምርምር ላብራቶሪ ቁሳቁሰ ልገሳ አግኝቷል።



ጉድኝት ለ'ትራፊክ ደህንነት ማበልጸጊያ ፕሮጀክት የሶስትዮሽ የመግባቢያ ሰነድ '

የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

ይህ ሰምምነት በአፋር ክልል የመንገድ ደህንነትን ለማሻሻል ጉልህ አበርክቶ ያመጣል። ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ከአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግሰት መንገድ ልማትና ትራንሰፖርት ቢሮ እና ከአፋር ፖሊስ ኮሚሽን ጋር የሶስትዮሽ የመግባቢያ ሰምምነት አድርጓል።



ሰምምነቱ የትራፊክ ደህንነት ማበልጸጊያ ፕሮጀክትን በትብብር ተግባራዊ ለማድረግ ያለመ ሲሆን ይህም የመንገድ አደጋዎችን በመቀነስ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የትራንሰፖርት አሰራሮችን በማሰተዋወቅ ላይ ያተኮረ ነው።

ይህ ሰልጠና ተሳታፊዎች የትራፊክ መረጃን በብቃት እንዲቆጣጠሩ እና እንዲተነትኑ አሰፈላጊ ክህሎቶችን ለማሰታጠቅ እና የፕሮጀክቱን ግቦች የበለጠ እንዲደግፉ ለማድረግ ያለመ ነው።

ይህ ፕሮጀክት በትምህርት ተቋማት፣ በመንግሥታዊ አካላት እና በህግ አስከባሪዎች መካከል ትብብርን በማጎልበት በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት ደህንነታቸው የተጠበቀ መንገዶችን ለመፍጠር ያለመ ነው።





በሰምምነቱ የተገለጹት ዓላማዎች የመንገድ መሠረተ ልማት እና የትራፊክ ቁጥጥር እርምጃዎችን ማሳደግ እና ሰለመንገድ ደህንነት ግንዛቤን የሚያጎለብቱ ፕሮግራሞችን መተግበር ይገኙበታል።

ጉድኝት L'Institut d'Études Politiques et Stratégiques (IEPS) ትብብር

የስመራ ዩኒቨርሲቲ (SU) እና በጅቡቲ የሚገኘው L'Institut d'Études Politiques et Stratégiques (IEPS) የምርምር ትብብርን ለማሳደግ እና መምህራን ለመለዋወጥ የመግባቢያ ሰምምነት (MoU) ተፈራርመዋል።





የመግባቢያ ሰነዱ በምርምር ተግባራት ላይ ትብብርን ለማጠናከር፣ የጋራ ፕሮጀክቶችን ለመስራት የፕሮጀክቶችን በጋራ ማደራጀት አፈጻጸማቸውን ለማሳደግ እና እውቀትን እና ሀብቶችን መጋራት ያለመ ነው። ሁለቱም ተቋማት በዚህ አጋርነት በብሔራዊ እና በክልል ደረጃ ተጽኖአቸውን ለማሰፋት ቁርጠኛ ናቸው።

በጅቡቲ የተመሰረተው የፖለቲካ እና ሰልታዊ ጥናት (IEPS) በወቅታዊ ፖለቲካዊ እና ጂኦፖለቲካል ጉዳዮች ላይ ገለልተኛ ትንታኔዎችን ለመስጠት ያለመ ነው።



መማር ማስተማር

ኦንላይን ኮርስ ያጠናቀቁ ተማሪዎችን አስመርቋል።

ኮርሱ የኮሙኒኬሽን ክህሎቶች፣ ወሳኝ አስተሳሰብ እና ችግር መፍታት እና የማህበረሰብ ፕሮጀክት ላይ ያተኮረ ነው።

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ እና ከብራይት ጀነሬሽን ጋር በመተባበር በአፋር ክልል የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን ያለመ የክረምት ኦንላይን ኮርስ ሰጥቷል።

ለተማሪዎቹ ከኢትዮጵያ ዲያስፖራ በተወጣጡ በጎ ፈቃደኛ መምህራን ቡድን እውቀታቸው እና ለትምህርት ያላቸው ቁርጠኝነት ለተማሪዎቹ በዋጋ ሊተመን የማይችል ግንዛቤዎችን እና እውቀቶችን ሰጥቷቸዋል፣ ለወደፊት ጥረታቸው አስፈላጊ ክህሎቶችን ማሰገንዘብ ችለዋል።

በሥነ ሥርዓቱ ማጠቃለያ ላይ ተመራቂዎቹ የትምህርት ግባቸውን እንዲቀጥሉ እና የተማሩትን ሙያ በማህበረሰባቸው ላይ ለውጥ እንዲያመጡ ለማበልጸግ ያለውን ሚና አመላክቷል ።



መማር ማስተማር

በግብርና፣ በቱሪዝምና በማዕድን ዘርፎች የልህቀት ማዕከል ለመሆን

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ በቀጣይ ዓመታት በግብርና፣ በቱሪዝምና በማዕድን ዘርፎች የልህቀት ማዕከል ለመሆን እየሰራ መሆኑን አስታወቋል።



የዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዝደንት አብዱራህማን ከድር(ዶ/ር) ለኢዜአ እንደተናገሩት ዩኒቨርሲቲው በግብርናው ዘርፍ ትኩረት አድርጎ ለመሥራት መዘጋጀቱን ተናግረዋል።

በዚህም መሠረት በሰብል፣ በእንሰሳትና የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤን በጥናት ታግዞ እንደሚሰራ ነው የገለፁት።
በአካባቢው ከፍተኛ የሆነ የማዕድን ሀብት መኖሩን ጠቅሰው፤ የማዕድን ሀብቶቹን የማልማት እና ሀገራዊ ጥቅም እንዲሰጡ የማድረግ ሃላፊነቱን ይወጣል ብለዋል።

አፋር በተፈጥሮው በርካታ የቱሪዝም መስዕብ ሰፍራዎች ያሉት እንደመሆኑ የቱሪዝም ዘርፉም ከተልዕኮው ዋነኛው መሆኑን አንስተዋል።
ዩኒቨርሲቲው በ50 የትምህርት ክፍሎች እና 107 ፕሮግራሞች ትምህርት በመስጠት ላይ የነበረ መሆኑን ጠቅሰው፤ አሁን ተመሳሳይነት ያላቸውን ፕሮግራሞች ወደ 20 በመለየት የአፕላይድ መልክ እንዲኖረው እየተሰራ ነው ብለዋል።

ዩኒቨርሲቲው ለ2017 ዓ.ም የትምህርት መርሃ ግብር የቅድመ ዝግጅት ሰራዎችን አጠናቆ በሀገር አቀፍ ደረጃ በተቀመጠው መመሪያ መሠረት ለነባር ተማሪዎቹ ትምህርት መሥጠት መጀመሩንም ተናግረዋል።

መማር ማስተማር

ለ2ኛ እና 3ኛ ድግሪ መግቢያ ፈተና NGAT ተፈታኞችን አሰፈትኗል

በአጠቃላይ ስለNGAT የቅድመ ዝግጅት ሂደቶች ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል።





ሰመራ ዩኒቨርሲቲ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚሰጠውን የ2ኛ እና 3ኛ ድግሪ መግቢያ ፈተና NGAT ለሚወስዱ ተፈታኞች የቅድመ ዝግጅት ስልጠና ሰጥቷል::

ስልጠናው በቀጣይ ለሚሰጠው ዋናው ፈተና መደረግ ያለባቸውን ዝግጅቶች: የሚቀርቡ ይዘቶችን እና በፈተና ወቅት መከተል ያለባቸውን ሂደቶች የሚያመላክት እና ተፈታኞችን በሰነ ልቦናም ጭምር የሚያዘጋጅ እንደሆነ ተገልጿል::



መማር ማስተማር

ለከዳስተር ሲስተም ስማርት ሲቲ" ትግበራ



የከተማ አስተዳደር ጽ/ቤቱ "ለከዳስተር ሲስተም ስማርት ሲቲ" ትግበራ ባለሙያዎችን ለመቅጠር በዩኒቨርሲቲው ፈተና ሰጥቷል::

የሰመራ ሎጊያ አስተዳደር የከተማ አገልግሎት ፅ/ቤት ከከተማው አስተዳደር የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት እና ከሰመራ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ለከዳስተር ሲስተም ስማርት ሲቲ ትግበራ ብቁ ባለሙያዎችን ለመቅጠር ፈተና ሰጥቷል::

የዚህ ፈተና ዋና አላማ የሰመራ ሎጊያ ከተማ አስተዳደርን ዘመኑን በሚመጥን ጂጂታል ቴክኖሎጅ በመታገዝ ወደ ከዳስተር ሲስተም/smart city ለማዘመን በዘርፉ ብቃት ያለው የሰው ሀይል ለመመልመል መሆኑ ተገልጿል::

የተቋማቱ ከፍተኛ አመራሮች በተገኙበት ከ40 በላይ የሚሆኑ በተለያዩ የኢንጂነሪንግ እና ቴክኖሎጅ ትምህርት ዘርፎች የተመረቁ ወጣት ባለሙያዎች ፈተናውን ወስደዋል::

ዩኒቨርሲቲው ተአማኒነት ያለው የምዘና ሂደት እንዲኖር ሀላፊነቱን ወስዶ መምህራን ፈተናውን እንዲያዘጋጁ እና እንዲፈትኑ በማድረግ የበኩሉን ማህበረሰባዊ አስተዋጽኦ አበርክቷል::



መማር ማስተማር

CURRENT E-LEARNING INITIATIVES AND FUTURE ACTIONS

ዩኒቨርሲቲው Current E-Learning Initiatives and Future Actions በሚል ርዕሰ የውይይት መድረክ አካሄዷል።



ሰመራ ዩኒቨርሲቲ Current E-Learning Initiatives and Future Actions በሚል ርእሰ ለትምህርቱ ዘርፍ አመራሮች እና መምህራን የተዘጋጀ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ አካሂዷል።
በዚ ጉዳይ Student Success Suit (SSS) Course እና Master Class: Foundations in excellence for teaching online ትግበራ እና አፈጻጸምን በተመለከተ ውይይት ተካሂዷል።

የአካደሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚደንት ዶ/ር አብዱረህማን ከድር በመክፈቻ ንግግራቸው: በe-SHE initiative የተዘጋጁትን የ Capacity Building ኮርሶችን በመውሰድ እና በዩኒቨርሲቲያችን በማስተርካርድ ፋውንዴሽን እና በትምህርት ሚኒስቴር ትብብር ተገንብቶ በቅርቡ የሚመረቀውን multimedia studio በመጠቀም ወደፊት ስፊ ስራ መስራት እንደሚጠበቅ እና በትኩረት እንደሚሰራበት አብራርተዋል።



መማር ማስተማር

የሥርዓተ-ትምህርት ዝግጅት ክለሳ ሂደት ግምገማ ተካሄደ

በሰመራ ዩኒቨርሲቲ አካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዝዳት ያዘጋጀው የሥርዓተ-ትምህርት ዝግጅት ክለሳ ሂደት ግምገማ አካሂዷል።



ግምገማው ዩኒቨርሲቲው ወደ ተግባር ተኮር ዩኒቨርሲቲ (Applied Science University) ለሚያደርገው ሽግግር ከባለፈው አመት ጀምሮ በትኩረት መሰክ (ግብርና፣ ቱሪዝምና ማዕድን) ያሉ 10 ፕሮግራሞችን ከተግባር ተኮር ዩኒቨርሲቲ መለኪያዎች እንድሁም ከኢንዱስትሪዎች ፍላጎት አንጻር ሲያዘጋጀው የቆየውን የሥርዓተ-ትምህርት ዝግጅት ክለሳ ሂደት ያለበትን ሁኔታ በማወቅ የተሻለ አፈጻጸም እንዲኖር ለማስቻል ያለመ መሆኑ ተገልቷል።

በመርሃ ግብሩም የሥርአተ ትምህርት ዝግጅት ክለሳ ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ከትምህርት ክፍሎች የተውጣጡ የዩኒቨርሲቲው መምህራን የተሳተፉ ሲሆን በእያንዳንዱ የሥርዓተ-ትምህርት ዝግጅት ክለሳ ሂደት ላይ የተዘጋጀው ጽሁፍ ቀርቦ ውይይት ተካሄዶበት በአስፈላጊነቱ ላይ ገንቢ አስተያየት ተሰጥቷል።

በመጨረሻም ሥርአተ ትምህርት ክለሳው በተባለው ጊዜ እንዲጠናቀቅ ቀጣይ ሥራዎችን በትኩረት መሥራት እንደሚገባ ተመላክቷል።



Samara University
2024/25
Annual Magazine
Third Edition ሦስተኛ ዕትም
የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

መማር ማስተማር

በዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ላይ የአቅም ግንባታ ሰልጠና



በስመራ ዩኒቨርሲቲ አካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዝዳት ያዘጋጀው በስመራ ዩኒቨርሲቲ የፈተና ማእከል ዳይሬክቶሬት ከጤናና ህክምና ሳይንስ ኮሌጅ ጋር በመተባበር የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ሰልጠና መርሃ ግብር አካሂዷል። የሥርዓተ-ትምህርት ዝግጅት ክለሳ ሂደት ግምገማ አካሂዷል።

ይህ ሰልጠና ከአምሬፍ ሄልዝ አፍሪካ እና ከጃፒዬጎ ጋር በመተባበር በተለያዩ ክፍሎች ውስጥ የመምህራንን እና የሰራተኞችን አቅም ለማሳደግ ያለመ ነው። ቁልፍ ርዕሶች ማዋቀርን፣ የተጠቃሚ አስተዳደርን፣ የይዘት አስተዳደርን፣ የሰርዓት ጥገናን፣ መላ ፍለጋን፣ እና ተስኪዎችን እና የሶስተኛ ወገን መሳሪያዎችን ማቀናጀትን ያካትታሉ።

ከጤናና ህክምና ሳይንስ ኮሌጅ መምህራን፣ የኮሌጆች ምክትል ዲኖች፣ የጥራት ማሻሻያ ባለሙያዎች፣ የኮምፒውተር ላብራቶሪ አስተዳዳሪዎች፣ የአይሲቲ ኔትዎርክ እና ሲስተም አስተዳደር ስፔሻሊስቶች፣ የኢ-ትምህርት አመቻቾች እና የፈተና ማእከል ዳይሬክቶሬት ሰራተኞች ሰልጠናውን ተሳትፈዋል።



መማር ማስተማር

Udacity's 5 Million Coders Initiative - Samara university

በመቀጠልም ዩኒቨርሲቲው በኢትዮጵያ መንግስት እና በተባበሩት አረብ ኢምሬቶች መካከል የተደረገውን የ5 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ኮድደር ኢኒሼቲቭ ትብብር በኢትዮጵያውያን መካከል አጠቃላይ የኢንተርኔት ማስልጠኛ ኘሮግራሞችን የዲጂታል ክህሎትን ለማሻሻል ያለመ በይፋ ጀምሯል።



ተማሪዎች እና የማህበረሰብ አባላት ለ Udacity የሥልጠና መርሃ ግብሮች በ ethiocoders.et ድህረ ገጽ በኩል እንዲመዘገቡ እናበረታታለን ይህም ጠቃሚ የምስክር ወረቀቶችን ለማግኘት እና የሰራ እድላቸውን ያሳድጋል።

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ Udacity's 5 Million Ethiopian Codeers ተነሳሽነት ከመጀመሩ ጎን ለጎን የተማሪዎች ሰኬት ሰዊት (ኤስኤስኤስ) እና የማስተር ክላሰ፡ ፋውንዴሽን ኢን ልቀንስ ፎር ቲቺንግ ኦንላይን (ኤምሲቲ) ኮርሶችን በጥልቀት ገምግሟል።

ዩኒቨርሲቲው በ e-Learning for Strengthing Higher Education (e-SHE) ተነሳሽነት፣የማስተር ክፍል ማስልጠኛ (MCT) ኮርሶችን ለአስተማሪዎች እና የተማሪ ሰኬት ሰዊት (ኤስኤስኤስ) ኮርሶችን ለተማሪዎች በመሰጠት ላይ ነው።

ኤስኤስኤስ የተነደፈው ተማሪዎችን ለመደገፍ ሲሆን ኤምሲቲ ግን የመምህራንን ክህሎት ማሳደግ ላይ ያተኩራል፣ ሁለቱም ቡድኖች ከትምህርታዊ አቅርቦቶች ተጠቃሚ መሆናቸውን ያረጋግጣል።
በግምገማው ወቅት የኮርሱን ሂደት ለመገምገም እና ለተሳታፊዎች የወደፊት መመሪያን ለመወሰን ውይይቶች ተካሂደዋል።



መማር ማስተማር

ለሕግ ት/ርት ቤት ተማሪዎች ስልጠና ሰጠ።

የኢትዮጵያ ህግ ትምህርት ቤቶች ማህበር በግጭት አፈታት እና ሁከት መከላከል ላይ ያተኮረ ስልጠና ለሰመራ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ት/ርት ቤት ተማሪዎች ሰጥቷል።





የኢትዮጵያ ህግ ትምህርት ቤቶች ማህበር ፕሮጀክቱን The International Foundation for Electoral Systems እና USAID የደገፉት መሆኑን ገልጾ ይህንን ተነሳሽነት ወደ ሌሎች ዩኒቨርሲቲዎችም ለማስፋፋት ማቀዱን አመላክቷል።

ይህ ለ20 የህግ ተማሪዎች የተሰጠው የ4 ቀን ስልጠና ተማሪዎቹ በሁከትና ግጭት አፈታት ዘዴዎች ላይ ያተኮሩ ትንንሽ ፕሮጄክቶችን እንድነድፉ የሚያግዝ ሲሆን በቀጣይ ስልጠናውን ለሁሉም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በተለይ ተፅዕኖ ፈጣሪ ሰዎችን በማሳተፍ ለመሰጠት እንዳቀደ ማህበሩ ገልጿል።



መማር ማስተማር

የቲካ መሪን ጋር የትብብር ተነሳሽነት ላይ ውይይት አድርጓል።

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ኤች.ኢ. በኢትዮጵያ የቱርክ ትብብርና ማስተባበሪያ ኤጀንሲ (ቲካ) ኃላፊ ሚስተር ኤነቨር ሬሱሎጉላሪ የማህበረሰብ ደህንነትን እና የትምህርት ግብአቶችን በማሳደግ በትብብር ሊሰሩ በሚችሉ ፕሮጀክቶች ላይ ውጤታማ ውይይት አድርጓል።



ሚስተር ኤነቨር እና በዶክተር መሀመድ ኡስማን (ፕሬዝዳንት) የሚመራውን የእንስሳት እርባታ ቦታ፣ ዲጂታል ላይብረሪ፣ እየተካሄደ ያለውን ጂምናዚየም፣ የሰራተኞች መኖሪያ፣ የአፋር ታለንት አካዳሚ እና የሬዶ የባህል ማዕከልን ጨምሮ ቁልፍ የዩኒቨርሲቲ ፕሮጀክቶችን ጎብኝተዋል።

ዶ/ር መሀመድ ከጉብኝቱ በኋላ በዩኒቨርሲቲው ጅምር ላይ ሰፊ ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን እንደ ምሁር (በሳማራ ዩኒቨርሲቲ እና በቱርክ ተቋማት መካከል ያሉ የሰራተኞች እንቅስቃሴ) በግብርና፣ ጂኦሎጂ እና የእንስሳት እርባታ ዘርፍ፣ የሰፖርት ጂምናዚየምን ጨምሮ ሌሎች በርካታ የትብብር ዕድሎችን ዘርዝረዋል።

ይህ ጉብኝት በክልሉ የማህበረሰብ ልማት እና የትምህርት ልቀት ለማሳደግ በጋራ ቁርጠኝነት በሰመራ ዩኒቨርሲቲ እና በቲካ መካከል ያለውን አጋርነት ለማጠናከር ትልቅ እርምጃ መሆኑ አመላክቷል።



Samara University
2024/25
Annual Magazine
Third Edition ሦስተኛ ዕትም
የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

መማር ማስተማር

ዘመናዊ የእንስሳት እርባታ ፋርም

ከእንስሳት እርባታ ውጤታማነት ጋር በተገናኘ በወተት ላም የምርት ጥራትና ብዛት፣ የእንስሳት መኖ አዘገጃጀት፣ ከእንስሳት ተረፈ ምርት ባዩ ጋዝ ማምረት፣የገቢያ ትስስር መፍጠር፣ ቴክኖሎጅን ተጠቅሞ መሥራት ፣ የእካባቢውን ሕብረተሰብ ተጠቃሚ ማድረግ በሚሉ ጉዳዩች ላይ የድርጅታቸውን ተሞክሮዎች አቶ እስክንድር አካፍለዋል::



ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ደረዳውን የጠበቀ ዘመናዊ የእንስሳት እርባታ ፋርም በግቢ ውስጥ ለመጀመር አስፈላጊ ዝግጅቶችን አጠናቆ ወደ ሰራ ለመግባት በትኩረት እየሰራ መሆኑ ተገልጿል።



በመድረኩ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚደንት ዶ/ር መሀመድ ኡስማን እንደገለጹት ክልሉ በእንስሳት ሀብት የታወቀ እና ምቹ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው ዘርፉን አዘምኖ ለማህበረሰብ በሚጠቅም መልኩ የሚታዩ ውስንነቶችን በምርምር አሟልቶ ለመስራት ግብርናን አንዱ የትኩረት አቅጣጫው አድርጎ በመያዙ ይህ የእንስሳት እርባታ ፋርም እና የመኖ ማምረቻ ማሳ የዝግጅት ሰራ መገባደድ ጥሩ እመርታ መሆኑን አብራርተዋል ።

የእንስሳት ፋርሙ ለመጠናቀቅ መቃረቡን ተከትሎ ዩኒቨርሲቲው በእንስሳት እርባታ እና የወተት ምርት ላይ የተሰማሩትን የ ANAN Agro Industry ባለቤት እና መሰራች የሆኑትን አቶ እስክንድር ዮሴፍን በመጋበዝ ለእንስሳት ህክምናና ሳይንስ ኮሌጅ መምህራን እና ተማሪዎች ልምድ እንዲወስዱ አድርጓል።

የእንስሳት እርባታ ፋርሙ በወተት ላሞች እና ፍየሎች እርባታ ሰራውን እንዲጀምር በትኩረት እየተሠራ እንደሆነና : ይህም በቀጣይ ለማሰተማሪያነት: ለምርምር : ለገቢ ማመንጫነት እንዲሁም ከዘመናዊ እና ከአካባቢው የተመረጡ እንሰሳትን ለይቶ ወደ ፋርሙ በማሰገባት ለማህበረሰብ ግብአት የሚሆኑ የጥናት ግኝቶችን ለማቅረብ የሚያስችል መሆኑን የእንስሳት ህክምናና ኮሌጅ ዲን ዶ/ር መሀመድ ሀሚድ ገልጸዋል::



Samara University
2024/25
Annual Magazine
Third Edition ሦስተኛ ዕትም
የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

መማር ማስተማር

የተቋምና የአካዳሚክ ፕሮግራም ዕውቅና አሰጣጥ” ላይ ሰልጠና ተሰጥቷል



የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ለአካዳሚክ ባለሙያዎች ተቋማዊ እና አካዳሚክ ኘሮግራም እውቅና ላይ ያተኮረ አጠቃላይ ሰልጠና በመጀመር የአካዳሚክ ፕሮግራሞቹን ጥራት ለማሳደግ ያለመ ነው።

ሰልጠናው በከፍተኛ ትምህርት የጥራት እና የጥራት ማረጋገጫ፡ ፅንሰ-ሀሳቦች እና ተግባራት፣ ውጤት ላይ የተመሰረተ ትምህርት፣ የእውቅና ሂደት እና የእውቅና ደረጃዎች፣ የእውቅና መረጃ ምንጮች፣ ሰልጣኞች የአካዳሚክ እውቅና ውሰብሰብ ጉዳዮችን እንዲዳሰሱ የሚያስችል አስፈላጊ እውቀትን የመሳስሉ ርዕሶችን ይሸፍናል።

ከትምህርትና ሰልጠና ባለሰልጣን በተውጣጡ ባለሙያዎች የተመራው ዶ/ር ዱንካና ንጉሳ ምክትል ዋና ዳይሬክተር እና የከፍተኛ ትምህርት ፕሮግራም ዕውቅና ባለሙያ ፋሲካ ተመሰገን ሰልጠናውን ተሰጥቷል።

የኮሌጅ እና የትምህርት ቤት ዲኖች ፣ዳይሬክተሮች እና መምህራንን ጨምሮ የአካዳሚክ ባለሙያዎች የተሳተፉበት ሰልጠና ነው ።

ይህ ሰልጠና ዩኒቨርሲቲው ወደ ተግባር ተኮር ሳይንስ ዩኒቨርሲቲ ሲሸጋገር ደረጃቸውን የጠበቁ ሰርአተ ትምህርቶችን ለማዘጋጀት እና ለማሻሻል እንደሚረዳ ታምኗል።



መማር ማስተማር

የመሬት መንቀጥቀጥ ግንዛቤ አውደ ጥናት አካሂዷል



በመሬት መንቀጥቀጥ ግንዛቤ ዙሪያ ዩኒቨርሲቲው የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ምክትል ፕሬዝዳንት ጽህፈት ቤት ከመሬት ሳይንስ ትምህርት ቤት ጋር በመተባበር ያዘጋጀው ጉልህ አውደ ጥናት ተካሄዷል።

የመሬት መንቀጥቀጥ እንቅስቃሴን የመረዳትን አስፈላጊነት በማሳየት ከአገራዊ፣ ከክልላዊ እና ከዓለም አቀፍ የመሬት መንቀጥቀጥ ተሞክሮዎች በተወሰዱ እግባብነት ባላቸው ሰታቲስቲክስ የተደገፈ ነው።

በእውደ ጥናቱ በራ ስመራ ዩኒቨርሲቲ የጂኦሎጂ ትምህርት ቤት ገለጻ የተደረገ ሲሆን ባለፉት ሁለት ወራት ውስጥ ተከታታይ ተደጋጋሚ የመሬት መንቀጥቀጦች በተከሰቱበት በአዋሽ ፈንታሌ አካባቢ የተደረጉ ጥናቶችን፣ የመስክ ምልከታዎችን እና የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሰጨበጫ ሰራዎችን አጉልቶ አሳይቷል።



እውደ ጥናቱ ዕውቀትን ለመለዋወጥ እና በአካባቢው ባለድርሻ አካላት መካከል ትብብርን የሚያጎለብት መድረክ ሆኖ አገልግሏል፤

በመጨረሻም የተፈጥሮ አደጋዎችን በመጋፈጥ የበለጠ መረጃ ያለው እና ዝግጁ የሆነ ማህበረሰብ እንዲኖር አስተዋጽኦ አድርጓል።



Samara University
2024/25
Annual Magazine
Third Edition ሦስተኛ ዕትም
የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

መማር ማስተማር

ዩኒቨርሲቲው በኦፕን ጆርናል ሲስተም ላይ ስልጠና ሰጠ።



የሳማራ ዩኒቨርስቲ በኦፕን ጆርናል ሲስተም (OJS) ለአፋር-አፍ እና ሶሺዮሊንጉስቲክስ ጆርናል (JASL) ጆርናል ኦፍ ኤዲቶሪያል ቦርድ አባላት፣ የአይሲቲ ባለሙያዎች እና ከተለያዩ ኮሌጆች እና ትምህርት ቤቶች ለተመረጡ ሰራተኞች ስልጠና ሰጠ።

የጆርናል ኦፍ አፋር-አፍ እና ሶሺዮሊንጉስቲክስ (ጃኤስኤል) በተሳካ ሁኔታ እንዲጀመር እና ዘላቂነቱን እንዲቀጥል በማገዝ ተሳታፊዎችን የኦጄኤስ መድረክን ለማስተዳደር የሚያስፈልጉትን ክህሎቶች ለማስታጠቅ ያለመ ነበር።



Samara University
2024/25
Annual Magazine
Third Edition ሦስተኛ ዕትም
የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

ምርምር የሥራ ክንውን

የአቅም ግንባታ የክትትል መርሃ ግብር የመነሻ ውጤት ሰርጭት አውደ ጥናት



የአቅም ግንባታ የክትትል መርሃ ግብር የመክፈቻ እና የመነሻ ውጤት ሰርጭት አውደ ጥናት በሰመራ አፋር ክልል ተካሄደ።

የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የአፋር ክልል ጤና ጥበቃ ቢሮ፣ የሰመራ ዩኒቨርሲቲ እና የጎንደር ዩኒቨርሲቲ በትብብር የአቅም ግንባታ የክትትል መርሃ ግብር የከፈቱ ሲሆን የጤና መረጃ ሰርዓት (ኤችአይኤስ) የመነሻ ውጤት ሰርጭት አውደ ጥናት በአፋር ክልል ሰመራ ከተማ አካሂደዋል።

ዝግጅቱ በአራቱም ተቋማት መካከል የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርሟል።

የሲቢኤምፒ (CBMP) የዳሰሳ ጥናት ውጤቱን መሰረት አድርጎ የሚተገበር ሲሆን በክልሉ የተመረጡ ሞዴል ወረዳዎችን በመፍጠር የቴክኒክ ድጋፍ ለማድረግ ያለመ ነው።

ይህ ተነሳሽነት የጤና መረጃ ሰርዓቱን ወደ ዲጂታላይዜሽን ከማድረግ በተጨማሪ ለ ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ተግባራዊ የጤና ሳይንስ ልምድን ይሰጣል እንዲሁም የሴቶችን ጨምሮ የጤና ባለሙያዎችን አቅም ይገነባል።



ምርምር የሥራ ክንውን

ለክልሉ የጤና መረጃ ባለመያዎች የአቅም ግንባታ ሰልጠና



ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ከ4 ወረዳዎች ለተውጣጡ የጤና ጣቢያ የመረጃ ባለሙያዎች Health Information System (HIS) የጤና መረጃ አያያዝ ሰርዓት ላይ ያተኮረ የአቅም ግንባታ ሰልጠና ሰጥቷል::

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ የምርምር እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ተ/ም/ ፕሬዚደንት አቶ አደም አሊ እንደገለፁት ባለፈው አመት ግንቦት ላይ የሰመራ እና የጎንደር ዩኒቨርሲቲዎች ከጤና ጥበቃ ሚኒሰቴር እና የአፋር ክልል ጤና ቢሮ ጋር በጋራ ለመሰራት የተፈራረሙትን የመግባቢያ ሰምምነት ወደ ተግባር የሚቀይሩ ሰራወች መጀመራቸውን አብራርተዋል::



በዚህ ፕሮጀክት የታቀፉ ወረዳዎች ሚሌ፣ተላላክ ፣ ጭፍራ እና ሰመራ-ሎጊያ መሆናቸውን ጠቅሰው በእነዚህ አካባቢዎች የሚገኙ የ 12 ጤና ጣቢያዎች ባለሙያዎች በሰልጠና የቀሰሙትን እውቀት አተገባበር ላይ ክትትል እና ድጋፍ የማድረጉ ሰራ እንደሚቀጥል ተናግረዋል::

ይህን የትብብር ፕሮጀክት ሰመራ ዩኒቨርሲቲ በባለቤትነት ይዞ የሚያሰቀጥለው ሲሆን:የክልሉን የጤና መረጃ ሰርዓት (HIS) ለማዘመን የባለሙያዎችን አቅም የመገንባት የመከታተል እና የመደገፍ Capacity Building Monitoring Program (CBMP) አላማ አንግቦ የሚተገበር የማህበረሰብ አገልግሎት መሆኑም ተጠቅሷል::

ምርምር የሥራ ክንውን በ3 ወረዳዎች የአረንጓዴ አሻራ መርሀ-ግብር ንቅናቄን



ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ሀገራዊ የአረንጓዴ አሻራ መርሀ-ግብር ንቅናቄን በ3 የአፋር ክልል ወረዳዎች ማለትም ወሰማ ፣አብአላ እና ኮነባ አድርጓል::

ዩኒቨርሲቲው ችግኞችን ለአብአላ ፣ ወሰማ እና ለገረኒ ወረዳዎች በዚህም ከ2ሺ በላይ ችግኞችን ተደራሽ ማድረግ ተችሏል::

ለሀገራዊ የአረንጓዴ አሻራ መርሀ-ግብሩ እየተከፋፈሉ ያሉት ችግኞች ለምግብነት የሚውሉ የፍራፍሬ ችግኞች ሲሆኑ ይህም የተፈጥሮ ሚዛንን ከማሰጠበቅ ባለፈ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ የማህበረሰቡን ገቢ የሚደግፉ መሆናቸው ተገልጿል::

በዩኒቨርሲቲው በምርምር እና ቴክኖዎሎጂ ሽግግር ም/ፕሬዚደንት አደም አሊ የሚመራው የዩኒቨርሲቲው አመራሮች እና ባለሙያዎች ቡድን በኮነባ ከወረዳው አመራሮች እና ማህበረሰቡ ጋር በመሆን አረንጓዴ አሻራውን አኑሯል::



ምርምር የሥራ ክንውን

የዩኒቨርሲቲው ደረጃ 1ኛ ዙር ሴሚናር ማቅረቢያ አውደ ጥናት



የሰመራ ዩኒቨርሲቲ የምርምር፣ ሕትመት፣ ሰነ-ምግባር እና ሰርፀት ዳይሬክቶሬት በዩኒቨርሲቲ ደረጃ 1ኛ ዙር የምርምር ሴሚናር አቀራረብ አውደ ጥናት አካሂዷል።

በይህ ወርክሾፕ በዚህ የትምህርት ዘመን ሊካሔድ ከታቀዱት አራት የምርምር ሴሚናር ገለጻ አውደ ጥናቶች የመጀመሪያው መሆኑን ዛሬው የምርምር ሴሚናር ማቅረቢያ አውደ ጥናት አምስት የምርምር ፕሮጀክቶች ቀርበዋል።

የምርምር ሴሚናር ማቅረቢያ አውደ ጥናት አምስት የምርምር ፕሮጀክቶች ቀርበዋል። የአውደ ጥናቱ አላማ ተመራማሪዎች ሰራቸውን የሚያቀርቡበት መድረክ መፍጠር፣ በተሳታፊዎች መካከል የአስተያየት ልውውጥ እና ሀሳብ መለዋወጥ እና ለወደፊት የምርምር ሰራዎች መሰረት መመሰረት ነው።

የዩኒቨርሲቲው በተግባራዊ ሳይንሶች የላቀ ብቃትን የማስተዋወቅ እና የአካዳሚክ ዝናውን ለማሳደግ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ በሚያበረክቱበት ወቅት ተሳታፊዎች በዘመናዊ የምርምር ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ጠቃሚ ግንዛቤዎችን ያገኛሉ።



Samara University
2024/25
Annual Magazine
Third Edition ሦስተኛ ዕትም
የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

ምርምር የሥራ ክንውን

በአዋሽ ፈንታሌ ወረዳመሬት መንቀጥቀጥ ተከሰተ

የመሬት መንቀጥቀጥ ከምድር የፈለቀውን ውሃ በጥናት ምንነቱ እስኪጣራ መጠቀም እንደማይገባ በሰመራ ዩኒቨርሲቲ የሰነ ምድር ትምህርት ክፍል አሰገነዘበ።

በአዋሽ ፈንታሌ ወረዳ ሳቡሬ ቀበሌ የተከሰተውን የመሬት መንቀጥቀጥ ተከትሎ የዩኒቨርሲቲ ምሁራን ወደ ቦታው በማምራት ምልከታ በማድረግ ማብራሪያ ሰጥተዋል።



በተደጋጋሚ የተከሰተው ይህ የመሬት መንቀጥቀጥ በሬክተር ስኬል 4 ነጥብ 9 የተመዘገበበት መሆኑም ተገልጿል።

በዩኒቨርሲቲው የሥነ ምድር ትምህርት ክፍል ሃላፊ ጌታቸው ገብረፃድቃን በበኩላቸው፤የመሬት መንቀጥቀጡ ከሰሞኑ በአዋሽ ፈንታሌ ወረዳ ሳቡሬ በተሰኘ ቀበሌ ለአራት ጊዜያት የተከሰተ መሆኑን ገልጸዋል።

በምልከታ እንዳረጋጡት እስከ አንድ ነጥብ አምስት ሜትር የመሬት መሰንጠቅ እንደተከሰተ መመልከታቸውን አሰረድተዋል።

ምልከታ ያደረገው ቡድኑ ባገኘው መረጃ እስከ አዲሰ አበባ ድረስ የተሰማ ንዝረት ያለው የመሬት መንቀጥቀጥ መፈጠሩን አረጋግጠው፤በዚህም በዱለቻ ወረዳ ፍል ውሃ ከታች ይዞ የመውጣት ክሰተት መፈጠሩን ገልጸዋል።

በአሁኑ ወቅት በሰፍራው ያሉ ማህበረሰቦች ወደ ሌላ ቦታ መኖሪያቸውን ማዛወር እንደሚጠበቅ አመልክተው፤የቅድመ ጥንቃቄ ሰራዎች በተከታታይ መሰራት እንደሚገባም ጠቁመዋል።

በዚሁ ትምህርት ክፍል መምህርና ተመራማሪ ዓሊ ሙሳ በበኩላቸው፤ ክሰተቱን ተከትሎ የተፈጠረው እንፋሎት እንደ ፀጋ ተወሰዶ ለቱሪዝምና ለጂኦተርማል ሃይል መጠቀም ይቻላል።



Samara University
2024/25
Annual Magazine
Third Edition ሦስተኛ ዕትም
የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

ምርምር የሥራ ክንውን

ዓመታዊ የምርምር ፕሮፖዛል ግምገማ አውደ ጥናት



ወርክሾፑ ከተግባራዊ ምርምር ተፈጥሮ እና የልህቀት ማእከል ጋር የተጣጣሙ የምርምር ሀሳቦችን በጥልቀት ለመገምገም ያለመ ነው።

በምርምር፣ ሕትመት፣ ሰነምግባር እና ሰርፀት ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀው አውደ ጥናቱ 29 ፕሮፖዛል አንድ ሜጋ፣ ሰባት ትልቅ እና 21 መካከለኛ ደረጃ ያለው ሲሆን የተሊያዩ የውጭ እና የውሰጥ ገምጋሚዎችን የሚያሳትፉ የምርምር ሰራዎችን ያሳያል።
አውደ ጥናቱ ለጠንካራ የግምገማ መድረክ ብቻ ሳይሆን በተመራማሪዎች፣ ገምጋሚዎች እና ሰራተኞች መካከል የእውቀት እና የልምድ ልውውጥን ለማበረታታት ያገለግላል።



ምርምር የሥራ ክንውን

ዩኒቨርሲቲው የፍራፍሬ ግብርና ምርት

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ከሶሰት አመታት ወዲህ በግብርና: በማዕድን እና በቱሪዝም መስኮች ላይ የልህቀት ማእከል ለመሆን በትኩረት እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል።



በማዕከሉ ካለው ብርቱካን አምና የተሻለ ምርት የተገኘበት እና ለሽያጭም ማቅረብ ተችሎ እንደነበር ገልፀው: ዘንድሮ በተለያዩ ምክንያቶች ምርቱ መቀነሰ እንደታየበት እና ይህን ክፍተት ለይቶ ለመሙላት በማለም በጥናት የተደገፈ የሰው ሀይል አደረጃጀት እና የአሰራር ለውጥ በማድረግ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን አብራርተዋል ።



ተቋሙ አፕላይድ ዩኒቨርሲቲ እንደመሆኑ መጠን ከመማር ማስተማር ሰራው ጎን ለጎን የምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት ተልዕኮውን ለመወጣት በጥናት የተደገፈ የማማከር እና የምርምር ውጤቶችን በግቢ ውስጥ በዱብቲ በአይሳኢታ እና ሌሎችም አካባቢዎች ባቋቋማቸው የሰርቶ ማሳያ ጣቢያዎች በማባዛት ለህብረተሰቡ እያደረሰ እንደሚገኝ የምርምር እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ተ/ም/ ፕሬዚዳንት አቶ አደም አሊ ገልጸዋል::

የግብርና የምርምር ማዕከላት አላማ የዩኒቨርሲቲው መምህራን እና ተማሪዎች ከአመት እስከ አመት የሚሰሯቸውን የምርምር ውጤቶች ለማህበረሰቡ በማሰረፅ የእውቀት ሽግግር እንዲያደርጉ ማስቻል መሆኑም ተገጿል::



ምርምር የሥራ ክንውን

የምርምር ህግና ስነ-ምግባር አቅም ግንባታ ሰልጠና



በሠመራ ዩኒቨርሲቲ በምርምር ስነ-ምግባር ላይ ያተኮረ የአቅም ግንባታ ሰልጠና በመሰጠት ላይ ሰጥቷል።

ዩኒቨርሲቲው ተግባራዊ የሚሆኑ እና የማህብረሰቡን ችግር በዘላቂነት የሚፈቱ ምርምሮች በትኩረት መስኩ ማለትም በግብርና፣ በማዕድን እና ቱሪዝም ላይ እንድሰሩ ስለሚያስፈልግ ሰልጠናው ለተመራማሪዎች የምርምር ስነ-ምግባር እና ህግን ጠበቀው ምርምር ለመሰራት እንደሚያግዝ ተመላክቷል።



ሰልጠናው በዩኒቨርሲቲው እስካሁን በሚሰሩ ምርምሮች ላይ በሰፋት የሚታዩ የምርምር ስነ-ምግባር ክፍተቶችን ለመሙላት ያስችላል ተብሏል::

ሰልጠናውን የምርምር ህትመት፣ ስነ-ምግባር እና ሰርፀት ዳይሬክቶሬት ያዘጋጀው ሲሆን ከሁሉም ኮሌጆች እና ትምህርት ክፍሎች የተውጣጡ መምህራን እየተሳተፉበት ይገኛል::



ምርምር የሥራ ክንውን የቴክኖሎጂ ሽግግር ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ግምገማ አውደ ጥናት



የሰመራ ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ሽግግር ፕሮፖዛልን ለመገምገም አመታዊ አውደ ጥናት በማካሄድ በህብረተሰቡ ላይ ሊኖራቸው የሚችለውን ተፅእኖ እና አዋጭነታቸውን የሚያጎሉ ስድስት ሀሳቦችን ገምግሟል።

የቀረቡትሀሳቦች በማህበረሰቡ አባላት ህይወት ላይ ትርጉም ያለው ለውጥ ለማምጣት የተነደፉ ተግባራዊ መፍትሄዎችን ለማቅረብ ያለመ ነው።



የምርምርናቴክኖሎጂ ሽግግር ምክትል ፕሬዝዳንት ሚስተር አደም አሊ እንደገለፁት የእነዚህ ጅምሮች የመጨረሻ ግብ በመድገም በህብረተሰቡ ውስጥ እንዲሰራጭ በማድረግ ኑሮን ማሻሻል ነው።



ምርምር የሥራ ክንውን

ዩኒቨርሲቲው የጥናት ውጤቱን ለመጋሌ ወረዳ አስረክቧል

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ከመጋሌ ወረዳ ጋር በነበረው ሰምምነት መሰረት በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት በወረዳው የደረሰዉን ጉዳት እና መልሶ ለመቋቋም የሚያስፈልገውን ግብአት (Damages, Loose and Needs Assessment) በሳይንሳዊ ዘዴ ጥናት አድርጎ ዉጤቱን ለወረዳዉ አስረክቧል።



ጥናቱን የተካሄደው ዩኒቨርሲቲው ከመጋሌ ወረዳ ጋር በነበረዉ ሰምምነት መሰረት የተመራማሪወች ቡድን አቋቁሞ ለአንድ አመት ያህል ሲያሰጠና የነበረውን በማጠናቀቅ ነው።

የጥናቱን የመጨረሻ ቅጂ የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ተ/ም ፕሬዚዳንት አቶ አደም አሊ ለመጋሌ ወረዳ አስተዳደር ተወካዮች አቶ አብዱ ሸክበራ እና እንድሪስ ፈረደ አስረክበዋል።

በርክክቡ ወቅት ለዚህ ፕሮጀክት መሳካት የተጉ የጥናት ቡድን አባላትን እና በመስክ ሰራው ለነበረው ተነሳሽነትና ያላሰለሰ ድጋፍ የመጋሌ ወረዳ አስተዳደርንና ማህበረሰብን አቶ አደም አመሰግነዋል።
በቀጣይም በወረዳው በተለያዩ የማህበረሰብ አገልግሎት ሰራዎች በጋራ እንደሚሰሩ ገልፀዋል።



Samara University
2024/25
Annual Magazine
Third Edition ሦስተኛ ዕትም
የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

ምርምር የሥራ ክንውን

የማህበረሰብ ትስስርን ለዘላቂ ልማት እና ሰላም ማጠናከር



የሰላም ተነሳሽነት በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ፣ በሳማራ ዩኒቨርሲቲ እና በአፍሪካ ቀንድ አርብቶ አደርና አካባቢ ጥበቃ መረብ (PENHA) መካከል በጋራ በመሆን በአፋር እና በትግራይ ማህበረሰቦች መካከል ዘላቂ ሰላም፣ መረጋጋት እና አጋርነት ለመፍጠር ያለመ ነው።

በአካባቢ ጥበቃ ሰላምን ለማሰፈን በጋራ ያላቸውን ቁርጠኝነት በማሳየት ችግኝ በመትከል ላይ ተሰማርተዋል። የዝግጅቱን የትብብር መንፈስ በማጠናከር የግንቦት ሸጉላ መሰኖ ፕሮጀክትን በመጎብኘት እና በAARIC ተጨማሪ ውይይት በማድረግ ቀኑ ተጠናቋል።

ይህ ጅምር በህብረተሰቡ መካከል ዘላቂ ልማትና ሰምምነትን ከማሰፈን አንፃር ያለውን ፋይዳ በማጉላት የሀገር ሽማግሌዎች የመዝጊያ ንግግር አድርገዋል።

የ Trees4Peace ተነሳሽነት በአካባቢው የጋራ ልማትን እና ዘላቂ ሰላምን ለማምጣት ወሳኝ እርምጃን ያሳያል, በቀጣይ የህብረተሰቡን ተሳትፎ እና የአካባቢን ዘላቂነት ለማጎልበት የታቀደ ተጨማሪ ተግባራት.

ይህ የፍራፍሬ ዛፎችን የመትከል ዘመቻ በሰዎች መካከል መተማመንን እና ትብብርን ለማጎልበት የተነደፈውን ሰፊ እንቅስቃሴ መጀመሩን ያመለክታል።

ተከላው የተካሄደው በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ አባላ ግብርና ምርምርና ኢኖቬሽን ማዕከል ሲሆን በሰመራ ዩኒቨርሲቲ ከአካባቢው ወረዳ እንስሳት እርባታና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽህፈት ቤት ጋር በመተባበር በተዘጋጀው ቦታ ላይ ነው።



Samara University
2024/25
Annual Magazine
Third Edition ሦስተኛ ዕትም
የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

ምርምር የሥራ ክንውን

ተንቀሳቃሽ የእንስሳት ህክምና አገልግሎት

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ በባለፉት አመታት ለአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ ሲሰጠው የነበረውን የተንቀሳቃሽ እንስሳት ህክምና አገልግሎት (Mobile Veterinary Service) በዱብቲ ወረዳ መሰጠቱን ቀጥሏል።



የተንቀሳቃሽ እንስሳት ህክምና አገልግሎት አላማ ማህበረሰቡ ጤናማ እንስሳት እንዲኖሩት እና ከእንስሳት ሀብታቸው ተገቢውን ጥቅም ማግኘት እንዲችሉ ማገዝ ነው::



በዱብቲ ወረዳ ያነጋገርናቸው የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች እና የወረዳ የእንስሳት ህክምና ባለሙያ እንደገለጹት ከሆነ: ከአየር ፀባይ መቀያየር ጋር በተያያዘ እንስሳቱን የተለያዩ በሽታዎች እያጋጠሟቸው እንደሆነና: ዩኒቨርሲው ባለሙያ እና መድሀኒት መድቦ: ወቅቱን የጠበቀ አገልግሎት በመሰጠቱ ምስጋናቸውን ገልጸዋል::



ምርምር የሥራ ክንውን

የዳጉ ኢንተርናሽናል ጆርናል አዳዲስ መጣጥፎችን አሳትሞ

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ሰምንት ኦሪጅናል የጥናት ጽሑፎችን የያዘ የዳጉ ኢንተርናሽናል ጆርናል ኦፍ መሰረታዊ እና አፕላይድ ጥናት ቅጽ 6 ቁጥር 2 መውጣቱን በኩራት ያስታውቃል። ይህ የቅርብ ጊዜ እትም የመጽሔቱ የአካዳሚክ ምርምር እና የእውቀት ሰርጭትን ለማራመድ ያለውን ቁርጠኝነት ያሳያል።



የሰመራ ዩኒቨርሲቲ የዳጉ ኢንተርናሽናል ጆርናል መሰረታዊ እና የተግባር ጥናት (DIJBAR) አዳዲስ መጣጥፎችን አሳትሞ ዋና ዋና የመረጃ ጠቋሚዎችን ማሳካት ችሏል።

ጆርናሉ በሚያሳየው እድገት በአካዳሚክ ማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ጽሑፉን የመታየት መጨመር እና ተደራሽነት በማጎልበት በአፍሪካ ጆርናል ኦንላይን (AJOL)https://www.jol.info/index.php/dijbar እና የአፍሪካ ምርምር ጆርናሎች (AFJUR) ተጠቁሟል።

እነዚህ ግኝቶች ለጥናት መጽሔቱ ጠቃሚ የሆነ እድገትን ያመለክታሉ፣ ይህም የጆርናሉን ሰም በአፍሪካ እና በሌሎችም ላሉት ተመራማሪዎች ጠቃሚ ግብአት ነው።



Samara University
2024/25
Annual Magazine
Third Edition ሦስተኛ ዕትም
የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

ምርምር የሥራ ክንውን የ1 ሚሊዮን ተምር ልማት ትልቁን የምርምር እና የምርት ማዕከል



ሰመራ ዩኒቨርሲቲ በባለፉት አመታት ለአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ ሲሰጠው የነበረውን የተንቀሳቃሽ እንስሳት ህክምና አገልግሎት (Mobile Veterinary Service) በዱብቲ ወረዳ መሰጠቱን ቀጥሏል።

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ በአይሳኢታ የተቀናጀ የግብርና ምርምር ማዕከል በ2ሺ 500 ሄክታር መሬት ላይ በቀጣይ 3 አመታት የእንሰሳት መኖ ያመርታል: ከ8-10 ባለው አመት ውስጥ ደግሞ 1 ሚሊዮን ተምር በማልማት በሀገራችን ትልቁን የምርት እና የምርምር ማዕከል እውን እናደርጋለን" ሲሉ የሠመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር መሐመድ ኡስማን ትናንት ለኢዜአ በሰጡት ቃለመጠይቅ ገልጸዋል::

ይህ ፕሮጀክት የአዋሽን ወንዝ ከ6 ኪሜ ርቀት ላይ የመጥለፍ ስራው የተገባደደ ሲሆን: ሌሎች የግብርና መሰረተ ልማቶች ከ70 በመቶ በላይ ተከናውኗል::
የተምር ምርት በአፋር ክልል አይሳኢታና አፋምቦ ወረዳዎች በግለሰቦች እና በማህበራት ደረጃ ለብዙ አሰርት አመታት እየተሰራበት ያለ ቢሆንም: በዘርፉ አንቱታን ያተረፉ አለም አቀፍ የምርምር ተቋማት እና ባለሀብቶች ጋር በመተባበር በምርምር እና በቴክኖሎጂ የታገዘ የተምር ግብርናን እውን ለማድረግ ከተደረጉ ጥረቶች ውስጥ ከሞሮኮ:ሳኡድ አረቢያ:ኩዌይት ኤምባሲዎች ጋር የተጀመሩ ግንኙነቶች አሉ::



ዲጂታል ቴክኖሎጂ ሽግግር የብቃትና ሰው ሃብት አስተዳደር መተግበሪያ ሲስተም ሰልጠና



ሰልጠናው የብቃትና ሰው ሃብት አስተዳደር ሰራተኞች አዲሱን መተግበሪያ ለመጠቀም የሚያስችል በተግባር የተደገፈ እንደሆነ ተጠቁሟል።

በሰመራ ዩኒቨርሲቲ የብቃትና ሰው ሃብት አስተዳደር ሥራ አስፈፃሚ ያዘጋጀው የሰው ሃብት አስተዳደር መተግበሪያ ሥርዓት (system software) ሰልጠና ለክፍሉ ሰራተኞች ተሰጥቷል::

ዩኒቨርሲቲው እስከ ዛሬ ድረስ በርካታ አገልግሎቶቹን ወደ ዲጅታል ሲስተም የቀየረ ሲሆን የሰው ሃብት አስተዳደር መተግበሪያ ዘመኑን የዋጀ እና በወረቀት የሚሰጡ አገልግሎቾችን ወደ ኮምፒውተር ሲስተም በመቀየር አጠቃላይ አሰራሮችን የሚያዘምን እና የሚያቀላጥፍ መሆኑ ተገልጿል።

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚደንት ዶ/ር መሀመድ ኡስማን በሰልጠናው ማጠቃለያ ላይ ሥራ አስፈፃሚው ይህን ሰልጠና ማዘጋጀቱ የሚበረታታ እንደሆነ ገልፀው መተግበሪያው ለተቋሙም ሆነ ለሰራተኞች የተሻለ አገልግሎት ለመሰጠት እና መረጃን በጥንቃቄ ለመያዝ የሚያግዝ በመሆኑ መተግበሪያውን በአግባቡ መጠቀም እንደሚያስፈልግ አሰገንዝበዋል።

ሰልጠናው ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲ በተጋበዙ አሰልጣኝ እና ከዩኒቨርሲቲው የሶፍትዌር ባለሙያ ጋር በመተባበር የተሰጠ ነው።



Samara University
2024/25
Annual Magazine
Third Edition ሦስተኛ ዕትም
የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

ዲጂታል ቴክኖሎጂ ሽግግር የብቃትና ሰው ሃብት አስተዳ የንብረት አስተዳደር መተግበሪያ ሰልጠና

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ የንብረት አስተዳደር ሂደቱን ቀልጣፋ:ተአማኒ እና ብክነትን የሚቀንስ የንብረት አስተዳደር መተግበሪያ ወደ ሰራ ማሰገባቱን ተከትሎ በተቋሙ ለአራቱም ዘርፍ በየደረጃው ላሉ አመራሮች እና ሰራተኞች ከጥር 26-28 2017ዓ.ም ድረስ የቆየ በንብረት አስተዳደር ሰራ-አሰፈጻሚ የተዘጋጀ ሰልጠና ሰጥቷል::



ሠመራ ዩኒቨርሲቲ የውሰጥ የአሰራር ሂደቱን ቀልጣፋ እና ተአማኒ የሚያደርጉ 10 የሚሆኑ መተግበሪያዎችን በፋይናንስ:በግዥ: በብቃትና ሰው ሀብት: በሬጅስትራር: ፈተናዎች ማዕከል እንዲሁም በሌሎች ክፍሎች በመዘርጋት ላይ እንደሚገኝ ተገልጿል::

ዩኒቨርሲቲው በቅርቡ የመማር ማስተማር ሰራውንም ወደ ኢ-ለርኒንግ ለማሰገባት ዘመናዊ መልቲ ሚዲያ ስቱዲዮ አሰገንብቶ:መምህራንን እና ተማሪዎችን እያሰለጠነ የሚገኝ ተቋም ነው::




ዲጂታል ቴክኖሎጂ ሽግግር የመጀመሪያ ወሰነ ትምህርት የማጠቃለያ ፈተና በኦንላይን



ሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ትምህርት ዘመን የመጀመሪያ ወሰነ ትምህርት የማጠቃለያ ፈተና በዲጂታል መተግበሪያ (software) ከወረቀት ነፃ በሆነ መልኩ (Computer Based Exam) መፈተን ጀምሯል።

ዩኒቨርሲቲው ኮምፒውተርን መሰረት ያደረገ የማጠቃለያ ፈተና መሰጠቱን እምና የጀመረ ሲሆን: ዘንድሮም በተደራጀ ሁኔታ 1ሺ 164 የ3ኛ እና 5ኛ አመት መደበኛ ተማሪዎችን እንደሚፈትን ገልጿል::

የበይነ መረብ ፈተና ጠቀሜታው እንደ ሀገር በትኩረት እየተሰራበት ያለውን የትምህርት ጥራት ለማረጋገጥ፣ ቀጣይነት ያለው የዘመነ የፈተና ሰርዓት ለመዘርጋት እና ተበታትኖ በተለያዩ ኮሌጆች ይሰጥ የነበረውን ፈተና ወጥ በሆነ ሁኔታ በአንድ ማዕከል የወረቀትና ቀለም ወጪን የሚቀንስ አሰራር እንደሆነ ተገልጿል። ከዚህም በተጨማሪ ተቋሙ እየተገበራቸው ካሉት የዲጂታል ትራንሰፎርሜሽን ተግባራት አንዱ የምዘና ሰርዓትን ማዘመን ይገኝበታል።



Samara University
2024/25
Annual Magazine
Third Edition ሦስተኛ ዕትም
የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

ግቢ ውበት ልማት የሰመራ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ዓመት እና የካምፓስ አረንጓዴነት



የሰመራ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ዓመት እና የካምፓስ አረንጓዴነት ።የሰመራ ዩኒቨርሲቲ የግቢውን አካባቢ በማሳደግ ላይ በማተኮር ለመጪው የትምህርት ዘመን በሚያደርገው ቅድመ ዝግጅት ከፍተኛ እመርታ እያሰመዘገበ ነው።

የአስተዳደር ጉዳዮች ምክትል ፕሬዝዳንት ሁሴን ኡመር (ዶ/ር) በአሁኑ ወቅት እየተካሄደ ያለውን የዘንባባ ዛፍ ተከላ ሂደት ተመልክተው ገምግመዋል።

ይህም ዩኒቨርሲቲው ለ2017 የትምህርት ዘመን አዲስ እና ተመላሽ ተማሪዎችን ለመቀበል በዝግጅት ላይ ባለበት ወቅት ዩንቨርስቲው ደማቅ እና እንግዳ ተቀባይ አካባቢ ለመፍጠር ያለውን ጠቀሜታ አጉልቶ ያሳያል።

የበጀት አመቱ የመጀመሪያ ሩብ አመት በግማሽ መንገድ እየተካሄደ በመሆኑ ግቢው ለተማሪዎችና ለሰራተኞች ምቹ እንዲሆን ዩኒቨርሲቲው ሰፊ ሥራዎችን በማድረግ አድርጓል።



ልዩ ልዩ

እናት ከሁለት ልጆቻቸው ጋር የብሔራዊ ፈተና ወሰደዋል



በሰመራ ዩኒቨርሲቲ ሰሞኑን የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ከወሰዱት መካከል ከሁለት ልጆቻቸው ጋር የተፈተኑት ጠንካራ እናት ይገኙበታል::

ወ/ሮ መይረም እሰማኢል አሊ ይባላሉ:: ከሴት ልጃቸው ጦይባ አብደላ መሀመድ እና ከወንድ ልጃቸው ከኢብራሂም አህመድ ሀሰን ጋር ከዞን ሁለት: ዳሎል መሰናዶ ትምህርት ቤት ነው የመጡት::
የህይወት ሰንክሳር ሳይበግራቸው በማህበራዊ ሳይንስ ትምህርት ዘርፍ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተናቸውን ወሰደዋል::

ለመማር ያለዎት ቁርጠኝነት ለሌሎች እናቶችም አርአያ ይሆናልና በርቱልን እንላለን:: በቀጣይ ከልጆችዎ ጭምር መልካሙ ሁሉ እንዲሆንላችሁ እንመኛለን!!! ክብር ለአርአያዎቻችን!

ልዩ ልዩ

የሉሲ ካፕ ጨዋታ በሰመራ ሰታድየም



የሉሲ ካፕ ጨዋታ ሰመራ ዩኒቨርሲቲ እግር ኳስ ክለብ (Camelboys) ከጅቡቲው As Obock በሚያደርጉት ጨዋታ በሰመራ ሰታዲየም ዛሬ ተካሄዷል።

ጨዋታውን የሰመራ ዩኒቨርሲቲ አካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዝዳንት እና የሰመራ ዩኒቨርሲቲ እግር ኳስ ክለብ የቦርድ ሰብሳቢ ዶ/ር አብዱረህማን ከድር አሰጀምረውታል።

የሉሲ ካፕ መካሄድ የሁለቱም ክለቦች ተጨዋቾች በብሄራዊ ሊግ ለሚያደርጉት ጨዋታ ራሳቸውን ለመለካት:የክልሉን ስፖርት ለማነቃቃት እና ወዳጅነትን የሚያጠናክር መሆኑ ተመላክቷል::

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ እግር ኳስ ክለብ (Camelboys) እና As Obock ያደረጉት ጨዋታ በ90 ደቂቃ 1 አቻ ተጠናቆ: በመለለያ ምት ሰመራ ዩኒቨርሲቲ እግር ኳስ ክለብ 6-5 በሆነ ውጤት አሸንፏል::



Samara University
2024/25
Annual Magazine
Third Edition ሦስተኛ ዕትም
የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

ልዩ ልዩ የ59 አመቱ አባት-የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ወሰደዋል



በሰመራ ዩኒቨርሲቲ ስሞኑን ፈተና ከወሰዱ የ2016 ትምህርት ዘመን የ12ኛ ክፍል ተፈታኞች ውስጥ አንድ አባት እናስተዋውቃችሁ:: አቶ አሊ ሁሴን ሀመዱ ይባላሉ::
ከዞን አምስት 'ደዌ ወረዳ' መህመድ ቦዳያ ትምህርት ቤት ነው የመጡት::

እድሜያቸው 59 አመት ሲሆን እድሜያቸው እና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸው ሳይበግራቸው የማህበራዊ ሳይንስ ተማሪ ሆነው ቆይተው እነሆ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ወሰደዋል::

ለመማር ያለዎት ቁርጠኝነት ለሌሎች አርአያ ይሆናልና በርቱልን እያልን:
ለቀጣይ መልካሙን ሁሉ እንመኛለን!!!

ልዩ ልዩ 33ኛው ሀገር አቀፍ የትምህርት ኮንፈረንስ እውቅና እና የምስክር ወረቀት ሰጠ

33ኛው ሀገር አቀፍ የትምህርት ኮንፈረንስ ለባለድርሻ አካላት እውቅና እና የምስክር ወረቀት በመሰጠት ተጠናቀቀ።


የምስጋና የምስክር ወረቀት

ለ ሰመራ ዩኒቨርሲቲ

የ2016 የትምህርት ዘመን የኢትዮጵያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቅያ ሰርተፊኬት ፈተና በበይነ-መረብና በወረቀት እንዲሰጥና ስኬታማ ሆኖ እንዲጠናቀቅ ላበረከቱት ሁሉን አቀፍ ድጋፍና የላቀ አስተዋጽኦ ከፍተኛ ምስጋና እያቀረብን፣ ይህ የምስጋና የምስክር ወረቀት ተሰጥቷል።

የትምህርት ሚኒስቴር ያዘጋጀው 33ኛው ሀገር አቀፍ የትምህርት ኮንፈረንስ አፋር ክልል ትምህርት ቢሮ ኃላፊዎች፣የዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንቶች፣የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣የሙያ ማህበራትና ሌሎች የትምህርት



በኮንፈረንሱ ላይ የሰመራ ዩኒቨርሲቲ አመራሮችም የተሳተፉ ሲሆን በመጨረሻም ትምህርት ሚኒስቴር በ2016 የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ከፍተኛ ሚና ላበረከቱ ባለድርሻ አካላት እውቅና ሰጥቷል።

ልዩ ልዩ

በአካባቢ ስሙ 'እስኤራ' ወይም 'እስኤራይቶ (As-era/ As-erayto) በሳይንሳዊ ስሙ (Dracaena ombet) በመባል ይታወቃል::

በሠመራዩኒቨርሲቲ የሰነ-ህይወትትምህርት ክፍል መምህርእና የሶስተኛ ዲግሪያቸውንበእፅዋት ሳይንስ ዘርፍበመከታተል ላይ የሚገኙትመ/ር መሀመድሹምባህሪ ጋር ያደረግነውንቆይታ እንደሚከተለው እናቀርባለን::



የእስኤራዛፍ ድርቅን የመቋቋምችሎታ ያለው ፣ቅጠሉን እንስሳት ይመገቡታ፣ ፍሬውን ደግሞሰዎች ለምግብነት እንደሚጠቀሙትእንዲሁም ለመድሀኒትነት ይውላል:: የእስኤራ ግንዱ ለቤትእቃዎች ማለትም ለወተትማለቢያ ፣ ለአይብናቅቤ መያዣ ፣ለገንፎ ማቅረቢያ ፣ለንብ ቀፎ መሰሪያነትእንዲሁም በሰሩ ከፀሀይተከልሎ አረፍ ለማለትየሚጠቅም አይነተኛ የደረቃማናየህፀተ-ዝናብ አካባቢዛፍ ነው::


racaena ombet in peril in
thiopia: a call for attention and
ction
view Paper | Published: 16 April 2025
025) Cite this article
Biodiversity and Conservation
Aims and scope →
Submit manuscript →
aniel Hagos Berhe, Mohammed Shumbahri,
Hailu Araya Show authors
47 Accesses Explore all metrics →
bstract
he genus Dracaena comprises 190 living species
ith only a few species reaching the arborescent
rm i.e., the dragon tree group. It is widely
stributed in the tropical and subtropical

እስኤራይቶእስከ አሁን በተደረጉጥናቶች በኢትዮጵያ ውስጥበአፋር ክልል ፣በትግራይ ክልል አንዳንድቦታዎች እና በሶማሌክልል እንደሚገኝ አመላክተዋል።በተለያዩ የተፈጥሮና ሰው-ሰራሽምክንያቶች ከጊዜ ወደጊዜ ቁጥሩ በመመናመንላይ የሚገኝ ተክልነው።

ጥናቶችንመሠረት በማድረግ በሰመራዩኒቨርሲቲ የምርምርና ቴክኖሎጂሽግግር ም/ፕሬዝዳንትፅ/ቤት ስርየተቋቋመ የደረቃማ አካባቢብዝኃ-ህይወት ምርምር: ልማትና ጥበቃ ማዕከልተቋቁሟል:: ይህም በተቋማችንዋናው ግቢ ውስጥለህገር በቀል ዛፎችማዕከልነት የሚውል ቦታበመረከብ ከክልሉ የተለያዩወረዳዎች የእፅዋት ዘርእና ቡቃያ በማሰባሰብቦታውን የማልማት ሰራለመጀመር ዝግጅቱ ተጠናቋል:: ይህንንም ማዕከል እኔበሀላፊነት እያሰተባበርኩ እገኛለሁ።

ልዩ ልዩ

ተማሪዎች በኢትዮጵያ ምርት ገበያ እየተተገበረ ያለውን የዘመናዊ ግብይት ሥርዓት ጎበኙ



የሰመራ ዩኒቨርሲቲ የ4ኛ ዓመት የአግሪ ቢዝነስ ተማሪዎች ግንቦት 4 ቀን 2017 ዓ.ም የኢትዮጵያ ምርት ገበያን ጎብኝተዋል። በጉብኝታቸውም በምርት ገበያው የዘመናዊ ግብይት አተገባበርና አሠራርን ተመልክተዋል።

አቶ ዳዊት ሙራ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የከርፖሬት ኮሚዩኒኬሽን ሥራ አስኪያጅ ምርት ገበያው የተመሠረተበትን ዓላማና የተሰጡትን ተልዕኮዎች የሚፈፅምባቸውን መንገዶችና በሀገራችን የዘመናዊ ግብይትን በብቃት ከመምራት አኳያ ባለፉት 17 ዓመታት ያከናወናቸውን ተግባራት በተመለከተ ለተማሪዎቹ ገለጻ አድርገውላቸዋል።

ምርት ገበያው የግብርና ምርቶችን በማገበያየት ረገድ ከፍሪካ ቀዳሚ ተቋም መሆኑና የግብይት ሥርዓቱ ከድምፅ ማሰተጋባት ጀምሮ አሁን ላይ በበይነ መረብ የታገዘ የቀጥታ ኦን-ላይን ግብይት ሥርዓት ላይ መድረሱ ለሀገራችን የንግድ ሥርዓት ከፍተኛ አሰተዋፅኦ እንዳለው ሐላፊው ገልጸዋል።

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ የ4ኛ ዓመት የአግሪ ቢዝነስ ተማሪዎች ግንቦት 4 ቀን 2017 ዓ.ም የኢትዮጵያ ምርት ገበያን ጎብኝተዋል። በጉብኝታቸውም በምርት ገበያው የዘመናዊ ግብይት አተገባበርና አሠራርን ተመልክተዋል።

አቶ ዳዊት ሙራ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የከርፖሬት ኮሚዩኒኬሽን ሥራ አስኪያጅ ምርት ገበያው የተመሠረተበትን ዓላማና የተሰጡትን ተልዕኮዎች የሚፈፅምባቸውን መንገዶችና በሀገራችን የዘመናዊ ግብይትን በብቃት ከመምራት አኳያ ባለፉት 17 ዓመታት ያከናወናቸውን ተግባራት በተመለከተ ለተማሪዎቹ ገለጻ አድርገውላቸዋል።



ልዩ ልዩ

Journal of Afar-Af and Sociolinguistics ማስጀመሪያ መርሐግብር



ሰመራ ዩኒቨርሲቲ Journal of Afar-Af and Sociolinguistics የተባለ የምርምር ጆርናል ማስጀመሪያ መርሐግብር አካሂዷል::

ይህ ጆርናል በሁሉም የትምህርት መስክ፣ በዋናነት ግን በአፋርኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚሰሩ ጥናትና ምርምሮችን ለማሳተም ያስችላል ተብሏል።



በተጨማሪም ጆርናሉ ስለ አፋር ህዝብ ታሪክ ፣ባህል ፣ ወግ እና ቋንቋ የተሰሩ ብዝኃ መስክ(multi disciplinary) የሆኑ የጥናትና ምርምር ሰራዎች የሚታተሙበት በመሆኑ ዘርፈ ብዙ ፋይዳ እንዳለው ተነግሯል።

Journal of Afar-Af and Sociolinguistics ዓለም አቀፍ የምርምር ጆርናል ሊይዛቸው የሚገቡ ይዘቶችን ያካተተ መሆኑም ተመላክቷል።



ልዩ ልዩ ሶስተኛ የአፕሊይድ ሳይንስ ጥምረት ፎረም እንዲያስተናግዱ ተመረጠ።

ሁለተኛው የህዝብ ዩኒቨርሲቲዎች የአፕላይድ ሳይንስ (UAS) ኮንሰርቲየም ፎረም ከፍተኛ ማስታወቂያ ስመራ እና አሶሳ ዩንቨርስቲዎች ሶስተኛውን ዙር የተከበረውን መድረክ በጋራ እንዲያዘጋጁ ድምፅ ተሰጥቷል።



በአርሲ ዩኒቨርሲቲ የተካሄደው ሁለተኛው የዩኤኤስ ኮንሰርቲየም ፎረም ከ15 የመንግሰት አፕላይድ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ከትምህርት ሚኒስቴር እና ከሌሎች ዋና ዋና ባለድርሻ አካላት የተውጣጡ ተወካዮችን ተሳትፈዋል። የፎረሙ ውይይት በዩኒቨርሲቲዎች መካከል ያለውን ትብብር ለማሳደግ፣የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል እና በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ የሚሰተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት ያለመ ነው።

ልዩ ልዩ በበጎ ፈቃድ የተሰራ አረንጓዴ መናፈሻ ቦታ(Green Area) የምረቃ ስነ-ሰርዓት

ይህ ቦታ ከ8.7 ሚሊዮን ብር በላይ የወጣበት ሲሆን፣ በተማሪዎች መመገቢያ አዳራሽ (Cafe) ፊት ለፊት የተሰራ ውብ መናፈሻ ነው:: ስመራ ዩኒቨርሲቲ Center for Volunteerism (የበጎ ፈቃድ አገልግሎት) መሰርቷል::





ልዩ ልዩ "Center for Volunteerism(የበጎ ፈቃድ ማዕከል)"እና የበጎ ፈቃደኞች እውቅና ፕሮግራም



በሰመራ ዩኒቨርሲቲ "Center for Volunteerism/ የበጎ ፈቃድ ማዕከል"እና የበጎ ፈቃደኞች እውቅና ፕሮግራም የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር መሀመድ ኡሰማን: የክብር እንግዶች: እንዲሁም የማእከሉ መሰራች አባል የሆኑ ከፍተኛ እና መካከለኛ አመራሮች እና ተማሪዎች በተገኙበት ተካሂዷል::

በአቶ ሰይድ አህመድ (የሰይድ አህመድ ጠቅላላ ንግድ/ ጅንዱ ፋሚሊ በጎ ፈቃድ ከ8.7 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ ተደርጎበት የተሰራ ደረጃውን የጠበቀ የተማሪዎች አረንጓዴ የመናፈሻ ቦታ ተመርቋል::
ለዚህም ዩኒቨርሲቲው ለአቶ ሰይድ አህመድ (የሰይድ አህመድ ጠቅላላ ንግድ/ጅንዱ ፋሚሊ የእውቅና እና የምሰጋና ሰጥቷል::



Samara University
2024/25
Annual Magazine
Third Edition ሦስተኛ ዕትም
የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

ልዩ ልዩ ሰመራ ዩኒቨርሲቲ በተለያዩ መርሐ ግብሮች ያሰተማራቸውን ተማሪዎች አሰመረቀ

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ለ16ኛ ጊዜ በተለያዩ መርሐ ግብሮች ያሰተማራቸውን 667 ተማሪዎች አሰመርቋል።
ዩንቨርሲቲው በአጠቃላይ በመደበኛ እና ድህረ-ምረቃ መርሐ ግበር ካሰመረቃቸው 677 ተማሪዎች መካከል 149 ሴቶች መሆናቸውም ተገልጿል።



ዩኒቨርሲቲው የተማሪዎችን የመማር ማስተማር ሥርዓት በማሻሻል ረገድ ሰፊ ሥራዎችን በመሰራት፤ በመውጫ ፈተና ዘንደሮን ጨምሮ በተከታታይ ሶስት ዓመታት ከ87 በመቶ በላይ ተማሪዎች ማሳለፉንም ፕሬዚዳንቱ ገልፀዋል።



የሰመራ ዩኒቨርሲቲ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ እና የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ ሰለሺ ግርማ በበኩላቸው፤ ሰመራ ዩኒቨርሲቲ በአሁን ወቅት በቱሪዝም ፣በመዓድን እንዲሁም በአርብቶ አደር ግብርና ዘርፍ በትኩረት እንዲሰራ መደረጉ ልዩ ዩኒቨርሲቲ ያደርገዋል ብለዋል።
ተመራቂ ተማሪዎችም በተማሩት የሙያ ዘርፍ የወጡበትን ማህበረሰብ በታማኝነት ለማገልገል ቁርጠኛ መሆናቸውን ተናግረዋል።



Samara University
2024/25
Annual Magazine
Third Edition ሦስተኛ ዕትም
የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

ማህበረሰብ ሳምንት

የጂኦ-ቱሪዝም ቀን በአቤ ሀይቅ እና ታሪካዊ ቦታዎች



በሰመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017ዓ.ም አመታዊ የማህበረሰብ አገልግሎት ሳምንት 6ተኛ ቀኑን የጂኦ-ቱሪዝም ቀን በአፋንቦ አቤ ሀይቅ እና በአፋር የሱልጣኖች ቤተ-መንግስት እና ከልጅ እያሱ ታሪክ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ታሪካዊ ቦታዎችን የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ እና ተማሪዎች ጉብኝት አድርገዋል::

ቱሪዝም (Tourism) እና ጂኦሎጂ(Earth Science) ግብርናን(Dry-Land Agriculture) ጨምሮ የሰመራ ዩኒቨርሲቲ የልህቀት መሰኮች በመሆናቸው በማህበረሰብ አገልግሎት ሳምንት መርሃግብር ውስጥ በልዩነት ትኩረት ተሰጥቷቸው ሲከናወኑ ቆይተዋል::

አካባቢው የታላቁ ሰምጥ ሸለቆ አካል በመሆኑ የመሰህብ ቦታዎች የጂኦሎጂን እና የቱሪዝምን(Geo-tourism)ጂኦቱሪዝም መዳረሻ እንደሆኑ ይገለጻል::



Samara University
2024/25
Annual Magazine
Third Edition ሦስተኛ ዕትም
የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

ማህበረሰብ ሳምንት ነፃ የህግ ድጋፍ እና ግንዛቤ ማሰጨበጫ-



ነፃ የህግ ድጋፍ እና ግንዛቤ ማሰጨበጫ በህግ ትምህርት ቤት በጎ ፈቃደኛ መምህራን እና ተማሪዎች በሰመራ አገልግሎት ሰጥተዋል::

በዛሬው እለትም የቱሪዝም ቀንን ምክንያት በማድረግ በአፋንቦ አቤ ሀይቅ: የሱልጣኖች ቤተ-መንግሰት እና የልጅ እያሱን ታሪካዊ ቦታዎች ለመጎብኘት የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ተጉዟል::



ማህበረሰብ ሳምንት የትምህርት ሳምንት Empowering Minds, Enriching Communities



በሰመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017ዓ.ም አመታዊ የማህበረሰብ አገልግሎት ሳምንት 5ተኛ ቀኑን ይዟል::

የትምህርት ሳምንት "Empowering Minds, Enriching Communities!" በሚል መሪ ሀሳብ ከሁሉም ኮሌጆች በተውጣጡ በጎ ፈቃደኛ መምህራን በሰመራ እና ሎጊያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲሰጥ የነበረው የትምህርት አገልግሎት ::

ፕሮግራም የጥያቄ እና መልስ ውድድር፣ የእጠናን ሰልቶችን ፣ የስነ-ልቦና ምክሮችን ለተማሪዎች መሰጠት ተችሏል::

በሰመራ እና ሎጊያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች መካከል በተካሄደው የጥያቄ እና መልስ ውድድር፣ የሎጊያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአሸናፊነት አጠናቋል:: በተጨማሪም ዩኒቨርሲቲው ለሁለቱም ትምህርት ቤቶች 500 የማጣቀሻ መፅሀፍት በስጦታ አበርክቷል::



ማህበረሰብ ሳምንት

የማህበረሰብ አገልግሎት ሳምንት-የግብርና ሙያዊ ድጋፍ

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017ዓ.ም አመታዊ የማህበረሰብ አገልግሎት ሳምንት የግብርና ቀን በህፀተ-ዝናብ አካባቢ ግብርና ኮሌጅ መምህራን ለዩኒቨርሲቲው የዱብቲ የፍራፍሬ ግብርና ማዕከል ሰራተኞችና የአካባቢው ማህበረሰብ ሙያዊ ድጋፍ መሰጠት አስችሏል::



የማህበረሰብ አገልግሎት ሳምንቱ ነገ 5ኛ ቀኑን የሚይዝ ሲሆን፣ላለፉት 4 ቀናቶች በሰመራ እና ሎጊያ 1ኛ እና 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲሰጥ የነበረው የትምህርት አገልግሎት ማጠቃለያ ነገ ይካሄዳል:: በተጨማሪም የነፃ እንሰሳት ህክምና፣ የህግ አገልግሎት መርሃግብሮች ማጠቃለያ ነገ ይካሄዳል::

ሳምንቱን በሙሉ በዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ መካከል ሲደረግ የነበረው የጤና ሰፖርት የእግር ኳስ ውድድር "በኑር ሁሴን አሊ(ኑሩ ከዳባ)" እግርኳስ ሜዳ ጨዋታዎችን እያስተናገደ ዛሬም የቀጠለ ሲሆን፣የመረብ ኳስ፣የሩጫ እና ሌሎች ውድድሮችን አካቶ ቅዳሜ እለት ፍፃሜዉን የሚያገኝ ይሆናል::



ማህበረሰብ ሳምንት Health Screening-የደም ግፊት እና የስኳር ልኬት/ምርመራ

-በሰመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017ዓ.ም አመታዊ የማህበረሰብ አገልግሎት የጤና ሳምንት-3ኛ ቀን ፕሮግራሞች እንደቀጠሉ ናቸው። ትናንት በእጅጉ የተሳካ የደም ልገሳ ተካሂዷል::



የጤና ሳምንት አገልግሎት መርሃ ግብር ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ነፃ የጤና ምርመራ አገልግሎት ማለትም Blood Pressure and Blood Sugar Screening and Counciling ሰራ ተከናውኗል::

በተጨማሪም የህክምናና ጤና ሳይንስና ኮሌጅ ባለሙያዎች በሰመራ አንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ነፃ የጤና ትምህርት እና ምክር አገልግሎቶች በተለይ የግል እና የቡድን ጤና ፣ንፅህና፣አጠባበቅን የተመለከቱ ትምህርቶች ለተማሪዎች እየተሰጡ ነው::



ማህበረሰብ ሳምንት

የማህበረሰብ አገልግሎት ሳምንት "የጤና ቀን" በደም ልገሳ

የማህበረሰብ ሳምንት

አመታዊውን የማህበረሰብ አገልግሎት ሳምንት "የጤና ቀን" ምክንያት በማድረግ የደም ልገሳ በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ ተካሂዷል።



በመርሃግብሩ የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር መሀመድ ኡስማን፣ የአፋር ክልል ጤና ቢሮ ሀላፊ አቶ ያሲን ሀቢብ፣ ምክትል ፕሬዚዳንቶች፣ መካከለኛ አመራሮች፣ ተማሪዎች በተገኙበት የደም ልገሳ ተካሂዷል::

የጤና አገልግሎቶች በተለያዩ የግንዛቤ መፍጠሪያ መርሃግብሮች በትምህርት ቤቶች ሳምንቱን በሙሉ እንደንሚካሄድ ተገልጿል::
የዚሁ የጤና ቀን አካል የሆነው ነፃ የእንሰሳት ህክምና እና ጤና አጠባበቅ የግንዛቤ ማሰጨበጫ መርሃግብሮች እንደሚካሄዱ ተገልጿል::



Samara University
2024/25
Annual Magazine
Third Edition ሦስተኛ ዕትም
የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

የፎቶ ማህደር









Samara University
2024/25
Annual Magazine
Third Edition ሦስተኛ ዕትም
የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

የፎቶ ማህደር









Samara University
2024/25
Annual Magazine
Third Edition ሦስተኛ ዕትም
የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2017 ዓ.ም አመታዊ መጽሔት

የፎቶ ማህደር









የፎቶ ማህደር









አድራሻችን

@Samara University of Ethiopia

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ በሰሜን ምስራቅ ኢትዮጵያ፣ በአፋር ክልል፣ ዞን 01 አውሲ ረሱ፣ በሰመራ ክፍለ ከተማ፣ ከዋናው ኢትዮ-ጅቡቲ መንገድ 4 ኪ.ሜ ገባ ብሎ የሚገኝ ነው።

- **የፖስታ ሳጥን ቁጥር-132**
- **የአውሮፖ ህብረት መታወቂያ -E10347045**
- **ድረገጽ-su.edu.et**
- **ኢሜይል-president@su.edu.et**
- **ስልክ ቁጥር-0944481518**